# ምዕራፍ ዐሥራ አንድ

## በ17ኛው አንቀጽ አለመሳካት የነአንቶኔሊ ወደ አገራቸው መመለስ

ኮንት አንቶኔሊ ፣ የኢጣልያን ንጉሥ ደብዳቤ ይዞ ከመጣ ወዲህ ቀድሞ ከነበሩት ከኮንት አውጉስቶ ሳሊምቤኒና ልጥ ማረፊያ ከሚቀመጠው ከዶክተር ሊዎፖልድ ትራቬርሲ ጋር እየተመካከረ ከላይ የተመለከትነውን ማስታወሻ በዝርዝር አቅርቦ በማግባባትም ፣ በማስፈራራትም ፣ በማባበልም የ17ኛው አንቀጽ ቃል እንዲረጋ ምንም ቢጣጣር አልሆነለትም ። የሚጣጣረውም ከራሱ መንግሥት የተሰጠውን መመሪያ እግብ ለማድረስ እንጂ ፣ በነገሩ ራሱ ያመነበት አይመስልም ። ስለዚህ አንቶኔሊ በዚህ ጊዜ በሁለት ወገን ተቸግሮ እንደ ተወጠረ ይታያል ።

ባንድ ወገን ያፄ ምኒልክንና የእቴጌ ጣይቱን ፣ የሌሎቹንም በዚህ ጉዳይ የሚያገባቸውን መኳንንት ቁጣና ክርክር በመመልከት 17ኛው አንቀጽ የገባው በወዳጅነትና በፈቃድ እንጂ ፣ በእውነትም በግዴታ ወይም በበላይ ጠባቂነት መንፈስ የተጻፈ አለመሆኑን በመጥቀስ ፣ "ይልቅስ ይኸንን በመሰረዝ ምኒልክን አስደስተን ስለ ወሰኑ ጉዳይ ብንከራከር ይሻላል" እያለ ላለቆቹ ወደ ሮማ ሲጽፍ ፣ "አንድ ጊዜ ለየመንግሥታቱ አስተላልፈን የበላይ ጠባቂነታችን ከታወቀልን በኋላ መሰረዙ ክብራችንን ስለሚነካ ፣ እዚያው እንደ ምንም በርትተህ አንቀጹ እንዲረጋ አድርግ" የሚል የትእዛዝ መልስ ይደርሰዋል ። በዚህም ረገድ ፣ የበላይ አለቃውን ክሪስፒን ማስደሰት እንጂ ፣ ማስቀየም ስለማይፈልግ ከአቅሙ በላይ በሆነው ጉዳይ ገትሮ ሲከራከር ይገኛል ።

በሌላ ወገን ደግሞ ፣ ያገር ተወላጆቹ ዐዋቂዎቹና የውጭ ተወላጆቹ ፈረንሳዮቹም ፣ መስኮቦቹም ሁሉ ፣ "ይህ ቃል የረጋ እንደሆነ ልክ የኢጣልያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ እንደ በላይ ጠባቂ (ፕሮቴክቶሬት) መሆኑን ስለሚያስገነዝብ መሰረዝ አለበት" እያሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ያስረዳሉ ። ንጉሠ ነገሥቱም እየጠሩ ፣ "ድሮውንም ይኸ ቃል ባይገባስ ቢቀርስ ብዬህ ነበር ። አሁንም ይኸን ቃል የሚናገረው

አንቀጽ ይሰረዝና ሌላው ይርጋ ፤ ወይም ውሉ እንደ ግዴታ እንዳይ ቆጠር የሚያስችል ሌላ ቃል ይግባና ወዳጅነታችን ይቀጥል ። ከሁሉም ይልቅ አንቀጹ ፈጽሞ ይቅር'' እያሉ ሲያዋክቡት ፣ እርሱም ''ማናቸውንም ለመንግሥቴ ሳላስታውቅ በራሴ ፈቃድ የምችለው ነገር የለም'' እያለ መልስ በመስጠት ሰፋ ያለ የክርክር ውዝግብ ከተፈጠረ በኋላ ፣ በመጨረሻ አንድ ጽሑፍ በደብዳቤ መልክ ተዘጋጅቶ የንጉሠ ነገሥቱ ማኅተም ፣ የአንቶኔሊ ፊርማና ማኅተም ታትሞበት ለኢጣልያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ እንዲላክና መልሱ ከዚያ እንዲጠበቅ ስምምነት ተደረገ ።

ጽሑፉ እንደ ተለመደው ፡ በደብዳቤ መልክ....ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ . . . ይድረስ ከወዳጃችን ከኡምቤርቶ 1ኛ የኢጣልያ ንጉሥ. . . ብሎ ይጀምርና ፣ ሀ/በፊተኛው ደብዳቤ የኢጣልያንኛው አነጋገር ቀርቶ ያማርኛው ብቻ እንዲሆን ብለው አንቶኔሊን ቢጠይቁት ከንጉሤና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳላስፈቅድ አልችልም ማለቱ ፤ ለ/ አሁን ግን ይህ 17ኛው አንቀጽ ቃል በፍጹም እንዲቀር ከአንቶኔሊ ጋር ተስማምተናል ። ይህንንም በወዳጅነት ስናደርግ መቼም ወደፊትም ቢሆን ፣ በወዳጅነት ከውጭ አገር የምፈልገውን በግርማዊነትዎ እርዳታ ለማድረግ መፍቀዴን በደብዳቤ ስገልጽልዎ ይኸውም በወዳጅነት ነው ። እንደኔ ያለ የነጻ አገር (መሪ) በወዳጅነት ካልሆነ በቀር የሚረባ ነገር የለውም የሚልና ሌላም የወዳጅነት አነጋገር ያለበት ነው ። በዚህ ጽሑፍ እላይ እንደ ተባለው ሁለቱም ወገኖች አትመውበት አንዳንድ ግልባጭ ከተለዋወጡ በኋላ እርሱም አንዱን ግልባጭ ይዞ ሔደ ። እርሱ ግን ፣ ''. . . 17ኛው አንቀጽ ይቅር'' ሲባል የተረዳው ፣ ''እንዳለ ይቅር ፤ ይኸውም ማለት እንዳለ ይርጋ'' የተባለ መስሎት ኖሯል ።

ስለዚህ ፡ በአማርኛ የተጻፈውንና የፈረመበትን ከቤቱ ወስዶ በራሱ አስተርጓሚ ባቶ ዮሴፍ (ሌላ ዮሴፍ የልጥ ማረፊያው) ቃል በቃል እያስተረጐመ ሲረዳው ፣ የ17ኛው አንቀጽ መሰረዙን እንደ ተስማማበት ሆኖ መጻፉን የሚያረጋግጥ መሆኑን ተገነዘበው ። በዚህ ጊዜ በንዴት በማግሥቱ ተመልሶ ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ ፣ ራስ መኰንንና ግራዝማች ዮሴፍ ወዳሉበት እልፍኝ ገብቶ ፣ ''እኔ የውጫሌ ውል የተደረገው ለ5 ዓመታት ነው ፤ ከዚሁ 2 ዓመታት ተቀንሶለታል ። ስለዚህ የ17ኛው አንቀጽ ጉዳይ እንዳለ ይርጋ ፣ ነገሩም መነሣቱ ይቅር አልሁ እንጂ አንቀጹ ይቅር ፤ ይሰረዝ አላልሁም ። አሁንም 'ይሰረዝ' ያላልሁትና ያልተናገርሁት ቃል ነውና የተጻፈው ይለወጥ'' ብሎ አመለከተ ።



ዐፄ ምኒልክም ፣ ''በግልጽ ባስተርጓሚ ተነጋግረን ተስማምተን የተጻፈውና የታተመው አሁን ቢጸጽትህ አይለወጥም'' ብለው መለሱለት ። በዚህ ጊዜ ፊቱን ወዳስተርጓሚው ወደ ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ መልሶ ፣ ''ይኸን ሁሉ የምትዘባርቅ አንተ ነህ'' ብሎ ተሳደበ ። በዚህ ጊዜ እቴጌ ጣይቱ ፣ ''ቢያጠፋስ አሽከራችንን እኛ እንቀጣዋለን እንጂ አንተ መሳደብ የለብህም'' ብለው በተግሣጽ መልክ መለሱለት ። ከዚያ እርሱ ፣ ''ውጫሌ ላይ የተዋዋልንበት የፈረንሳዩ ቃል ይታይ'' ሲል ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌ ጣይቱ ፣ ''እኛ የምናውቀው አማርኛውን እንጂ የፈረንጅ ቋንቋ አናውቅም'' ብለው ሲመልሱለት በጣም ተበሳጭቶ ''ተሰርዟል'' የሚለው ቃል ያለበትንና እርሱም የፈረመበትን የንጉሠ ነገሥቱም ማኅተም ያለበትን ጽሑፍ ከፊታቸው በጫጭቆ ፣ ''እንግዲህ ወዳጅነት ቀርቷል ። ጦርነት ብቻ ነው'' የሚል ቃል ወርውሮ በድፍረት ደንፍቶ ለመሔድ ሲወጣ ፣ እቴጌ ጣይቱ ከት ብለው በመሳቅ ፣ ''ጦርነቱን የዛሬ ሳምንት አድርገው ፣ በዚህ የሚደነግጥልህ የለም'' ብለው በታላቅ ቁጣ መለሱለት ።[1]

ሁኔታው ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ በቀር እዚያ ያሉትን እነራስ መኰንንንና እነግራዝማች ዮሴፍን ሁሉንም አስገረማቸው ። ሁሉም አድራጎቱን እንደ ብልግና ቈጠሩበት ። እውነትም ቀድሞውኑ ያማርኛውን ጽሑፍ ከመፈረሙ በፊት ማስተርጐምና መረዳት ፣ ከተረዳ በኋላ መፈረም ወይም እምቢ ማለት ነበረበት እንጂ ፣ ተመልሶ ''ቃሌ አይደለም'' ብሎ ጽሑፉን ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት መቅደድ ፣ የራሱ ዜጋ ያልሆነውን አስተርጓሚ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት መገሠፅ ከየትም አገር ሥነ ሥርዓት ውጭ መሆኑ የታወቀ ነው ።

የሆነ ሆኖ ፣ በእጁ ያለውን ቀዳዶ በንጉሠ ነገሥቱ እጅ ያለውንም ለማስመለስ ፈቅዶ ሳይሆንለት ከቀረ በኋላ ፣ ወደ መኖሪያ ቤቱ ሔዶ ጉዳዩን ለሥራ ጓደኞቹ ለኮንት ሳሊምቤኒና ለዶክተር ትራቬርሲ ነግሮ ከተመካከሩ በኋላ ፣ ''ከእንግዲህ ወዲህ ምንም ለመሥራት አንችልምና ወደ አገራችን እንመለስ'' ብለው ወሰኑ ። ቢሆንም ፣ ''ይኸን ያህል ዘመን የቆየንበትን አገር እንደዚሁ ትተን ዝም ብለን መሔድ አይገባንምና በደብዳቤ ንጉሠ ነገሥቱን እንሰናበት'' ብለው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን በኢጣልያንኛ ጽፈው ሦስቱም ፈርመው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ ።

---

1 አፈወርቅ ዘብሔረ ዘጌ ስለ አወጣጡ ሲጽፉ ፡ ''ሰላምታ ነፍጎ እንደ ቡኸር በንጉሦች ፊት ዘሎ ገና ተልፍኙ ቆቡን ተራሱ አድርጎ እንደ ዘላን ከበርቱ እያፎጫጨ ቢሔድ...'' በማለት በራሳቸው ልዩ አነጋገር ገልጸውታል ። ዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ገጽ 66—79 Let - -Marefia, L. Traversi, Cap. XXXVII

ለግርማዊ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ። በሁለት አገሮች መካከል ክርክር ሲፈጠርና ክርክሩ መንገድ ሳይገኝለት ሲቀር የዚያ መንግሥት መላክተኞች በያገራቸው መመለስ በሠለጠኑት የክርስቲያን አገሮች የተለመደ ነው ። ዛሬ እነሆ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መንግሥታት መካከል በወዳጅነት ለመሥራት የፈተንነው ሥራ ፍሬ ቢስ ሆኗል ። በዚህ ዓይነት የኛ በግርማዊነትዎ ግዛት መቆየት ከንቱ ነው ። ለንጉሣችን ትእዛዝ ታማኞች ሠራተኞች እንደ መሆናችን በሐረር በኩል አድርገን ወደ አገራችን እንድንመለስ እንዲፈቀድልን እንለምናለን ። በምንሰናበትበት ጊዜ ፣ እዚህ አገር በደግነት ስለ ተስተናገድንበት ለግርማዊነትዎ ምስጋና እያቀረብን ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ለግርማዊነትዎና ለቤተሰቡ ለሠራዊቱም ደስታና ዕድል እንዲሰጥ እንለምናለን ።

ተጻፈ አዲስ አበባ የካቲት 9 ቀን 1891 ዓ. ም. እ.ኤ.አ

ፊርማ አንቶኔሊ
ሳሊምቤኒ
ትራቬርሲ

ለዚህ መልስ ፣ ዐፄ ምኒልክ እንደዚህ ብለው ጻፉለት ።
"ይድረስ ከኮንት አንቶኔሊ የተለመደ ሰላምታ ፤

እዚህ አገር ከመጣህ ዠምሮ እስካሁን በኔ መንግሥትና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ያለው ጉዳይ ስምምነት እንዲያገኝ በትእግሥት ስደክም ቆየሁ ። አንተንም እንደ ልብ ወዳጄ እንጂ እንደ አንድ የመንግሥት መላክተኛ አልመለከትህም ነበር ። አንተም እንደ ተቻለህ ወዳጅነትህን አሳይተኸኛል ።

አንድ የመንግሥት መላክተኛ እንኳን ንጉሠ ነገሥቱን ያገሩንም ሕዝብ ሊያከብር ይገባል እንጂ ፣ ትናንት እንደ ሠራኸው ያለ ሊሠራ አይገባም ። ጉዳዩ ያለቀ መስሎኝ የውሉን አሳብና ንጉሡ ኡምቤርቶ ለጻፉልኝ መልስ የተዘጋጀውንና ሁለታችንም ያተምንባቸውን ደብዳቤዎች እኔን በፍጹም ሳትጠይቀኝ ላንድ ንጉሥ የሚገባውን ክብር አጓድለህ በመቅደድህ አሳዝነኸኛል ። በዚህ በሠራኸው አስበህ የተጸጸትህ ሲመስለኝ አንተና ኮንት ሳሊምቤኒ ዶክተር ትራቬርሲም ወደ አገራችን እንድንሔድ ብላችሁ ጠየቃችሁኝ ። በፊት ይኸ ነገር ሳይደርስ የስምምነቱን ነገር ስንነጋገር ያልተስማማንበትን ወገን ንጉሡ ኡምቤርቶና ክሪስፒ ካልፈቀዱ አይሆንም ብለህ ለዚሁ ተመካክረን ጽፈን መልሱን እመጠበቅ ላይ ነበርህ ። አሁን መልሱ ሳይመጣ ያለፈቃዳችን ብትሔድ ደስ አይለኝም ! እንሒድ ብላችሁ ከቆረጣችሁ ደግሞ አልከለክላችሁም ። እናንተ እምቢ ብትሉና ብትሔዱም በእናንተ ምክንያት በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ያለው ወዳጅነት የሚጠፋ አይመስለኝም ።

ተጻፈ የካቲት 3 ቀን 1883 ዓ.ም. 1

1 እነዚህ ደብዳቤዎች ካርሎ ሮሴቲ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ትርጕማቸው በኢጣልያንኛ ይገኛል ። Storia Diplomatica . . .C. Rossetti; P. P. 102 - 103



አንቶኔሊ ፣ ከኢጣሊያ አገር መልስ መጠበቅ እንደማይጠቅመው በመገንዘብ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ ወደ አገሩ ለመመለስ ተነሣ ። ንጉሠ ነገሥቱም በጥሩ ዐይነት የተጫኑች በቅሎ ስጦታ በቀር በየአደረበት ፍሪዳው ፣ እንጀራው እንዳይጐድልበት ትእዛዝ ለየሹማምንቱ አስተላልፈው ነበር ። ኢጣልያኖቹም ከአዲስ አበባ ልጥ ማረፊያ (አንኮበር) ደርሰው የልጥ ማረፊያ ጣቢያቸውን ፣ "እስክንመለስ ድረስ ጠብቅ" ብለው ገመዳ ለሚባል ሰው አደራ ብለው ከልጥ ማረፊያ ወደ ሐረር ሔዱ ከሐረርም እንደዚሁ ቺዛሬ ኔራሲንና በርሱ እግር ተሾሞ ሐረር ራስ መኰንን ዘንድ ለመቀመጥ የመጣውን ካርሎ ዲሩዲን ጨማምረው በዘይላ በኩል አድርገው ወደ አገራቸው ተመለሱ ። እንደ ተመለሱም አንቶኔሊ በምኒልክ ፊት ያሳየውን የብልግና አቅዋም በመገንዘብ ፣ በኢጣልያ አገር ወቀሳ ዠምረውት ነበርና ላለቆቹ ሁኔታውን በራፖር በገለጸበት ላይ ራሱን ከጥፋተኛነት ለማዳን ሲል ፣ "ጽሑፉ በስሕተት ነውና የተጻፈው እመልስልሃለሁ ብለው በኋላ ከዱኝ" በማለት ጥፋቱን ሁሉ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለመላከክ ሞከሯል ። በኢጣልያም አገር የርሱን አባባል የሚያስተባብል ወኪል ስለሌለ ፣ ዐፄ ምኒልክ አንቶኔሊ እንደሔደ ወዲያው አከታትለው የርሳቸውን አቅዋም ለኢጣልያ ንጉሥ ዝርዝር ጉዳዩን በፈረንሳይኛ ቋንቋ አጽፈው በመላክ ለማስተባበል ሞክረዋል ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ከሥልጣን ላይ ከወጡ ዠምሮ ያለፈውን በኢትዮጵያ የደረሰውን የጦርነት ዘመን በመገንዘብ ፣ በዚህ የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ በጫኑበት ወቅት ባገር ላይ የተነሣውን የከብትና የሰው እልቂት በማሰብ ፣ በቅርብ ጊዜ በእርሳቸው ቀጥተኛ አመራር ሥር የተጠቃለሉትን ታላላቅ አውራጃዎች ለማጠናከር በማናቸውም ረገድ ባገር ላይ ትልቅ ጦርነት ከውስጥም ፣ ከውጭም እንዳይቀሰቀስ አጥብቀው ከመጣር ላይ እንደሆኑ ሁኔታው ያስገነዝበናል ። በየምክንያቱ ለውጭ አገር መንግሥታት መሪዎች በጻፉዋቸው ደብዳቤዎች ውስጥ ሕዝቡን ከጦርነት ለማሳረፍ ፣ ወዳገር ውስጥ የአውሮፓን ሥልጣኔ ለማስገባት ያላቸውን ምኞት ደጋግመው መግለጻቸው ተጠቅሷል ። ከኢጣልያም ጋር ጦርነት እንዳይነሣ በበኩላቸው አጥብቀው የሚጣጣሩት ለዚህ ነው ። በየደብዳቤያቸውም ፣ ባነጋገራቸውም ላይ የሚታየው ይኸው ሰላምና ዕረፍት ፈላጊ መሆናቸው ነው ።

ኢጣልያኖቹ ፣ በአውሮፓውያንነታቸው ፣ በሥልጣኔያቸውና በኃይላቸው ተማምነው የሚመኩ እንደ እንግሊዝ ፣ እንደ ፈረንሳይ ፣ እንደ ጀርመንና ቤልዥክ በአፍሪካ ሰፊ ቅኝ አገር ለማግኘት በምኞት ተውጠውና ቆርጠው የተነሡ በመሆናቸው ፣ ባፄ ምኒልክ በኩል የሚደረገውን ሰላማዊ መንገድ ሁሉ ከምንም አልቆጠሩትም ። በፊተኛው

ዘመን ምኒልክን ባዬ ዮሐንስ ላይ ለማስታጠቅና ለማዋጋት ተነሥተው በምኒልክም ፥ በዮሐንስም መቻቻል የሳተውን የውስጥ ጦርነት አሁን አንቶኔሊ ከነጓደኞቹ 17ኛውን አንቀጽ ለማስቀበል ፈትኖና ሳይሳካለት ቀርቶ ወዳገሩ ከተመለሰ በኋላ ፥ ራስ መንገሻን አስታጥቀው ባዬ ምኒልክ ላይ ለማስነሣትና ለማዋጋት ፥ ከዚህም ውጊያ መካከል የነርሱ የመስፋፋት ዓላማ ግቡን እንዲመታ ይጣጣሩ ዠመር ። ይኸን የመሰለውንም የከፋፍለህ ግዛ ዓላማ ጣልያኖቹ በምኒልክ ላይ ለመፈጸም ሲመኙ ፥ ይልቅስ ምኒልክ ኢጣልያንና መንገሻን እርስ በእርሳቸው ከፋፍለው እንደምን እንደ አዋጉዋቸው ወደፊት ስንመለከት ፥ በፖለቲካ ዘዴ ትምህርት ካገኙት ኢጣልያኖች ይልቅ ፥ ምንም አውሮፓዊ ትምህርት ያልቀሰሙት ምኒልክ በልጠዋል ። ስለዚህ ነው አንጀሎ ዴልቦካ የሚባለው የኢጣሊያ ጸሐፊ ፥ "... መንግሥቱን ለመገንባት ምኒልክ ምንም ዓይነት አጋጣሚ ጊዜና ሁኔታ አያመልጠውም ። በሚያምኑቱት ወገኖች ላይ ይጠቀማል ። የርሱ መዘግየት በምቹው ጊዜ ላይ ለመጠቀም ነው ። ይኸም በፍጥረቱ ያለውን የፖለቲካ ባሕርያዊ ስጦታ ያሳያል"[1] ሲል አትቷል ።

1. Gli Italia in Africa Orientale, P. 222.



## ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት

### የውጫሌ ውል በግራዝማች ዮሴፍና በግለኞች ላይ ያደረሰው ችግር

የውጫሌው ውል ፥ 17ኛው አንቀጽ ያስከተለው ችግር በዝርዝር ሆኖ በየመልኩ ቢጻፍ ራሱ አንድ መጽሐፍ ይወጣዋል ። አሁን በመጨረሻ ዘመን ጉዳዩን በዝርዝር ያጠኑት የኢጣልያ ጸሐፊዎች ነገሩን ከበላይ ሆኖ በሐሰት ፥ በአጠራጣሪና በተጭበረበረ መንገድ አንቶኔሊ ያቀረበለትን ውል በመቀበል ፥ ምክር ቤቱን በማታለል ወደ ዓድዋ አዋራጅ ጦርነት የመራው ራሱ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ መሆኑን ተገንዝበውታል ። ከነዚህም ውስጥ ካርሎ ጁሊዮና አንጀሎ ዴልቦካ ፥ ናፖሊዎኒ ኮላጃኒ ፥ ቢዘኒ አኪለ ይገኛሉ ።[1]

ዮሴፍ ንጉሤ ፥ የትግራይ ተወላጅ ናቸው ። በምጥዋ በካቶሊክ ሚሲዮን ተምረዋል ። በኋላም ሙሴ አርኑ ከሚባሉት የፈረንሳይ ነጋዴ ዘንድ ተቀምጠው በአስተርጓሚነት ሠርተዋል ። ቀጥሎም ከጓደኛቸው ከገብረ ተክሌ ጋር ሆነው ወደ ምኒልክ ገብተው በማስተርጐምም ፥ ወደ ኤደንና ወደ ጅቡቲም በመላክ ንጉሥ ምኒልክን አገልግለዋል ። ገብረ ተክሌ ኤደን ሆነው ምኒልክ አገራቸውን ለማሠልጠን ያላቸውን ምኞት ከመግለጽ ጋር ከፈረንሳይ መሪዎች ከነማጀንታ ጋር እንዲወዳጁ ከመጣጣር አልፎ ፥ በነአቡበከርና በነአንፋሪ አማካይነት የጦር መሣሪያ ለምኒልክ እንዲደርስ ያደርጉ ነበር ።[2]

በምኒልክ ቤተመንግሥት በአነጋጋሪነት ከገብረ ተክሌ ፥ ካቶ ዮሴፍ (የልጥ ማረፊያው) ፥ ካቶ ገብርኤልም ፥ ካቶ ሚካኤልም ፥ ከማንም ኢትዮጵያዊ የበለጠ የታወቁት ዮሴፍ ንጉሤ ናቸው ። እርሳቸውም በዚሁ አገልግሎታቸው የግራዝማችነት ማዕረግ አግኝተው የታወቁ ሆነዋል ። ከውጫሌ ውል በኋላ ፥ ራስ መኰንንን ተከትለው ሮማ መሔዳቸውን በምዕራፍ አምስት ላይ አውስተናል ። ከጠቡ በፊት

1 Italiani in Africa Orientale, A. Del Boca,, PP. 352 - 353

2 በሰኔ 11 ቀን በ1870 ዓ.ም. ከኤደን ለማጀንታ የጻፈው ደብዳቤ ቁ. 261 ፥ ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ።

በነአንቶኔሊ አማካይነት ልጃቸው አበራ ዮሴፍ ሮማ ላይ እየተማረ አድጓል ይባላል ።

ግራዝማች ዮሴፍ ንጉሤ ፣ ባስተርጓሚነታቸው የተነሣ በውጫሌው ውልና በ17ኛው አንቀጽ ምክንያት ከሁሉ የበለጠ ከችግር ላይ የተገኙ ናቸው ። ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌይቱ ፊት ፣ "ይኽን ሁሉ የምትዘባርቅ አንተ ነህ" ብሎ አንቶኔሊ እንደ ሰደባቸው ተመልክተናል ። ከኢጣልያኖቹ ዘንድ አስተርጓሚዎቹ ሁሉ በብድርም ፣ ያለብድርም ገንዘብ ተቀብለዋል የሚል ወሬ ስለነፈሰ ፣ በእቴጌይቱና በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ጥርጣሬ አድሮ ላጭር ጊዜ ፊት የመነሣት ዕድል የገጠማቸው ይመስላል ። የዚህን ጉዳይ ሳሊምቤኒ በጻፈው ማስታወሻ ላይ ፣ "... በ17ኛው አንቀጽ አተረጓጐም ተንኮል እንዳለበት በንጉሡ ልብ ላይ ጥርጣሬ አድሮበታል" ካለ በኋላ ፣ "በዚህ ነገር የታመመ የከሳ ዐይኑ ጐድጉዶ የሚታየው ግራዝማች ዮሴፍ ነው " ሲል ጠቅሷል ።[1]

ጠቅላላው ሁኔታ ሲታይ ከዐሥር ዓመት በላይ ዮሴፍ ከአንቶኔሊ ጋር ሲተዋወቁ ፣ እነ አንቶኔሊ ለየመኳንንቱ ገጸ በረከት በማቅረብ አስተርጓሚውን ሁሉ በገንዘብ ስጦታ ሰበን የምኒልክን መንግሥት ቦርቡረን እንገባለን ብለው በተያያዙበት ሰዓት እንደ ሌላው ሁሉ ፣ ግራዝማች ዮሴፍ ልዩ ልዩ ስጦታ መቀበላቸውና ገንዘብ ችግር ባላቸው ወይም ጥሬ ብር በአማራቸው ጊዜ በብድርም በጉርሻም ሳይቀበሉ አልቀረም ። ብድር ብለው የተቀበሉትንም ፣ ጣሊያኖቹ እንደ ጉቦ ሆኖ ለመሳብ እንዲመቻቸው ሲሉ መልሰው አይቀበሉም ። ዮሴፍም ጐትጉተው አይሰጡም ይሆናል ። ይሁን እንጂ ፣ ግራዝማች ዮሴፍ በገንዘብ ተደልለው በክዳት መልክ የ17ኛው አንቀጽ ቃል እንዲገባ ያደረጉበት መንገድ አይታይም ።

በዚህም ላይ ፣ የፈረንሳይኛ ዕውቀታቸው በንግግር ላይ የተመሠረተ እንጂ ጠለቅ አድርገው በክፍል ያልተማሩት ይመስላል ። ለፈረንጆቹ በተለይም ስለማናቸውም ጉዳይ ደብዳቤ ሲጽፉ በአማርኛ ነው እንጂ በፈረንሳይኛ ሲጽፉ አልታየም ። ምናልባት ባለፈው ምዕራፍ በእርሳቸው አስተርጓሚነት ምኒልክና አንቶኔሊ በመጨረሻ ሲከራከሩ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ይህ 17ኛ አንቀጽ ቀድሞውንም እንዲያው ነውና የገባው አሁንም ይቅር ፤ ይኸውም ማለት ይሠረዝ" ሲሉ ግራዝማች ዮሴፍ ለአንቶኒሊ "qu'il reste" ብለው ተርጕመውለት ይሆናል ። ቃል በቃል "rester" የሚባለው ግሥ ፣ በአማርኛ መቅረትን ሲያሰማ በፈረንሳይ ይርጋን ያሰማል ። ይህ አተረጓጐም ይሆናል

1 C. Zaghi, Crispi e Menelich P. 258



ኮንት አንቶኔሊን ያስቆጣና ከመሳደብ ያደረሰው ። በግራዝማች ዮሴፍ በኩል ደግሞ ፣ አንቶኔሊን ከተዋወቁበት ጊዜ ዠምሮ ከልብ በወዳጅነት ሲያገለግሉት ኖረው ሳለ ፣ እርሳቸው ባማርኛ የጻፉትን "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከአውሮፓ ነገሥታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣልያ መንግሥት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል" የሚለውንና ንጉሠ ነገሥቱም የተቀበሉትን ቃል ወዳገሩ ቋንቋ ሲገለብጥ በተንኰልና በማጭበርበር ፣ "S. M. il re dei re d'Etiopia consente di Servirsi del governo di S. M. il re d'Italia" የሚለውን ቃል ጨምሮ ይኸንኑ መንግሥቱ ለየመንግሥታቱ በማስተላፍና ፣ "የኢትዮጵያ የበላይ ጠባቂ ሆነናል " በማሰኘት ፣ እኔን በንጉሠ ነገሥቴ ዘንድ አስወጋኝ የሚል ቅሬታ ሳይሰማቸው አልቀረም ።

ስለዚህ ፣ እነአንቶኔሊ ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ እንደ ተመለሱ አከታትለው ለአልቤርቶ ጆሴፒ ፒዛኒ አሁንም በአማርኛ አንድ የስሞታ ደብዳቤ ጽፈዋል ። ፒዛኒ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ለክሪስፒ የቅርብ ረዳትና የካቢኔ ዲሬክተር ሆኖ የሚያገለግል ከፍተኛ ባለሥልጣን ነበር ። ግራዝማች ዮሴፍ ከደብዳቤው ግንኙነት በቀር ሮማ ከራስ መኰንን ጋር የሔዱ ጊዜ የተዋወቁትና የተላመዱት ይመስላል ። የደብዳቤውን ቃል ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

> "...የተላከ ከግራዝማች ዮሴፍ ይድረስ ከካባሊዬሬ ፒሳኒ ደሲዬ እጅጉን እንዴት ነህ ። እኔ ከአንተ ከተለየሁ ከጤናዬ በቀር በሌላው የመንግሥት ጉዳይ ሁሉ በጦርነት ተቀምጫለሁ ። ይህ ሁሉ መሆኑ በኮንት አንቶኔሊ ሥራ የተነሣ ነው ። ኮንት አንቶኔሊን ካወቅኋቸው ከ14 ዓመት ይበልጣል ። ይህን ያህል ዓመት ስንኖር ከማገልገል በቀር ያሳዘንኋቸው ነገር ያለ አይመስለኝም ። ደግሞ ወዳጁን በማይታይ ጦር መግደል የጥሩ ሰው ሥራ አይደለም ። እውነተኛ ሰው ሲጣላ በጦር በጎራዴ ፣ በጠመንጃ ይጣላል እንጂ ወዳጁን በመርዝ አይገድልም ። ኮንት አንቶኔሊ ግን ፣ በተወለድሁበት አገር እንኳን አገልግዬ ለምኜ እንዳልበላ አድርገውኝ ሔዱ ። ከመንግሥት የመጣ ሰው ቢሆንም ባይሆንም ፊት ለፊት ተናግሮ የተገሰጠ ሥራ ሠርቶ ባገሩም በተላከበትም አገር ይመሰገን ዘንድ ያደርጋል እንጂ ፣ ንጉሠ ነገሥትን እስከ ሠራዊቱ ለማታለል የቄሶች ዘር መሆን ያስፈልጋል ።* የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዐጤ ምኒልክ የፈለጉት ከኢጣልያ መንግሥት ጋር የሚቀር ፍቅር ለማድረግ ነበር እንጂ ፣ ዐጤ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ጉዳያቸው ሲሞላ ወንድማቸውን ወደናንተ አይልኩም ነበር ። ነገር ግን ምስጋና ቢስ እሆናለሁ ብለው የኢጣልያ መንግሥት ፍቅር ለመጨረስ ፣ በቤተ መንግሥቱ ብዙ ትልልቅ ሰው ሞልቶ ሳለ የሚወዱትን ወንድማቸውን (ራስ መኰንንን) ልከው የኢጣልያን መንግሥት

* የካርዲናል ጃኮሞ አንቶኔሊ ተወላጅ መሆኑን አሹፈው ለመጥቀስ ነው ።

ማክበራቸውን ገለጡት እንጂ ዐጼ ዮሐንስ ሳሉ የችግራቸው ጊዜ ያለመኗችሁን (ያልጠየቋችሁን) ጥግነት ዛሬ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሲባሉ ምን ቢቸግራቸው የኢጣልያ መንግሥትን ጥግነት ይለምናሉ ። ነገር ግን 30 ምልዮን ነፍስ (ሕዝብ) ባለበት አገር አንድ መከሪ ይጠፉና በ31 ዓመት ሙሉ ደከማችሁ ከኢትዮጵያ ጋር ያደረጋችሁት ፍቅር ይፈርሳል አይመስለኝም ።”

ይኸን ካመለከቱ በኋላ ፣ በጠቅላላው በኮንት አንቶኔሊ ምክንያት የተበላሸው የኢትዮጵያና የኢጣልያ ግንኙነት ከሳሊምቤኒና ከትራቬርሲ ጋር ሆነው እንደገና እንደሚቃና ለመግለጥ ያላቸውን ምኞት በማውሳት ፤

“ላይረባ ይህ 17ኛ ክፍላችሁ (አንቀጽ) ነገሩን ሁሉ አበላሸብን ይህ ነገር (አንቀጽ) ባይኖር እኔና ኮንት ሳሊምቤኒ ብዙ ጉዳይ እንሞላ ነበር ። ደግሞ ሁሉን ነገር በደብዳቤ ዛሬ መጻፍ አይቻለኝም ። የኔንና የኮንት ሳሊምቤኒን ኑሮ የነገሩን መጨረሻ ከሐኪም ትራቬርሲ ታገኙታላችሁ ።[1] ” የሚል ቃል አስፍረዋል ።

በዚህ ዓይነት ፣ ትራቬርሲና ሳሊምቤኒ የበላያቸው ከሆነው ከአንቶኔሊ ጋር በከርከሩና አገር ለቆ በመሔዱ የተባበሩ ቢመስልም ፣ ከልባቸው የውጫሌውን ውል እንዳልተቀበሉትና ማጭበርበር እንዳለበት ተረድተው ይህ አንቀጽ ቀርቶ ከምኒልክ ጋር ያላቸው የቆየ ወዳጅነት እንዲረጋ ተመኝተዋል ማለት ነው ።

ነገር ግን ፣ በአንቶኔሊ ዐውቆ ማጭበርበር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ፣ “አንድ ጊዜ ለዘለቄታ በኢትዮጵያ ላይ የበላይ ጠባቂነትን ለኢጣልያ አስገኘሁ” ብሎ በምክር ቤቱ ፊት የፎከረበትና ለመንግሥታቱ ያስተላለፈበት ጉዳይ ስለሆነ ፣ የሁለቱ ባለሥልጣኖች ከግራዝማች ዮሴፍ ጋር መተባበር በምንም ዓይነት ሊጠቅም አልቻለም ። እነሱም በልባቸው የራሳቸውን መንግሥት እየታዘቡ ለእንጀራቸውና ለእድገታቸው ሲሉ ባላመኑበት ነገር ከአንቶኔሊ ጋር ተባብረዋል ማለት ነው ።

1 Archivio Storico dei Soppressi . . .(Etiopia) XV 1857 - 1895) ROMA.



# ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት

## ከነአንቶኔሊ መመለስ ወዲህ የኢጣልያኖች አያያዝ የራስ መንገሻና የዠኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ መስማማት

በኢጣልያ አገር ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ተሽሮ ማርኪዜ ዲሩዲኒ አንቶኒዎ * ስታራባ ተሾሞ ነበር ። እርሱም አጭር ጊዜ እንደሠራ ተሽሮ እ. ኤ. አ. ግንቦት 15 ቀን 1892 ዓ. ም. ጆዎቫኒ ጂዎሊቲ ጠቅላይ ሚኒስትር ፣ ብረ ቤኔዲቶ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ ። እነአንቶኔሊ ከተመለሱ ወዲህ የኢጣልያ ባለሥልጣኖችና በኤርትራ የሚገኙ ወኪሎቻቸው ፣ “ምኒልክ በፊት የሸዋ ንጉሥ የነበሩ ጊዜ ገራገር ፣ የዋህና ጣልያኖችን ወዳድ የነበሩት አሁን የንጉሠ ነገሥትነት ዘውድ ሲጭኑ ተለውጠው ጥብቅና ክፉ ሆኑ ። የቀድሞውን የኛን ወዳጅነት ትተው ፣ ጉዳያቸው ከተሟላና የጦር መሣሪያ ከሰበሰቡ በኋላ ፣ ከፈረንሳይና ከመስኮብ መንግሥታት ጋር ይወዳጁ ዠመር ። ይኸን ለማድረግ የሚገፉፉ የኛ ጠላቶች የሆኑትና አዲስ አበባ የሚቀመጡት የፈረንሳይ ፣ የስዊስና የመስኮብ ተወላጆች ናቸው” እያሉ ያሙ ዠመር ።

ዶክተር ትራቬርሲ ፣ “. . . ሁል ጊዜ የሸዋን ሐቀኝነት እጠራጠር ነበር ። ምኒልክ አሁን የፈለጉትን አግኝተዋል ። ለኛ የመልካውበት ሲል የሐበሻ ጠባይ የሚለወጥበት ምክንያት የለም ። በሚቹ ንጉሠ ነገሥትና ባሁኑ ንጉሠ ነገሥት መካከል ልዩነት የለም ። በመካከላቸው ያለው ልዩነት ያኛው ዮሐንስ ፣ ይኸኛው ምኒልክ በመባል የሥያሜ ልዩነት ብቻ ነው”[1] ሲል ጽፏል ።

በኢጣልያኖቹ ፊት የሁለቱም ነገሥታት ኃጢአት የኢትዮጵያን ወደብና አውራጃ ስንወር ፣ ወሰናችን እስከ መረብ ይድረስ ስንል ፣ ለምን ዝም ብለው አይመለከቱም፣ ለምንስ ይከራከራሉ ነው ። ባለሥልጣኖቹ ያን ጊዜ እርስ በርሳቸው የተጻጻፉበት ሰነድ ዛሬ ሲነበብ

* ሐረር የመጣው ዲሩዲኒ ዘመዱ ነው ።
1 Let - Marefia - L. Traversi, P. 386.

በነርሱ ዘንድ ፣ “እገሌ የሚባለው ራስ ወይም ደጃዝማች ኢጣል
ያንን ይወዳልን ”ብሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ያለውን አን
ዱን ወኪሉን ሲጠይቅ ፣ ወኪሉም አዎን ብሎ ሲመልስ ትርጓሜው
ይህ ራስ ወይም ደጃዝማች ኢጣልያ ከኢትዮጵያ አንዱን አውራጃ
ቆርሳ ብትወስድ ፣ መላውንም አገር ብትወር ዝም ይላል ፤ በዚህ የተ
ነሣ የኢጣልያ መንግሥት ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ቢዋጋ ወደኛ ዞሮ
ሊሰለፍ ይችላል የሚል የቂል ስሜት ነው ። እገሌ ጣልያንን አይወ
ድም ሲሉ አገሩን ብንወር ሊዋጋን ይችላል ነው ። በዚህ ዓይነት አገ
ሩን ከድቶ ለነርሱ የሚያደላውን ፣ ወሬ የሚያቀባብለውን ፣ “ብልህ ፣
ሥልጣኔ ወዳድ” እያሉ ሲያሞጋግሱ ፣ ያኛውን አገር አፍቃሪ ፣ “ግትር
(ፋናቲክ) ሞኝ” እያሉ ሲጠሉ ሲያጥላሉ ይታያሉ ። ነገሩን ሁሉ እንደ
ራሳቸው በመገመት ፈንታ የአፍሪካዊውን መልክ የሚመለከቱት
በተዋረደ ዓይነት ነው ። በነርሱ ዘንድ በዚያን ጊዜ ያገር አፍቃሪነት
ስሜቱም ፣ መብቱም የተሰጠው ለአውሮፓዊ ብቻ እንደሆነ አድር
ገው ነው የሚገምቱት ።

መቼም ሁሉም ቢሆን ፣ “ጥቁር ፣ አገርና የራሱ ነጻ መንግሥት
አይገባውም” ብሎ የመናቅ ፣ የነጭን ዘር የማኩራት ጉዳይ ነው እንጂ
ያለዚያ በንጹሕ ወዳጅነትና ባገር ጉዳይ ያለውን ግልጽ ልዩነት ሳያ
ውቁት ቀርተው አይደለም ። እነርሱ ራሳቸው በቅርብ ጊዜ ከአው
ስትሪያ የቄሣር ግዛት ተዋግተው ደማቸውን አፍስሰው ነጻነታቸውን
ያቋቋሙ ስለሆነ ፣ በነጻነትና በተራ ወዳጅነት መካከል ያለው ልዩነት
እስኪደናገራቸው ድረስ ይኸን ያህል ሞኞች አይደሉም ። ይኸውም
ሆኖ አገሩን ክዶ ለነርሱ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግላቸውን በልብ እየ
ታዘቡ ፣ አበክሮ የሚጠላቸውንና የሚዋጋቸውን ግን ፣ በልባቸው ማክ
በር የሚወዱ ከመካከላቸው እንደማይጠፉ የታወቀ ነው ።

በጠቅላላው አብዛኞቹ ኢጣልያኖቹ ግን ፣ በአውሮፓና በአፍሪካ
መካከል ያለውን ሁኔታ ሁሉ ባንድ ዓይነት አይመለከቱም ። ቢማርም
ባይማርም ፣ በጠባዩ ወይም በትምህርቱ ከነሱ የተሻለ የሞራል ከፍታ
ቢያሳይም ፣ ባያሳይም አፍሪካዊውን የሚመለከቱበት የዚህ ዘመን
ዐይናቸውና የሚመዝኑበት አእምሮአቸው ከአውሮፓዊው ጋር የተለ
ያየ ነው ። “አውሮፓዊው ለገዥነት የተመደበ አገሩን አፍቃሪ ፣ ጥቁር
ግን ላበላው ብቻ የሚሞት ፣ የነጻነትን ጣዕም ያላጣጣመ ፣ የወገን
ፍቅር የሌለው ነው” ብለው ያምናሉ ። ይኸ ከሆነ ደግሞ ያልሠለጠ
ነው አፍሪካዊ በሠለጠነው አውሮፓዊ መገዛት አለበት የሚሉና እም
ነታቸውን ሁሉ በዚህ መስመር ላይ ብቻ ያተኩሩ ናቸው ።



በተለይ ደግሞ ፣ ይህ ዘመን አውሮፓውያን ፣ አፍሪካን ተከፋፍለው
የሚገዙበት ጊዜ ነበር ። ከዚህም አልፎ የቤልዥክ ንጉሥ ፣ ዳግማዊ
ሊዎፖልድ ፣ ኮንጎን (ዛየርን) የሚያህል ታላቅ አገር ለግሉ ይዞና አቆይቶ፣
በኋላ እንደ ጉርሻ ሳገሩ ፣ ለቤልዥክ በስጦታ መልክ እ.ኤ.አ. በ1906
ዓ. ም እስኪያስተላልፈው ድረስ እንደግል ንብረት ይዞ በወኪሉ የሚ
ያስተዳድርበት ጊዜ ስለነበረ ፣ ጣልያኖቹም የኢትዮጵያን ነጻ መንግ
ሥትነት መቀበሉ ይቀፋቸው ነበር ። የነርሱው ተወላጅ የሆነው ፖላሚ
ንጊ የሚባለው ኢጣልያዊ ባዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የዚህን ጉዳይ
ሲያብራራ ፣ “የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታዊ
መንግሥት መኖሩን እንደማያውቅ ይመስል ነበር”[1] ሲል አመልክ
ቷል ። እውነትም ከዓድዋ ድል ወዲህ ኢጣልያኖች በጽሑፍም
በቃልም ምኒልክን ፣ “ንጉሠ ነገሥት እያሉ በውጫዊ መልክ ለማክ
በር ቢገደዱም ፣ እርስ በርሳቸው በሚጻጻፉበት ጊዜ አንዳንዶቹ ንቀታ
ቸውን አይሰውሩም ። ይህ አገር በሺ የሚቆጠር ዘመን ነጻነቱን ጠብቆ
የኖረ ፣ በታሪኩም ፣ በዠግንነቱም የሚኮራ ፣ በቅርቡ ባፄ ዮሐንስ ጊዜ
ግብጾችን ሁለት ጊዜ ተዋግቶ የመለሰና ነጻነቱን ያጠነከረ መሆኑ
በቅኝ አገር ምኞት የተሸፈነው አእምሮአቸው በትክክል ሊመለከ
ተው አይችልም ነበር ። ሊመለከቱ የሚችሉት ወገኖች በጣት የሚ
ቆጠሩ ናቸው ። እነሱም በዚህ ጊዜ ቢናገሩም ፣ ቢጽፉም አድማጭም
የላቸውም ። እንደ ከሐዲም እየተቆጠሩ በምክር ቤትም በጋዜጣም
ይዘለፉ ነበር ።

ስለዚህ ስለ ወሰኑም ፣ ስለ አንቀጹም አዲስ አበባ ላይ ገንዘባቸውን
ረጭተው ፣ አባብለውም ፣ አስፈራርተውም ጉዳዩ ሁልጊዜ ጥሬ በመ
ሆኑ ተስፋ ቆረጡ ። እነአንቶኔሊ ወደ አገራቸው እንደ ተመለሱ አስ
ቀድሞ ፣ “አንቀጹ ካልጸደቀ መንገሻና አሉላ ቢሸፍቱብዎት ፣ እንግሊ
ዞች ቢነሡብዎት መደገፍ አይቻለንም . . ,” እያሉ ያስፈራሩበትን
አሳብ እነርሱው ራሳቸው መሳፍንቱን በማሸፈት በሥራ ለመግለጽ
ተነሣሡ ። በነዚሁ ከኢትዮጵያ በተመለሱት ወኪሎችና በጠቅላይ
ሚኒስትሩ ተመርቶ የኢጣልያ ንጉሥ ኡምቤርቶ ባፄ ምኒልክ ላይ
ለማስነሣት ከመደባቸው ውስጥ ለዋናውና ለቀንደኛው ለራስ መን
ገሻ ፣ “ማናቸውንም የሚያስፈልግዎትን ነገር ምጥዋ ወዳለው የበላይ
ኃላፊያችን ቢልኩ ይከናወንልዎታል” የሚል ደብዳቤ በሰው እጅ
በመላክ ራስ መንገሻን ለማሸፈት መቀስቀስ ዠመረ ። እርሳቸውም
ያፄ ዮሐንስ አልጋ ወራሽነት ከልባቸው ስለ አልጠፋ ፣ ነገሩን በደስታ
ተቀብለው መልስ ሰጡ ።

1 Palamenghi. Crispi e Menelich, . . p. 307.

ይሁን እንጂ ፡ ዳግማዊ ምኒልክ ከነአንቶኔሊ ጋር በተጣሉ ጊዜ ጠቡን በማባባስ አራዝመው ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ፈጽሞ ላለመ ቆራረጥ ይጠነቀቁ እንደ ነበርና እንደዚሁም የኢጣልያ ንጉሥና ራስ መንገሻ በሚጻጻፉበት ጊዜ ፡ ውስጡን ልብ ለልብ እየተዋወቁ ወይም በመልክተኛ አማካይነት በምስጢር ግልጹን እየተነጋገሩ በጽሑፍ ላይ በሚያሰፍሩት ቃል ግን ፡ የኢጣልያ ንጉሥም ራስ መንገሻም እንደሚ ጠነቀቁ በየደብዳቤዎቹ ላይ ይታወቃል ።

በዚህ ምክንያት ፡ እነአንቶኔሊ በየካቲት ወር የስንብት ደብዳቤ ጽፈው ወዳገራቸው እንደ ተመለሱ ፡ ራስ መንገሻ ፡ ቀድሞ ምኒልክ ባፄ ዮሐንስና በኢጣሊያኖች ጠብ የተጠቀሙትን መጠን አሁን ደግሞ በፋንታቸው በምኒልክና በኢጣልያኖች ጠብ ለመጠቀም ሲሉ ፡ በሐምሌ ወር መዠመሪያ ላይ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ፡ ካፄ ምኒልክ ደብቀው ፡ ከኢጣልያ ንጉሥ ለመጣላቸው ደብዳቤ መልስ ሰጡ ።

በእግዚአብሔር ቸርነት በአገር ፈቃድ የነገሡ 1ኛ ኡምቤርቶ የኢጣልያን ንጉሥ . . . እኔ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ደህና ነኝ ። ባለፈው መልክታችሁ አንድ ነገር ከኔ ብትፈልጉ ምጽዋ ወዳለው ወደኔ ሹምና ጸሐፊ እመልከቱ ብላችሁ ጽፋችሁልኛል ። ልዑል ሆይ እኔ ከናንተ ፍቅር ለማድረግ ነው እንጂ ፡ ሌላ ነገር የምፈልገው የለኝም ። ፍቅራችሁንም ለዘለዓለማዊ ፍቅር እንድትሆን በልቤ ያለ ቅን አሳቤን በዚሁ ደብዳቤ እገልጽላችኋለሁ ። ነገር ግን እኔ የምፈልገው ፍቅራችን ለጊዜው ብቻ አይደለም ። ለትውልደ ትውልዳችን እንድትሆን ነው ። እንደ አሳቤ ሊሆንልኝም ተስፋ አለኝ ። ሐምሌ 6 ቀን 1882 ዓ.ም.

ለዚህ ደብዳቤ የኢጣልያ ንጉሥ እንደዚህ ሲል ይመልሳል ።

ራስ መንገሻ ፡ የንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ልጅ ጤና ይስጥልኝ ። የጻፉልኝ ደብዳቤ ደረሰኝ ። እጅግም ደስ አለኝ ። እኔም ደግሞ ከናንተ ጋር ወዳጅነት ለማድረግ ብዙ ምኞት አለኝ ። በኢትዮጵያ ሁሉ በዳግማዊ ምኒልክ የናንተ ንጉሠ ነገሥት ብዙ ተስፋ አለኝ ። ነገር ግን አሳቤና የናንተ አሳብ ይስማማ እንደሆነ ለመመርመርና ለማስረገጥ የኔ እሙን አሽከር ዶክተር ነራዚኒ ከወዳጃችሁ ከዶክተር ዴማርቲኖ ጋር ከናንተ ሊዋዋሉ እስድላችኋለሁ ። ሁሉንም ነገር እንደ አሳቤ ልትስማሙ ተስፋ አለኝ ። የበለጠ ነገር ግን ፡ ከጄኔራል ጋንዶልፊ የምጥዋ ገዥ ጋር አንድ ትልቅ ጉባኤ አድርጋችሁ እንድትገናኙ ለሁላችሁም የሚጠቅም ውል ተስማምታችሁ እንድትዋዋሉ ። ፍቅራችንም በሁለታችን ተጠብቃ ረዥም ዘመን እንድትኖር እግዜርን እለምናለሁ ። ተጻፈ በኢጣልያ መንግሥት ቤት 15 መስከረም 1891 (መስከረም 5 ቀን 1884 ዓ.ም.)

ፊ ፡ ኡምቤርቶ[1]

1 አቶ ገብረ ሚካኤል ጉርሙ ያጠናቀሩት በዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ክፍል ቁ. 324 ።



በዚህ ደብዳቤ ላይ የተጠቀሱት ፡ 1ኛ ኔራዚኒ የተባለው ዶክተር ቺዛሬ ኔራሲኒ የተባለው ነው ። ስለርሱ ጉዳይ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ስሙን ጠቅሰናል ። ተቀማጭነቱ በሐረር ሆኖ ራስ መኰንንንና የሐረርጌን ሁኔታ የሚሰልል ነው ። በዚያ በኩል የዘይላን ሁኔታ እያጠና ፡ ቢያስፈልግ ወደፊት በሐረር በኩል የጦር ግንባር ለመከፈት የሚያስችለውን መንገድ የሚመረምርና ራስ መኰንንም ካፄ ምኒልክ የሚለዩበትን መንገድ ሲያውጠነጥን የቆየ ነው ። አሁንም በመጨረሻ የራስ መኰንን ለከዳት አለመበገር ሲታወቅ ፡ ከሐረር ወደ ሮማ ከተመለሰ ወዲህ ራስ መንገሻን ካፄ ምኒልክ ለማስከዳት የታቀደውን ዓላማ ከፍጻሜ ለማድረስ ተመርጦ የመጣ ነው ።

2ኛው የርሱ ጓደኛ ደማርቲኖ (ዶክተር ደማርቲኖ አንጀሎ) በፊት በአውሳ ሆኖ ከመሐመድ እንፋሪ ዘንድ አራት ዓመታት ተቀምጦ ባላባቱን ለማስከዳት ብዙ ሠርቷል ። ቀጥሎ በአንቶኔሊ አላሳቢነት ከአሰብ ተዛውሮ ዓድዋ ላይ የኢጣልያ ወኪል ሆኖ በፊት ከንጉሠ ነገሥቱ ወኪል ከደጃች መሸሻ ወርቄ ፡ ቀጥሎ ከራስ መንገሻ ጋር ተዋውቆ በጣም የተለማመደና ከዚያም አልፎ በልዩ ልዩ ሰበብ የተወዳጀ ነው ። በኋላ ግን ፡ በሌተና አርቱሮ ሙላዚኒ ተለውጦ ወደ ኢጣልያ አገር ተመልሶ ነበር ። አሁን የኢጣልያ መንግሥትና የምኒልክ ወዳጅነት ወደ ጠብ ተለውጦ መንገሻን በምኒልክ ላይ ለማስነሣት በሚፈለግበት ጊዜ ደማርቲኖ ለራስ መንገሻ እንደግል ወዳጅ በመቆጠርና የትግሬዎቹን ጠባይ ያውቃል ተብሎ እንደ ኔራሲኒ ተመረጠ ። ራሳቸው ራስ መንገሻ ፡ "እሱ ይምጣልኝ" ብለው ቀደም አድርገው ጽፈው ነበር ። በሁለቱም ወገን የርሱ ምርጫ የተስማማ ሆኖዋል ። ለዚሁ የመለያየትና ምኒልክን የማዳከም ተግባር መመሪያ ተቀብሎ ወደ መቀሌ መጣ ።

ደማርቲኖና ኔራሲኒ ፡ ከኢጣልያ አገር መጥተው በስፍራው ካለው ከሙላዚኒ ጋር እ.ኤ.አ. ጥቅምት 20 ቀን 1891 ዓ. ም. (ጥቅምት 13 ቀን 1884 ዓ.ም.) ዓድዋ ላይ ተገናኙ ። በኅብረት ከተነጋገሩና ከተስማሙ በኋላ ፡ ወደ ራስ መንገሻ ሔደው እስከ መረብ ያለው የኢጣልያ ይዞታ እንዲጸና ፡ ስለ አከለ ጉዛይና ስለ ሠራዬ የወደፊት ሁኔታ ተወያይተው ስምምነት አደረጉ ። ይሁን እንጂ ፡ በዚያው በትግሬ የንጉሠ ነገሥቱ ያፄ ምኒልክ አንዳንድ ወዳጅና ወሬ አቀባይ እንደማይጠፉ በመገመት ፡ በተቻለ ሁኔታውን በዝርዝር እንዳይሰሙ ለማድረግና ቢሰሙም የራስ መንገሻና የኢጣልያኖች ግንኙነት ወዳጅነትንና ንግድን ለማስፋፋት ፡ የመልካም ጉርብትና ግንኙነት እንዲመስል ይጣጣሩ ነበር ። ወሬውን ቢሰሙና ደብዳቤው ቢገኝም ፡ ዐፄ ምኒልክን የሚያስቆጣ እንዳይሆን ራስ መንገሻ ፡ "ከወዳጅነት በቀር

ምንም አልፈልግም" የሚል ዐረፍተ ነገር በማከል ፡ የኢጣልያ ንጉሥም "ከዳግማዊ ምኒልክ ከናንተ ንጉሠ ነገሥት ጋር ወዳጅነት ለማድረግ ተስፋ አለኝ" በሚል አነጋገር ለመሸፋፈን ሞክረዋል ።

እነዚሁ የፖለቲካ ሰዎች ወዲያና ወዲህ ብለው ከራስ መንገሻ ጋር ተስማምተው ሲጨርሱ ፡ በመጨረሻ ምጥዋ የሚቀመጠው ዋናው አገረ ገዥ ጄኔራል ዦሴፔ ጋንዶልፊና ራስ መንገሻ በንጉሥ ኡምቤርቶ ደብዳቤ ላይ እንደ ተጠቀሰው ተገናኝተው እንዲዋዋሉ አደረጉ ። ግንኙነቱ በመጀመሪያ የታሰበው ዓድዋ ላይ ነበር ። በኋላ ግን ፡ ባንድ ወገን ምስጢሩ እንዲጠበቅ ፡ በሌላም ወገን ጄኔራል ጋንዶልፊ ከመረብ ወንዝ እጠገብ እዲ ኳላ እጠገብ እንዲሆንለት ስለጠየቀ ፡ ራስ መንገሻ በራስ አሉላም በሌሎቹም መኳንንትና ሠራዊት ታጅበው ወደ መረብ ሔዱ ። በዚያም ሁለቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በወዳጅነት መልክ ተገናኝተው አሳባቸውን ከተለዋወጡ በኋላ ፡ ከዚያው ላይ እንደ ዘለዓለማዊ የኢጣልያኖች ጠላት ይቆጠሩ የነበሩት ራስ አሉላ በራስ መንገሻ አማካይነት ከጄኔራሉ ጋር እጅ ለእጅ ተጨባብጠው በኢጣልያኖችና በነራስ መንገሻ መካከል ጠቡ ቆሞ ፍቅር መተካቱ ተነገረ ።[1]

ቀጥሎ ወንጌልና መስቀል ቀርቦ ፡ ራስ መንገሻና ጄኔራል ጋንዶልፊ ከዚህ እንደሚከተለው በመሐላ ስምምነት አደረጉ ።

1ኛ ራስ መንገሻን የሚጠላ ለኢጣልያ መንግሥት ጠላቱ ነው ። ራስ መንገሻን የሚወድ ወዳጅ ነው ። የኢጣልያ መንግሥት ራስ መንገሻን ይወደዋል ፤ ያከብረዋል ። የኢትዮጵያም ንጉሥ ልጅ እንደ መሆኑም ያውቀዋል ። ራስ መንገሻን የሚያሳዝን ትንሽ ነገር በኝኳ ምንም ነገር እንዳያደርግ ምኗል ።

2ኛ የኢጣልያን መንግሥት የሚጠላ ለራስ መንገሻ ጠላት ነው ። የኢጣልያን መንግሥት የሚወድ ወዳጅ ነው ። ራስ መንገሻ የኢጣልያ መንግሥት ይወደዋልና ያከብረዋል ። ኅዳር 29 ቀን 1884 ዓ. ም.[2]

የራስ አሉላ መሐላ ፡ ከሌሎች መኳንንት ለየት ይላል ። የቀሩት ለኢጣሊያ ወዳጅነታቸውን በመሐላ ሲያጸኑ ፡ የእርሳቸው አማማል ግን ፡ "ለራስ መንገሻ ታማኝ አገልጋይ ነኝ" ብቻ የሚል ነው ይባላል ። መሐላው የተደረገው ጋንዶልፊ ለራስ መንገሻ ፡ ራስ መንገሻ ለኢጣልያ ንጉሥ ለኡምቤርቶ በመጻፍ በደብዳቤ መልክ ነው ። ውሉን በተለይ ወዲያና ወዲህ እያለ እንዲከናወን ያደረገው እላይ

1 Italia ed Etiopia p. 62, No. 1.
2 Storia Diplomatica . . .Rossetti PP. 108 -111



እንዳልነው ፡ ከሮማ ከንጉሡ ዘንድ ለራስ መንገሻ ደብዳቤ ይዞ የመጣው ቼዛሬ ኔራሲኒ ነው ።[1]

የስምምነቱ ዓይነት ፡ ምንም ባይገለጽ ዘወር ባለ አባባል በንጉሠ ነገሥቱ በዳግማዊ ምኒልክ ላይ መሆኑ ለማንም የተሰወረ ሊሆን አይችልም ። ደንበኛው ትርጉም ኢጣልያ ከምኒልክ አሁን እንደ ተጀመረው ቢጣሉ ፡ መንገሻ ከኢጣልያኖች ጋር ሆነው ከምኒልክ መጣላት አለባቸው ። መንገሻም ከምኒልክ ጋር ቢጣሉ በኢጣልያኖቹ በኩል የሚደረገው ይኸው ነው ። እንዲያውም ኢጣልያኖቹ ከምኒልክ ተጣልተው መንገሻ ከሚደረቡ ፡ መንገሻ ከምኒልክ ቢጣሉና ቢዋጉ መንገሻን በመደገፍ ኢጣልያኖቹ ከምኒልክ ጋር መዋጋትን ይመርጣሉ። የኢጣልያ መንግሥት ምኞትና የውሉም መሠረተ ሐሳብ ይኸው ነው። በተረፈ ኔራሲኒ በጽሑፍ ይዞ በመጣው መመሪያ መሠረት ፡

1ኛ ለእከለ ጉዛይና ሠራዬ አስተዳዳሪዎቹ የሚሾሙት በራስ መንገሻና በምጥዋው ገዥ ስምምነት እንዲሆን ፡

2ኛ እነዚህ ሁለቱ አውራጃዎች በውስጥ አስተዳደር ነጻ ሆነው ግብር ለኢጣልያም ለኢትዮጵያም እንዳይከፍሉ ፤

3ኛ በሁለቱ አውራጃዎች ሹማምንት ዘንድ ተቀማጭ የሚሆኑ የጦር መሣሪያ የያዙ የኢጣልያ ሹማምንትን ለመሾም የኢጣልያ መንግሥት መብቱ እንዲታወቅለት ፡

4ኛ በሁለቱ አውራጃዎች ላይ ምንም ዓይነት ዘረፋ እንዳይደረግ የሚል ነው ።[2]

ከዚህ ሁሉ ስምምነት በኋላ ፡ ራሳቸው ራስ ሆነው የንጉሥነት ማዕረግ ሳያገኙ ውሉን ተዋውለው ከጨረሱ በኋላ ፡ ራስ መንገሻ ለጄኔራል ጋንዶልፊ የራስነት ማዕረግ ለዶክተር ኔራሲኒ የቀኛዝማችነት ማዕረግ ከልዩ የኒሻን ሽልማት ጋር ስለሰጡ ፡ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ መሸፈታቸውን ራሳቸው አስታወቁ ማለት ነው ። ይኸንንም አድርገው ከተለያዩ በኋላ ፡ ከመረብ ወዲያ ከአሥመራ ወዲህ በሁለቱ መካከል ከንጉሠ ነገሥቱ ተሹመው የነበሩትን ደጃዝማች መሸሻ ወርቄን ሁለቱም ወገኖች ጠብ እየቀሰቀሱ አላስቀምጥ አሉዋቸው ። በፊተኛው ጊዜ ከወዲህ የራስ መንገሻ ሰዎች ባስቸገሯቸው ጊዜ ወደ አሥመራ ሲሔዱ ፡ የአሥመራ ገዥዎች እነጄኔራል ባልዲሠራ፡ እነጄኔራል አሬሮ እንከባክበው ያስቀምጧቸው ነበር ። አሁን ጄኔራል

1 Crispi e Menelich . . ,P. 293. No. 8
2 Ibid.

ጋንዶልፊ ከራስ መንገሻ ጋር ከተስማማ ወዲህ ፣ ስንቅ ለራሳቸውም
ለሰዎቻቸውም ካገር ላይ እንዳያገኙ በማድረግ እየከለከለና ፊት እየነሣ ፣
"ሰዎችህ አገር አጠፉ ያንተ ጭፍሮች ባላገር ዘረፉ" በማለት እያወ
ገዘ ፣ በመጨረሻ እንዲያውም ፣ "ግዛቴን ለቀህ ውጣ " ብሎ የጦር
መሣሪያቸውን ቀምቶ አስወጣቸው ።[1] በፊት አንከባከበው ይዘዋቸው
የነበሩት ራስ መንገሻም ፣ ተመሳሳይ እርምጃ በመሸሻ ላይ ስለወ
ሰዱ ፣ መሸሻ ሁሉንም ትተው ወደ አዲስ አበባ ፣ ወደ ንጉሠ ነገሥቱ
ተመልሰው የሚያውቁትን ሁሉ በዝርዝር ገለጹ ።

ራስ መንገሻ ፣ ራስ አሉላን ፣ ራስ ሐጎስንና የአክሱሙን እጨጌ
ቴዎፍሎስን ይዘው በስብሰባ ምክር እየተደረገ ለሸዋ ያደላሉ የሚባ
ሉትን እነፊታውራሪ ለውጤን እያገለሉ ለቀረው ሹመት ሽልማት
ይሰጡ ገሠመር ። ምናልባት ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ትግሬ መዝመታቸው
አይቀርም በሚል ሥጋት ካሁኑ ጀምሮ የወታደር ድርጅት ያደርጉ
ገሠመር ። ለዚህም ከጄኔራል ጋንዶልፊ 35,000 ጥይት ተቀበሉ ። የአ
ጋሜው ደጃዝማች ስብሐት ከራስ መንገሻ ጠበኛ ሆነው በአሁኑ
ጊዜ ከኢጣልያኖች ጋር ነበሩ ። በኢጣልያኖች አሳሳቢነትና በአ
ማቻቸው በራስ አሉላ አማካይነትም ተላልከው ገብተው ፣ ድንጋይ
ተሸከመው ራስ መንገሻን ላለፈው ጥፋታቸው ምሕረት ጠይቀው
በመሐላ ታረቁ ። ራስ መንገሻም ለርሳቸው የራስነት ማዕረግ ፣ ለልጃ
ቸው ለደስታ የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጧቸው ። ራስ መንገሻም በዚህ
ጊዜ ወዲያና ወዲህ ሲሉ ልክ እንደ ንጉሥ ቀይ ጃንጥላ ያስይዙ ገሠመር ።
ሐውዜን ላይም ታላቅ ስብሰባ አድርገው ለመንገሥ ማሰባቸውንና
ካፄ ምኒልክ መከዳታቸውን የሚገልጽ ዲስኩር ለሕዝቡ በይፋ ተናገሩ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ዋና ባላንጣቸው የነበሩት ደጃች ደብብ አርአያ ፣ በራስ
መንገሻ ትእዛዝ አምባ ስላማ ላይ ታስረው ይኖሩ ነበርና ከዚያ አም
ልጠው ወንድማቸውን ደጃች ቦጋለን ይዘው ዱሃ ላይ ከራስ መንገሻና
ከራስ አሉላ ጦር ጋር ተዋግተው በጦርነቱ ሲሞቱ መላው ትግሬ
በራስ መንገሻ ሥር ይነስ ይብዛ ተጠቀለለ ። የእንደርታዎቹም እነደጃች
ተድላ ዋህድ ገቡላቸው ። ይኸም ሳይበቃ ቀርቶ ወጣቱ ደጃች ውብ
ነህ የራስ ሐጎስ የልጅ ልጅ ፣ ከአያቱ ከራስ ሐጎስ ግዛት ከጸለምት
ጦር እያሳበረ የራስ ወሌ ግዛት የሆነውን ሰሜንና ወገራን ፣ የሸሬው
ደጃች አብርሃ ደግሞ ፣ ከራስ ወሌ ሹሞች ከነደጃች ወርቅነህ ጋር በራስ
መንገሻ ስም እየተዋጉ በወልቃይትና በጸገዴ በኩል ግዛት ያስፋፉ
ገሠመር ።

1 Archivio Stroico (Etiopia) XV 1857 - 1895 (Roma)



በዚህ ዓይነት ራስ መንገሻ ፣ ያፄ ዮሐንስን ዙፋን በኢጣልያኖቹ
እርዳታ ከፀፄ ምኒልክ ላይ መልሰው ለመውሰድ እንደ ቀረቡ ተማመኑ።
በበኩላቸው ኢጣልያኖቹ ደግሞ የኤርትራ የቅኝ ግዛት ወሰናቸው
ከምጥዋ ዝምሮ እስከ መረብ ወንዝ እንዲደርስ የተመኙትንና ምኒ
ልክ በልመና እምቢ ያሉትን ፣ መንገሻን ከምኒልክ በማሸፈት በቀ
ላሉ እንደሚያገኙት ብቻ ሳይሆን ወደፊትም በሰሜን ኢትዮጵያ እንደ
ልባ ለመስፋፋት እንደሚችሉ ቆጠሩት ።

በ1884 ዓ. ም. ላይ መንገሻና ጋንዶልፊ መረብ ላይ ከመዋዋ
ላቸው በፊት ቀደም ባሉት ወራት በንጉሥ ኡምቤርቶና በራስ መንገሻ
መካከል የወዳጅነት ግንኙነት ፣ የስጦታው ልውውጥ ለጊዜው እየተ
ሟሟቀ ሔዶ ነበር ። ራስ መንገሻ ከደጃች ደብብ ጋር ተዋግተው
የገደሉበትን ሰበብ የኢጣልያን ወዳጅነት ለመጠበቅ መሆኑን ገልጸው ፤

> ደጃች ደብብ ኢጣልያኖች ወዳጆቼ ናቸውና ውደዱልኝ ብዬ ብላ
> ቸው እንቢ ብለው ስጓዝ ካንገት (መዋጊያ በር ይዘው) ላይ ቆይ
> ተው ተሰልፈው ተዋጉኝ በእግዚአብሔር ቸርነት በእምነ ጽዮን አማ
> ላጅነት በርስዎ ጸሎት ድል አደረግኋቸው እርሳቸውም ሞቱ . . . .

የሚል የምሥራች ደብዳቤ ለኢጣሊያ ንጉሥ ጻፉ ።

ይኸን ደብዳቤ ከጻፉበት ከመስከረም 13 ቀን 1884 ዓ.ም. ቀደም ብሎ፣

> ይድረስ ኀበ ዓቢይ ወክቡር ንጉሥ ኡበርቶ (ኡምቤርቶ) . . . ገጸ
> በረከት ያባቴ የጃንሆይ (ያጼ ዮሐንስ) የነበረ የወርቅ ኮርቻ ለፍቅር
> ምልክት እንዲሆን ሰድጄልዎታለሁ . . .[1]

ከሚል ደብዳቤ ጋር የወርቁን ኮርቻ በመላክ ወዳጅነታቸውን ለማ
ጠንከከር ጥረት ማድረጋቸው ይታያል ።

ይሁን እንጂ ፣ ወደፊት ያሉት ምዕራፎች እንደሚያስረዱን ፣ በምኒ
ልክና በአማካሪዎቻቸው የፖለቲካ ዘዴ ፣ በጦር ኃይላቸው ብዛት ፣
በመንግሥታዊ ድርጅታቸው ክብደት የመንገሻ ምኞት ሳይሳካ ይቀራል።
ኢጣልያኖቹ ራስ መንገሻን ከድተው እንደገና ወደ ምኒልክ ተለጥፈው
ምኞታቸውን ከግብ ለማድረስ ይፈትናሉ ። ራስ መንገሻ የኢጣልያኖቹ
ክደት ገርሟቸው ካፄ ምኒልክ ምሕረት ጠይቀው ከታረቁና ግዛታቸውን
ካስመረቁ በኋላ ከኢጣልያኖቹ ጋር ይዋጋሉ ። የሁለቱም ውጊያ ተከታ
ትሎ መጨረሻው ዓድዋ ጦርነት ላይ ይወድቃል ።

1 Archivio Storico (Etiopia) XV 1857 - 1895 (Roma)



ባዬ ምኒልክ ላይ ከራስ መንገሻ ጋር በመረብ የተዋዋለው ጄኔራል ጋንዶልፊ

ሊ.ኢ.ታሊያ ኢን አፍሪካ

# ምዕራፍ ዐሥራ አራት

## የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ለማለያየት የተደረገ የፖለቲካ ዘዴ ኢጣልያኖች መንገሻን ከድተው ወደ ምኒልክ እንደዞሩ

ንጉሠ ነገሥቱ ከመዠመሪያው ወቅት ላይ ፣ የራስ መንገሻን ክዳት በትክክል አያውቁም ነበር ። ነገር ግን የኢጣልያ ወኪል አንቶኔሊ ፣ "...ከእንግዲህ ወዲህ ከናንተ ጋር ጦርነት እንጂ ሰላም የለም" ብሎ ፎክሮ ከሔደ በኋላ ፣ እንደ ራስ መንገሻ ያሉትን ለማስነሣት እንደማ ይመለስ ያውቃሉ ። ራስ መንገሻም ፣ "እኔን ደግፉኝና እስከ መረብ ድረስ ያለውን ግዛትልፍቀድላችሁ ብለው አጎታቸውን ግራዝማች ሳዶርን ልከውብን እኛ ሳንቀበላቸው ቀረን" ብለው ኢጣልያኖቹ ከዚህ በፊት የተናገሩትን ላይጠራጠሩት ይችላሉ ። ራስ መንገሻን በመጠርጠርና በማመን መካከል ሆነው ለማናቸውም ወደ ወሎ ብቅ ብለው ሁኔታውን ለመጠባበቅ ምኒልክ ቦሩ ሜዳ ላይ ሰፍረው ነበር ።

የአካሔዳቸውም ዓላማ ፣ የራስ መንገሻን ክዳት አምነውም ይሁን ሳያምኑ ፣ ቦሩ ሜዳ ድረስ ራስ መንገሻን ጠርተው ፣ በልዩ ልዩ ሽልማት አስደስተውና የትግሬን ግዛት በሙሉ ሰጥተው ከኢጣልያኖች ደባ እንዲጠበቁ ለማድረግ ነበር ። በዚህ ምክንያት ከአዲስ አበባ ሔደው ቦሩ ሜዳ ከደረሱ ዠምሮ ራስ መንገሻ ይመጣሉ ተብሎ ሽልማቱ ሲዘጋጅ ድግሱ ሲደገስ ሰነበተ ። በዚህም ጊዜ ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ልጅ ወይዘሮ ሸዋረጋ አብረው ነበሩ ። በሰው ሁሉ ዘንድ ፣ "ልጃቸውን ድረው ራስ መንገሻን ስማቸውን ገብረ መስቀል አሰኝተው በትግሬ ሊያነግሧቸው ነው "ተብሎ ተወራ ። ይሁን እንጂ ፣ ቦሩ ሜዳ ድረስ እንዲመጡ ተልኮባቸው ሳለ ፣ በየምክንያቱ ከዘገዩ በኋላ በመጨረሻ የከዳታቸው ወሬ በይፋ እየተወራ ሔዶ በንጉሠ ነገሥቱ ዘንድ ለመታመን ቻለ ።

በዚህ ጊዜ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱና ከእቴጌ ጣይቱ ጋር አቡነ ማቴዎስ ፣ እጨጌ ገብረ ሥላሴ ፣ ራስ ሚካኤል ፡ ራስ ወሌ ፣ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስ ፣ ደጃች ወልደ ገብርኤል አባ ሰይጣን ፣ ደጃች ገርማሜና ሌሎችም አብረው በቦሩ ሜዳ ነበሩ ። ከራስ መንገሻ ግዛት ጋር

ከሚወሰኑትና ጠበኛ ከሆኑት ከነዋግሹም ብሩ ፥ ከእንደርታው ከነደጃች ተድላ ዋህድ ዘንድ ፥ "ራስ መንገሻ ከኢጣልያኖች ጋር ተማምለው ከድተዋልና አይመጡም" የሚሉ ወሬ ሲነፍስ ቆይቶ ነበር ። አንዳንዶቹ ደግሞ ፥ "የመጡ እንደሆነ ይታሰራሉ" እያሉ ወደ ራስ መንገሻ በሐቅም ፥ በተንኮልም ይልኩባቸው ነበር ይባላል ። ዐፄ ምኒልክም በራስ መንገሻና በዋግሹም ብሩ መካከል ያለውን ጠብ ያውቃሉና ወሬውን በሙሉ ለመቀበል አጠራጥሯቸው ነበር ።

ስለዚህ ፥ ዐፄ ምኒልክ የሰሙትን እንዳልሰሙ እየመሰሉ ፥ ከዳታቸውን ለሚነግሯቸውም "እያደርገውም" እያሉ ብዙ ቀን ሲጠባበቁ ቆይተው ፥ በመጨረሻ የራስ መንገሻ በተባለው ቀን አለመግባት ከተወራው ወሬ ጋር ስለ ገጠመ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ ዝርዝሩን ጉዳይ ከትግሬ ተባረው ከመጡት ከደጃች መሸሻ ወርቄና ከሌላውም ካዳመጡ በኋላ በነገሩ አዝነው ለራስ መንገሻና ለትግሬ መኳንንት የተዘጋጀውን ሸልማት ለራስ ሚካኤልና ለወሎ መኳንንት ሸልመው ፥ ግብሩንም አብልተው እንዳበቁ ፥ ብዙ መኳንንት "አሁኑኑ ጉዟችንን ቀጥለን ወደ ትግሬ እንዝመት" ብለው ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱም አሳቡን ለጊዜው ተቀብለው ፥ ራስ መኰንንም ከሐረር ወደ ወሎ ሠራዊታቸውን ይዘው እንዲመጡ መልእክት ሔዶ ነበር ።

ነገር ግን ዳግማዊ ምኒልክ ፥ ማናቸውም የሰላም መንገድ ሳይሞከር ፥ ማናቸውም የፖለቲካ ዘዴ ሳይሠራበት በችኰላ ነገር ማባባስ ፥ ሁከት ማስነሣትና ሊድን የሚችለውን ችግር አጋንነው የጦርነት ውሳኔ ማድረግ እንደማይወዱ ባለፈው አመልክተናል ። "ራስ መንገሻ መረብ ወንዝ ላይ ከጄኔራል ጋንዶልፊ ጋር በርስዎ ላይ ተዋዋሉ ፥ ለጄኔራሉና ለደጃች ስብሐት የራስነት ማዕረግ ሰጡ ። ሐውዜን ላይ የትግሬን ሕዝብ ሰብስበው ለመንገሥ ማሰባቸውን አስታወቁ ። እንጂ ንጉሥ ቀይ ጃንጥላ አሲዘው ወዲያና ወዲህ ይላሉ" የሚባለውን ወሬ ሰምተው ። ምንም በልባቸው ቢናደዱ ፥ ንዴታቸውን በትእግሥት ውጠው ታላቅ ስብሰባ ተደረገና ፥ "አሁን ሠራዊቱም ስለሚራብ ፥ ያለፈውም በሽታና ረኃብ ገና ከአገር ላይ ስለ አልተወገደ ወደ አዲስ አበባ ሔደን ትንሽ ዐርፈን በአዲስ ኃይል ተዘጋጅተን እንደገና መመለሱ ይሻላል" ተብሎ በምክር ተወሰነ ።

ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ በሚዘጋጁበት ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱን ልጅ ወይዘሮ ሸዋረጋን ፥ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ሆነው ሁልጊዜ የሚያዩዋቸው ራስ ሚካኤል "ላግባ" ብለው አማላጅ እቴጌ ጣይቱን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ላኩ ። ንጉሠ ነገሥቱም ፥ "ሚካኤልን እንደ ልጅ ነውና የማየው ልጄን ለወዳጄ ፥ ለልጄ እንደምን እሰጣለሁ ፥



ከሆነም አሁን ሁዳዬ ነውና አዲስ አበባ ገብተን ከተፈሰከ በኋላ መጥቶ ይውሰዳት" ሲሉ ተግደረደሩ ። ራስ ሚካኤል ግን ፥ ካሁን ዠምሮ ሚስቴ ናትና ትሰጠኝ ብለው ጥያቄያቸውን ስለአጸኑ ልመናቸውም በእቴጌ ጣይቱ ስለተደገፈ ፥ እዚያው ደሴ ላይ በጥር ወር 1884 ዓ. ም. ሠርጉ ተደግሶ አጋቡዋቸውና ንጉሠ ነገሥቱ ከነሠራዊታቸው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ። ሲመለሱም ፥ "መቼም እንደገና ወደ ትግሬ መዘመቱ የማይቀር ይሆናል ብለው በመገመት የያዙትን መድፍ አህያ ፈጅ ላይ ትተውት መጡ ። አዲስ አበባ እንደገቡ የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ለማለያየት የሚችሉበትን ዘዴና መንገድ አጥብቀው ይፈልጉ ዠመር ። በዚሁ ጐን ጦር የመሰብሰቡም ጉዳይ አልተዘነጋም ።

ንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተመለሱ ፥ ኢጣልያኖች ውል እያፈረሱ ከአሥመራ አልፈው እስከ መረብ ያለውን አገር መውረራቸው ፥ በቤተ መንግሥቱ ያልታሰበውን የውጫሌ ውል ልዩ ትርጒም እየሰጡ ፥ ጠባቂ እንሁን ማለታቸው ፥ አሁን ደግሞ ራስ መንገሻን ማስከዳታቸው እየተጠቀሰ የኢጣልያኖች ተንኮል ፥ የራስ መንገሻ ከዳት ፥ በሁሉም ዘንድ በርክቶ እየተወራ ቁጭትንና ንዴትን አሳደረ ። በዚህም ጊዜ አዲስ አበባ ያሉት ፈረንሳዮቹም ፥ አርመኖቹም ፥ ግሪኩና ስዊሱ ሁሉ ፥ "የኢጣልያንን ተንኮል ቀድሞም ተናግረናል" እያሉ ራሳቸው በመቆጨት ኢትዮጵያውያኑንም ያስቆጯቸው ነበር ይባላል ።

ባለፈው ዓመት ፥ ከነአንቶኔሊ ጋር ወደ ኢጣልያ ለመመለስ ተሰናብቶ የነበረው ዶክተር ትራቬርሲ እነአንቶኔሊ ያበላሹትን የወዳጅነት ፖለቲካ እንዲያቃና እንደገና ተመልሶ መጥቶ በዚህ ጊዜ አዲስ አበባ ነበር ። ወደ ደሴም ፥ ወደ ሐረርም ፥ ወደ እንጦጦም እየተመላለሰ ፥ "ራስ መንገሻና ጄኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ የተስማሙት ሁለቱም የኢጣልያና የኢትዮጵያ ነገሥታት ወኪሎች እንደ መሆናቸው መጠን በስምምነት የየክፍል አገራቸውን በሰላም ለማስተዳደር እንዲመች ነው እንጂ ፥ የኢጣልያ መንግሥት ራስ መንገሻን ከግርማዊነትም አስከድቶ ለመስማማት በፍጹም አሳብም ምኞትም የለውም" እያለ ንዴታቸውንም ፥ ሐዘናቸውንም ለማረጋጋት ሞከረ ። እነራስ መኰንንም ፥ "ይኸ ከሆነ የንጉሥነት ማዕረግ ከሌለው ከራሱ ከራስ መንገሻ የራስነት ማዕረግና ኒሻን የናንተ ጄኔራል ጋንዶልፊ እንደ ምን ተቀበለ? ራሱስ ማዕረጉ ራስ ሆኖ እንድምን የራስነት ማዕረግ ለነራስ ስብሐት ይሰጣል?" እያሉ ተከራከሩት ። ፈረንሳዮቹ እነ ሙሴ ሸፍነ ፥ እነ ሙሴ ሞንዶን ፥ ዋናው አማካሪያቸው ሙሴ ኢልግ ከፈረንሳይ 'ለታ' እና 'ሲዬክል' ከሚባሉ ጋዜጦችና በኢጣልያ አገር ከሚታተሙት ጋዜጦች በራስ መንገሻና በጋንዶልፊ መካከል የተደ

ረገውን የውሉን ግልባጭና የተሰጠውን ሐተታ ፣ በኢጣልያ የባሕር
መዝገብ በደንብ ከተመዘገበው ላይ እየቀዱ እያመጡ ፣ የመረቡን የቃል
መሐላ ስምምነት ቃሉንም ፣ መንፈሱንም አሳዩ ። በቃልም ጉዳዩን
የኢጣልያ መንግሥት መቀበሉን እያስረዱ የትራቬርሲን አባባል ያስ
ተባብሉ ዠመር ።[1]

በዚህ መካከል ፣ ቀድሞ ከነበረው የወረርሽኝ በሽታ ያገገመውን
ሕዝብ እንደገና ከወደ ጅቡቲ የመጣ አዲስ በሽታ 'ኮሌራ' ተነሥቶ
ብዙ ሰው ፈጀ ። ንጉሠ ነገሥቱም ከዚሁ በሽታ ለመከለል አንኮበር
ሔደው በሽታው ከበረደ በኋላ ፣ በመስከረም ወር 1885 ዓ .ም. ተመል
ሰው አዲስ አበባ መጡ ። ቀጥሎ ባዲስ አበባ ትልቅ ቃጠሎ ተነሥቶ
የንጉሠ ነገሥቱ እልፍኝ ሳይቀር በመቃጠሉ አንድ ዓይነት ሐዘን
ባገር ላይ ጥሎ ነበር ።

በተለይ ደግሞ ዐፄ ምኒልክ የሠጉት ፣ ራስ መኰንን ከኢጣልያ አገር
ገዝተው ያመጡት 2 ሚሊዮን ጥይት በአሰብ በኢጣልያኖቹ እጅ እን
ደተያዘ ነበርና አሁን ኢጣልያኖቹ ከራስ መንገሻ ጋር በተስማሙበት
ሰዓት እንደዚህ ቁጥሩ የበረከተው ጥይት እንዳይቀርባቸው ነው ።
ባሁኑ ሰዓት አሳባቸው በጥብቅ ያተኮረው ኢጣልያኖችን እንዳልጠሉ
በመምሰል ፣ በፖለቲካ ዘዴ ኢጣልያኖቹንና ራስ መንገሻን ከማለያየቱ
ላይ ነው ። ለዚህ ጉዳይ ዋና መሣሪያ ይሆነኛል ብለው የመደቡት የመ
ረቡ ስምምነት ውሸት ነው እያለ ለማስተባበል የሚሞክረውን ራሱን
ሊዎፖልድ ትራቬርሲን ነው ። እርሳቸውም የሚያምኑትን በልባቸው
ይዘው ፣ በእንደበታቸው እኔም የኢጣልያ ንጉሥ ይኸን የመሰለውን
ተንኮል ያደርገዋል ብዬ አልጠረጥርም እያሉ የርሱን አባባል ለማጽ
ደቅ ይሞክሩ ነበር ። ይኸውም ዓይነቱ አነጋገራቸው ባንድ ወገን
ለፖለቲካ እርምጃቸው መሣሪያ ሲሆን ፣ ትራቬርሲንም መንገሻን
ከኢጣልያ ለመለየት ይገፋፋዋል ፣ ወይም ይረዳዋል በሚል መንፈስ
ነው ።

ስለዚህ ፣ አንድ ደብዳቤ ለኢጣልያ ንጉሥ በተለመደ አነጋገራ
ቸው ሰላም ፈላጊነታቸውን ፣ ወዳጅነት አጥባቂነታቸውን የሚገልጥ
አዘጋጅተው ከጨረሱ በኋላ ዶክተር ትራቬርሲ ወደ ግቢ ተጠራ ።
ወደ እልፍኝም ገብቶ የአክብሮት ሰላምታውን አቅርቦ ከተጨባበጡ
በኋላ ፣

"ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ወዳጅነታችን በዳግማዊ ቪክቶር አማ
ኑኤል ዠምሮ ነው ። ያሁኑም ንጉሥ ኡምቤርቶ ለኔ ወዳጄ ወንድሜ

1 Let - Marefia - L. Traversi, PP. 278 - 381; Italia ed Etiopia .,PP. 70-72.



ነውና ምናልባት እንደዚህ ያለውን መጥፎ ሥራ የምጥዋ አስተ
ዳዳሪዎች (እነ ዤኔራል ጋንዶልፊ) ይሠሩት ይሆናል እንጂ ፣ የኢጣልያ
መንግሥትና ወዳጄ ኡምቤርቶ ይሠሩታል ብዬ አልጠረጥርም ። የቀ
ረውንም ክርክራችንን ሁሉ በሰላምና በወዳጅነት እንፈጽመዋለን
እንጂ የሚያጣላን የለም ። አሁንም ይኸን የጻፍሁትን ደብዳቤ ለወ
ዳጄ ለኡምቤርቶ ወስደህ አስረክብና አንተው ራስህ ነገሩን ሁሉ አስ
ረድተህ ጨርስ ። ይኸን በመረብ የሆነውን ስምምነት ምጥዋ ያሉት
ሹሞች ሠርተውት እንደሆነ እነሱ ይቀጣሉ ። የኢጣልያ መንግሥት
ዐውቆ አድርጎት እንደሆነ መቼስ ምን ይደረጋል ። ወዳጅነቱ ቀርቶ
ጠብ መሆኑን ከዚያ ወዲያ እናውቀዋለን" አሉት ።

ለንጉሥ ኡምቤርቶ የጻፉት ደብዳቤ ይዘት ፣ የምጥዋ ባለሥልጣ
ኖች ስምምነታችንን እየጣሱ ለራስ መንገሻ መሣሪያ ማቀበላቸው
በማንም ዘንድ የተገለጸ ስለሆነ ፣ እንዲህ ያለው ሥራ የክፉ ሰዎች ሥራ
መሆኑን ፡ ራሳቸው ንጉሠ ነገሥቱ የሸፈቱባቸውን መሳፍንት እነራስ
መንገሻን ለማሳመን በሚያደርጉት ዘመቻ በመካከሉ የኢጣልያ ዜጎች
ተገኝተው ቢሞቱ በርሳቸው እንዳይፈረድ የሚያስጠነቅቅ ሲሆን ፣ የቀ
ረው ስለ ውጫሌው ውል አተረጓጐምና አሰብ ስለተያዘው ጥይት
መለቀቅ የሚያሳስብ ነው ። ለሁሉም ትራቬርሲ መላኩን ይገልጻል ።[1]
ስለዚህ ትራቬርሲ ይኸን ለኢጣልያ ንጉሥ የተጻፈውን ደብዳቤ
ተቀብሎ ሲያበቃ ፣ "የኢጣልያ ንጉሥ እንደዚህ ያለውን ዝቅተኛ አድ
ራጎት አይፈጽምም . . . አሁንም ሁሉንም እኔ ጨርሼ እስከመለስ
ድረስ ግርማዊነትዎ ምንም ዓይነት እርምጃ እንዳይወስድ ፣ በአሰብ
ያለውንም 2 ሚሊዮን ጥይት እኔው ራሴ እንዲመጣ አደርጋለሁ ።
ነገር ግን ፣ ወደ አዲስ አበባ እስኪደርስ ያምስት ወራት ጊዜ መፍጀቱ
አይቀርም ብሎ መለሰላቸው ።

በዚህ ጊዜ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አነጋገሩ ስለ አስደሰታቸው፣ እርሳቸውም
በበኩላቸው በስጦታም ፣ በንግግርም አስደስተው አሰናበቱት ። በዚያም
የነበሩት ራስ መኰንን ለኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትርና ለዥዎግራፊያ
የኢጣልያ ማኀበር ፕሬዚዳንት የተጻፉ የወዳጅነት ደብዳቤዎች ሰጥ
ተውና ከንጉሠ ነገሥቱ የተረፈውን አሟልተው አስረድተውት ፣ በመ
ልካም ስሜት አሰናበቱት ። ከግቢ ሲወጣ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዞ በጥሩ
ዕቃ የተጫነች የምታምር ሰጋር በቅሎ በስጦታ ቀረበችለት ።

በዚህ ዓይነት ዶክተር ሊዎፖልድ ትራቬርሲ ፣ በግንቦት ወር ላይ
ከአዲስ አበባ በሐረርና በዘይላ አድርጎ አሰብ ደረሰ ። ከአሰብ በመ
ርከብ ተሳፍሮ በሐምሌ ወር ሮማ ደረሰ ። በዚህ ጊዜ ከዚህ በፊት

1 Italia ed Etiopia . . .p. 55

እንዳመለከትነው ፣ ክሪስፒ ተሸሮ ጂዎሊቲ ጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ፣ በዲሩዲኒ ፉንታ በኔዴቶ ብሪ የሚባለው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ይዘው ነበረ ። እነዚህ አዳዲሶቹ ባለሥልጣኖች ቅኝ አገር ማስፋፋትንና ለዚህም ብዙ ገንዘብ ማውጣትን እምብዛም የማይፈልጉ ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በስምምነት መቀጠልን የሚመኙና የቀድሞዎቹ ባለሥልጣኖች እነክሪስፒ የሠሩትን በመጠኑም ቢሆን የሚቃረኑ ናቸው ። ስለዚህም የምኒልክ መልክተኛ ሌዎፖልድ ትራቬርሲ መልክቱን እንደልቡ ለማከናወን በሮማ የተደለደለ ሜዳ አጋጠመው ። በዚህም ለውጥ ትራቬርሲ ሲቀናው ፣ የመጨረሻውና ዋናው ተጠቃሚ ያፄ ምኒልክ መንግሥት ሲሆን የሚጐዱት ደግሞ በሌላው አንጻር ራስ መንገሻ መሆናቸው ነው ።

ትራቬርሲ ይዞ የሔደውን ደብዳቤ ለንጉሡና ለየባለሥልጣኖቹ አድሎ ከጨረሰ በኋላ ለንጉሡም ፣ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በመረብ ከራስ መንገሻ ጋር የተደረገው ውል ለኢጣልያ በፍጹም የማይጠቅማት መሆኑን ገለጸ ። ራስ መንገሻ ባሁኑ ጊዜ ጠንካራ የወታደር እቅዋምና ብዙም ተከታይ የሌላቸው ሲሆኑ ፣ ዐፄ ምኒልክ ግን ምንም እንኳን ባንዳንድ ቦታ ሽፍታ ባይጠፉም ፣ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተገዛላቸውና ለከፋም ፣ ለደጉም ሕዝቡ የሚከተላቸው መሆኑን በዝርዝር አስረድቶ ከራስ መንገሻ ጋር የተወጠነው የወዳጅነት ፖለቲካ በፍጹም እንዲለወጥና በማናቸውም ረገድ የወዳጅነቱ ጉዳይ ከምኒልክ ጋር እንዲጸና አጥብቆ አሳሰበ ። አዳዲሶቹ ባለሥልጣኖችም የርሱን አባባል እያጤኑ ወደ መቀበል አዘነበሉ ።

እንደዚሁም በአሰብ የተቀመጠው 2 ሚሊዮን ጥይት አንድ ቀን ጠላት ሊሆነን ለሚችለው ለምኒልክ አይሰጥ የሚሉ ነበሩ ። ለነዚህም መልስ ዶክተር ትራቬርሲ ፣ "ራሳቸው የገዙትን ጥይት ስንከለክላቸው ትርፉ ቅያሜና ጠብ ነው ። የፈለጉትን ያህል ጠመንጃና ጥይት እኛ ብንከለክላቸው በጅቡቲ በኩል ከፈረንሳዮቹ በቀጥታ ሊያገኙ ይችላሉ" ብሎ አስረድቶ አሳመነ ። ከራስ መንገሻ ጋር መረብ ላይ "ወዳጅህ ወዳጄ ፣ ጠላትህ ጠላቴ ነው" ተባብሎ የተዋዋለውን ጄኔራል ጋንዶልፊን አሽሮ ፣ በርሱ እግር ጄኔራል ኦሬስቲ ባራቲዬሪን አሾመ ። ባራቲዬሪ እስካሁን ምክትል ገዥ ሆኖ ሲሠራ አለቃው ጋንዶልፊ የወጠነውን አዲስ ፖለቲካ የሚቃወም ነበር ።

የኢጣልያ መንግሥት ፣ በምንም ዓይነት መንገሻን እንደማይረዳ ለምኒልክ እንዲያረጋግጥ ሊዎፖልዶ ትራቬርሲ ከመንግሥቱ መሪዎች ቃል ተቀብሎና በዚህ ዓይነት ጉዳዩ ሁሉ ቀንቶት ተመለሰ ።



እርሱም ከሮማ ወደ አሰብ መጥቶ 2 ሚሊዮን ጥይት በስድስት መቶ ግመል አስጭኖ እስከ አንኮበር አመጣ ። ከአንኮበር ደግሞ አዛዥ ወልደ ጻድቅ ተቀብለው ወደ አዲስ አበባ አደረሱ ። ትራቬርሲም ወደ አዲስ አበባ እንደ ተመለሰ ለንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ቀድሞውንም እንደተናገርሁት ስምምነቱ ለጉርብትና ጉዳይ ነበር እንጂ ፣ የኢጣልያ መንግሥት የለበትም" ብሎ በመንግሥቱ ስም በማረጋገጥ አንድ ታላቅ ጉዳይ እንዳከናወነ ተሰምቶት በመመካት ገለጸላቸው ።[1]

እንደ እውነቱ ፣ የኢጣልያ መንግሥት መሪዎች ከፋፍለህ ግዛ ተብሎ ካባቶቻቸው ከሮማውያን የወረሱትን ፍልስፍና በመጠቀም ራስ መንገሻን በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለማስነሣት ከልብ አቅደው እንደ ተነሡበት ሰነዱ ሁሉ በግልጽ አመልክቷል ። አሁን የተሻረው ጄኔራል ጋንዶልፊ መረብ ላይ ከራስ መንገሻ ጋር የተዋዋለው የዚህኑ መሪ ትእዛዝ ኔራሲኒ ከሮማ ከንጉሡ ከኡምቤርቶና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ ዘንድ ካመጣለት በኋላ መሆኑን ባለፈው አመልክተናል ።

ኢጣሊያኖች ፣ ንጉሠ ነገሥታዊው መንግሥት መጽናቱን ፣ የራስ መንገሻንና የራሳቸውን አቅም ደካማነት አመዛዝነው ከራስ መንገሻ ጋር የዶለቱት ውለታ ሩቅ መንገድ እንደማያዘልቅ ሲረዱት ፣ ወንጌልና መስቀል አቅርበው ፣ "የራስ መንገሻ ጠላት ጠላታችን ነው" ብለው በመሐላ ያረጋገጡትን በቀላሉ ክደውና ወዳፄ ምኒልክ ዞረው ራሳቸው የራስ መንገሻ ጠላት ለመሆን በቁ ። ለጄኔራል ባራቲዬሪም ከዚህ በፊት እንደ ተባለው ፣ "እኛ በቂ ገንዘብ ስለሌለን ወደ አፍሪካ አዲስ ወታደር ለመላክም ሆነ ጦርነት ለማድረግ ፣ ካለው በቀር ግዛት ማስፋፋትም አንፈልግምና በተቻለ መጠን ከንጉሠ ነገሥቱ ከምኒልክ ጋር በወዳጅነት ስምምነት ለማድረግ ሞክር ። ለራስ መንገሻ በሩቅ የወዳጅነት ስሜት ከማሳየት በቀር ማናቸውንም የጦር እርዳታ አታድርግ ። የጦር መሣሪያም በፍጹም አትስጥ" የሚል ዝርዝር መሪ ትእዛዝ ባዲስ ዓይነት ከመንግሥቱ ደረሰው ። ምኒልክም የራስ መንገሻንና የኢጣልያን ወዳጅነት በትራቬርሲ በኩል ካስፈረሱ በኋላ ራስ መንገሻ እንዲገቡላቸው ጥሪያቸውን አጠነከሩ ።

ራስ መንገሻም ፣ ራስ አሉላም ፣ ይኸን ሁሉ የተደረገባቸውን ክዳት ስለ አልተረዱት ፣ ከሸዋ የሚደርሳቸውን ጥሪ ችላ እያሉ ፣ በዚያው በወንጌልና በመስቀል መሐላ በተዋዋሉት ውላቸው ተማመኑ ። ተጠርተን

1 Let - Marefia . . p. 382; Italia ed Etiopia . . „Conti Rossini, p. 75 - 76

ስንቀር ከሸዋ ጦር መምጣቱ አይቀርም በሚል ግንጋኔ ፡ “ማናቸው-
ንም ለመመከከር እንገናኝ” ብለው ቀጠሮ ቢጠይቁት ፡ ባራቲዬሪ
የፖለቲካውን ለውጥ ሳይገልጥ ምክንያት ብቻ እየፈጠረ ገሸሽ አደረ
ጋቸው ። ቢሆንም ፡ በዚያው ሰሞን ባራቲዬሪ ሠራዊን ሲጎበኝ እርሳ
ቸው ካሉበት ሩቅ ስላልነበረ ፡ “ራስ አሉላ መጥቼ ልገናኝህ” ብለው
ቢልኩበት የማይችል መሆኑን ስለ ገለጸላቸው ፡ የኢጣልያ መንግሥት
እንደ ከዳቸው ተረዱት ። በዚህ ጊዜ ፡ ሹም አጋሜ ተስፋዬ የሚባሉት
የራስ መንገሻ ባለሟል ከበፊቱ ሁኔታውን ይጠራጠሩ ኖሮ ፡ “ጣልያ
ኖች ለማንም የማይታመኑ ለሁሉም በሐሰት ወዳጅ የሚመስሉ አታ
ላዮች ናቸው” ሲሉ በራስ መንገሻ ፊት ተናገሩ ይባላል ።

ከዚህ በኋላ ነገሩን ለብዙ ጊዜ መደበቅ ስለ አልተቻለ ፡ “ከእንግ
ዲህ ወዲያ እኛ አንረዳዎትም ፡ ወደ ንጉሠ ነገሥትዎ ገብተው ይታረቁ”
እያሉ በመልእክት በይፋ ይገፋፉዋቸው ዠመር ። ይኸም አንሶ ባንድ
ወገን የኢጣልያን ንጉሥ እንደ በላይ አድርጎ ለማስከበር ፡ በሌላው ወገን
ምኒልክ በሙሉ ተደስተው ፡ “እንግዲህስ የመረብን ወሰንና 17ኛውን
አንቀጽ ልቀበል” ወደ ማለት እንዲያዘነብሉ ለማድረግ ጄኔራል ባራ
ቲዬሪ ያንኑ የራስ መንገሻ ወዳጅ የተባለውንና ከንጉሡ ከኡምቤርቶ
ተልኮ በመረብ ከጋንዶልፊ ጋር እንዲዋዋሉ ያደረጋቸውን ካፒታኖ
ደማርቲኖን ልኮ ፡ “ለግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ ፈቃድ በመታዘዝ ያኔ
ምኒልክን ንጉሠ ነገሥትነት እቀበላለሁ” ብሰው ራሳቸው ወደ ዳግማዊ
ምኒልክ ቢጽፉና ቢታረቁ ይሻላል ብሉ ላከባቸው ። በራስ መንገሻ
በኩል ነገሩ በጣም አናዳጅ መሆኑ አይጠረጠርም ። በዚህ ጊዜ በራስ
መንገሻም ፡ በራስ አሉላም ዘንድ የሚያድረውን የሐዘንም የጸጸትም
ይልቁንም የትዝብት ስሜት ለመረዳት ቀላል ነው ። ሹም አጋሜ
ተስፋዬም ፡ “ጣልያን አታላይ ነው” የሚለውን ቃል የወረወሩት እዚህ
ላይ ሳይሆን አይቀርም ። የዚህ ዓይነቱም አታላይነት በግልጽ በእድ
ራጎት የታየ ስለሆነ ነጋሪም አያሻውም ። “ለግርማዊ የኢጣልያ ንጉሥ
ፈቃድ መታዘዝ” የሚለው ቃል እንዲጨመር የፈለጉት ፡ ዐፄ ምኒልክ
የኢጣልያ ንጉሥ ለካ ሥልጣን አለው ብለው እንዲያምኑ ሆን ተብሎ
የተደረገ የቂልነት ዘዴ ነው ።

ቢሆንም ፡ ራስ መንገሻ ትዝብትና ጸጸታቸውን በልባቸው እንደ
ያዙ ፡ “ደህና ነው እንዳላችሁት በናንተው አስታራቂነት የምኒልክን
የበላይነት ዐውቃለሁ ! ወደ ሸዋም ሔጄ ከምኒልክ ጋር እገናኛለሁ”
የሚል የቃል መልእክት ጨምረው በደብዳቤ ግን ፡ “ዓድዋ ድረስ መጥቼ
ከእርስዎ እንገናኝና ሐሳቤን ገልጨልዎት ወዳጅነታችንን እናጽና ።
ማናቸውም ነገር በደብዳቤ አያልቅምና ሁለታችን ተገናኝተን እርስ
ዎም አሳብዎን ይንገሩኝ ። እኔም በልቤ ያለውን ሁሉ ቃል በቃል



ልገልጽልዎት” ብለው በጽሑፍ አስፍረው ያንኑ ደ ማርቲኖን መል
ሰው ወደ ጄኔራል ባራቲ ፡ ላኩት ።

ጄኔራል ባራቲዬሪም ፡ ~ኸ ደብዳቤ ሲደርሰው ሁኔታውን ትንሽ
ስለሚያፍርበት እሺ ማለት አልፈቀደም ። በዚህ ጊዜ ሌዎፖልዶ
ትራቬርሲ ለጥይቱ ጉዳይ አሰብ ነበርና ወደ ምጥዋ በቶሎ ተጠ
ርቶ ከምክሩ ውስጥ ገባ ። በምክሩ ጊዜ ፡ “የዚህ ቀደሙ የጋንዶልፊ
አንሶ አሁን ደግሞ አገረ ገዥው ባራቲዬሪ ዓድዋ ሔዶ ከመንገሻ
ተገናኘ ሲባል ወሬው በቶሎ ሸዋ ደርሶ የምኒልክን ቁጣ በመቀ
ስቀስ የተዠመረው የሰላም መንገድ ስለሚበላሽ አይሆንም” ብሎ
ስለ ተናገረ ፡ በዚሁ ተወስኖ ባራቲዬሪ አሁንም ግንኙነቱን እንደማይ
ፈልግ ገለጠላቸው ።[1]

እንግዲህ ራስ መንገሻም ፡ ራስ አሉላም ቢወዱም ቢጠሉም ወደ
ንጉሠ ነገሥቱ ተላልከው ከመግባት በቀር ሌላ ምርጫ እንደሌላቸው
ተረዱት ። ራስ መንገሻ በዚህ ዓለም ብዙ ጊዜ በሕይወት ላይ የሰው
ልጅ ሊቀበለው የማይፈልገውን ፡ የመቀበል ግዴታ እንደሚያጋጥመ
ውና ስለ ሕዝብም ኃላፊነት እንዳለበት በመገንዘብ ፡ ያለ አንድ
የውጭ ኃይልም ድጋፍ የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመመለስ አለመቻ
ሉንና የማይቻለውንም እንደሚቻል አድርጎ በእልህ ጦርነት መዠመር
ሕዝብንና የተከተላቸውን የንጹሑን ወታደራቸውን ደም በከንቱ ማፍ
ሰስ ፡ የራሳቸውንም ሕይወት አደገኛ ሁኔታ ላይ መጣል መሆኑን ይረ
ዱታል ።

ስለዚህ ፡ ልባዊ ጉብዝና የሚሰማቸው ራስ አሉላ ቀድሞም
የመረቡን ውል ከልብ እንዳልተቀበሉት አሁንም የራስ መንገሻ
በቶሎ ወደ ሰላም ማዘንበል ቅር ብሏቸው ሲያፈነግጡ ፡ መንገሻ
ግን የመንገሡ ተስፋ በኢጣልያኖች ግልጽ ክዳት ፈጽሞ ስለ
ጠፋ በሰላም ለመግባት ወዳፄ ምኒልክ መላላክ ዠመሩ ። ምኒልክ
ደግሞ ለውጊያ እንደማይቸኩሉ ሁሉ ፡ ያለውዴታውም ቢሆን በሰ
ላም ገብቶ በሚገዛላቸው ፊት የፉከራና የድንፋታ ስሜት አያሰ
ሙም ። በዚህ ፈንታ ጥፋቱን ሸፍነውና አረሳስተው ሸፍቶ ቆይቶና
ተመልሶ የገባላቸውን ሳይቆጡ በደስታ በመቀበል ፡ መልሶም ከልቡ
የጥቃቱና የመሸነፉ መንፈስ እንዲጠፋለት ማድረጉን ያውቁበታል።
የኢትዮጵያን ሕዝብ ባንድ እግር አቁመው ባንድ ሥልጣን አስተባ
ብረው በዓድዋ ከኃያሉ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ለመዋጋትም ለማ
ሸነፍም የረዳቸው የዚህ ዓይነቱ አቅዋም ነው ።

1 Memoire d' Afrique -O.- Baratieri pp. 39 - 43 ; Italia ed Etiopia - C. Rossini PP. 76 - 81; Let - Marefia -L. Traversi, Cap. XLIII - PP. 391 - 399

ባጠገባቸው በመቆየት የምኒልክን ጠባይ የገመገመው ሲልቪ ቪኜራስ የሚባለው የፈረንሳይ ተወላጅ ከኢትዮጵያ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ እንደዚህ ይላል ።

“ . . . ምኒልክ በጠባዩ መሐሪ ነው ። ደግሞም የጭካኔ ቅጣት ጥላቻን እንደሚወልድ ያውቃል ። ከጠባዩ ሁሉ በላይ ደግነቱ ጐልቶ ይታያል ። ሕዝቡም ከልብ ይወደዋል ። አሸንፎ የያዛቸው እንኳን ቀድሞ እርስ በርሳችን በየነገዳችን ያስዕረፍት አንዋጋ ነበር እያሉ አሁን ግን ፥ ይኸን በመሰለ መሪ ውስጥ በጸጥታ በመተዳደራቸው ተደስተዋል ። . . . . .[1]

1 Sylvian Vigneras, Une Mission Française en Abyssinie, p.191.



# ምዕራፍ ዐሥራ አምስት

## የነፊታውራሪ ጉልላቴ አድማ—የራስ መንገሻ ምሕረት ጠይቀውና ታርቀው ወደ ዐፄ ምኒልክ መግባት

ዳግማዊ ምኒልክ ፥ በራስ መንገሻ ላይ ደም ሳያፈሱ ሁለት ጊዜ የሰላምና የፖለቲካ ድል አግኝተዋል ። አንደኛው በ1881 ዓ.ም. እነ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ሲገቡ ፥ እርሳቸው እምቢ ብለው ራስ አሉላን ይዘው ባመፁ ጊዜ ፥ እንጦጦ ላይ በ1882 ዓ.ም. የንጉሠ ነገሥትነት ዘውዳቸውን ከደፉ በኋላ ፥ ወደ ትግሬ ራስ መንገሻን ለማስገበር ዘምተው ያለ ጦርነት ራስ መንገሻን አሳምነው ተመልሰዋል ።

አሁን ደግሞ ፥ በ1884 ዓ. ም. ላይ ራስ መንገሻና የኢጣልያ መንግሥት በመሐላ መረብ ላይ መዋዋላቸው በመንግሥታቸው ላይ ከፍ ያለ አደገኛ ሁኔታ እንደ ፈጠረ ንጉሠ ነገሥቱ አልተዘነጋቸውም ። አንድ የሠለጠነ አውሮፓዊ መንግሥት አንድን ከፍተኛ መስፍን እስከሚበቃው ድረስ በጦር መሣሪያ አስታጥቆ ራሱ ከኋላ ድጋፍ ሆኖ ሲነሣ ምናልባት ማሸነፉ እንኳን ቢያጠራጥር ፥ ላንድ አዲስ ዠማሪ ንጉሠ ነገሥት ምን ያህል ከባድና አደገኛ እንደሚሆንበት ግልጽ ነው ። ኢጣልያ አንደኛ በራሷ ፋብሪካ ማናቸውንም የጦር መሣሪያ ከተራ አልቤን እስከ መድፍ ድረስ እንደልቧ የሠራችውን ያለምንም ገደብ ከኢጣልያ አገር ወደ ምጥዋ አግዛ በማራገፍ ያገሯንም ፥ ያገር ተወላጅንም ወታደር ስታስታጥቅ ፥ በርሷ አንጻር የምትገኘው ኢትጵያ በዚህ ጊዜ ምንም ዓይነት ዘመናዊ መሣሪያ ከመሥራት ደረጃ ላይ አልደረሰችም ። በዚህም ላይ የአውሮፓ መንግሥታት አፍሪካን እንደ ልብ ለመግዛት እንዲመቻቸው ብሩክሴል ላይ በ1890 ዓ. ም. እ.ኤ.አ. በባሪያ ንግድ እገዳ አስመስለው የጦር መሣሪያ ለአፍሪካ (ለኢትዮጵያ ጭምር) እንዳይሸጥ ስምምነት ማድረጋቸው ይታወሳል ።

ስለዚህ ፥ በዚህ የቅኝ አገዛዝ በተስፋፋበት ዘመን ፥ ካንድ ከሠለጠነ መንግሥት ጋር መጣላት አደገኛ ከመሆኑም በላይ ፥ በተለይ ይህ መንግሥት ራስ መንገሻን ከመሰለ የታወቀ መስፍንና ራስ አሉላን ከመሰለ ስመ ጥሩ ዠግና ጋር ተስማምቶ ሲነሣ አደገኛነቱ የበለጠ የሰፋ ነው ። በዚህ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፥ ኢጣልያንንና መንገሻን ለማለ

ያየት ረቂቁን የፖለቲካ ዘዴ ባላቸው ሙሉ ኃይል ተጠቅመው በሚሠሩበት ወቅት ሥጋት በሕሊናቸው ውስጥ እንደሚመላለስ አይጠረጠርም ። ስለዚህም ፣ በኢጣልያ ግንባር ባለፈው የተመለከትነውን የማለያየት ፖለቲካ እየሠሩ ባገር ውስጥ ደግሞ ፣ ራስ መንገሻን ለማጋለጥና ደጋፊ ለማሳጣት ሌላ ዓይነት የፕሮፓጋንዳ ዘዴ በትግሬ ይነዛሉ ።

በዚህ ምክንያት ፣ የራስ መንገሻን ክዳት እንደሰሙ ትራቬርሲን ወደ ሮማ በላኩበት ወቅት ፣ "የመንገሻን ነገር እዩልኝ መሐላና ግዝቱን አፍርሶ እኔን አባቱን ከድቶ ከማያውቃቸው ሰዎች ጋር ሆኖ ጠላት ሊሆነኝ ነው ። እኔም እንግዲህ ወደናንተ መዝመቴ ነው ። ካህናቱ ቢበድሉ ፣ ቤተ እግዚአብሔር ቢጠፉ ነጻ ነኝ"[1] የሚል የኃይል እርምጃ እንደሚወሰዱ ወደ ትግሬ አድባራት እየላኩ በማስፈራራት በፖለቲካው ዘዴ ጐን ኃይላቸውን ለማሳየት ይጣጣሩ ነበር ።

ዳግማዊ ምኒልክና ራስ መንገሻ ፣ በዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚገኙበት ጊዜ ሁለቱም በየቤታቸው የውስጥ አድማ አጋጥሟቸው ነበር ። በ1885 ዓ. ም. የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ የልጅ ልጅ የመርዕድ አዝማች ኃይሌ ልጅ ፊታውራሪ ጉልላቴ (ተክለ ማርያም) እስከ አሁን በመልካም አገልግሎት የቆዩትን የንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ሆነው በትግሬ ተሾመው የነበሩትንና የመረቡ ስምምነት ወደ አዲስ አበባ ያባረራቸውን ደጃች መሸሻ ወርቄንና አለቃ አድማሱን ጨምረው ንጉሠ ነገሥቱን አስገድለው ጉላልቴ ንጉሠ ነገሥት ፣ መሸሻ ወርቄ ራስ ቢትወደድ ሊባሉ ማደማቸው ተገለጸና ተያዙ ። በዚህም ጊዜ እነዚህ ሁሉ ከራስ መንገሻና ከኢጣልያኖች ጋር ስምምነት አድርገዋል ተብሎ ተወራ ።

ደጃች መሸሻ ወርቄ ፣ ኢጣልያኖችና ራስ መንገሻ በምኒልክ ላይ መስማማታቸውን በዝርዝር ስለሚያውቁ ፣ ምናልባትም ፈረንጅ በዚህ ዓይነት ሲነሣ አበሻ አይመልሰውም በሚል ግምት የምኒልክ ዕድል እንዳለቀ ቆጥረው አዲስ የኑሮ ቤት ለማስናዳት አስበው ይሆናል ። በዚህም ላይ ዓፄ ምኒልክ አገልግሎታቸውን ያበረከቱት ከመዠመሪያው ዠምሮ ስለሆነ እነራስ ወሌ ፣ እነራስ መንገሻ አቲከም ፣ እነራስ መኰንን ራስ ሲባሉ ፣ እኔስ ለምን ቀረብኝ የሚል ውስጠ ንዴት እንዳላቸውም አይታወቅም ። ጸሐፊ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ እንደሚሉት ምኒልክ የአድማውን ወሬ እንደሰሙ እውነተኛነቱን በመጠራጠር

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 212 ።



ብዙ ጊዜ ቆይተው ሳለ ፣ እያደር እውነትነቱን ስለ ተገነዘቡት እንዲያዙ አድርገዋቸዋል ።

ንጉሠ ነገሥቱ ደብረ ሊባኖስ ሳሉ ፣ ጳጳሳቱ አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ማቴዎስ ፣ እጨጌ ገብረ ሥላሴ ፣ ራስ ዳርጌ ፣ ራስ ሚካኤልና ራስ ወሌ ሌሎችም ባሉበት አድመኞቹ እንደ ተያዙ ቀርበው በአደባባይ ሲመረመሩ ፣ ንጉሠ ነገሥቱን ለመግደል ማደማቸውን አመኑ ። የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ለመደብደብ ሊሔዱ ሲሉ ጳጳሳቱም ፣ መሳፍንቱም ከተቀመጡበት ተነሥተው የሞቱ ፍርድ እንዲቀርላቸው ልመና አቀረቡ ። በዚያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "እነዚህ ካልተቀጡ በነዚህ ምን መጣባቸው እያለ ሌላው ሁሉ እንዲህ ያደርግ የለምን" ቢሉ ፣ ጳጳሳቱና መሳፍንቱ ፣ "እስካሁን ድረስ ጠላትዎን የሚጥልልዎና የሚቀጣልዎ እግዚአብሔር ነው እንጂ ፣ እርስዎማ ማንን ቀጥተው ያውቃሉ? አሁንም ስለ እግዚአብሔር ብለው ይማሩልን" ብለው ልመናቸውን ስለአጸኑ ፣ የሞቱ ፍርድ ወደ እስራት ተለውጦ ፊታውራሪ ጉልላቴ ለራስ ዳርጌ ፣ ደጃች መሸሻ ለደጃች ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፣ አለቃ አድማሱ ለደጃች ወልዴ ተሰጥተው ታሰሩ ።

ፊታውራሪ ጉልላቴ ፣ በራስ ዳርጌ እጅ ሰላሌ ፣ ሸንኩርት እንደ ታሰሩ በ1887 ዓ.ም. ሲሞቱ ፣ ደጃች መሸሻ ወርቄና አለቃ አድማሱ በኋላ ምሕረት አግኝተው ተመልሰው ባለሟል ሆኑ ። ገንዘብ ተቀብሎ ዐፄ ምኒልክን ከሰገነት ደርብ ላይ ገፍትሮ ለመጣልና ለመግደል የተመደበው ልጅ አበበ የሚባለው የልፍኝ አሽከር ግን እጅና እግሩን ተቆርጠ ተቀጣ ።[1]

በዚህ ዓይነት ፣ ተመሳሳይ አድማ በትግሬ በራስ መንገሻ ዘንድ ተፈጽሟል ። በአዲስ አበባ ባፄ ምኒልክ ላይ የተነሣው አድማ ከኢጣልያኖቹና ከራስ መንገሻ ስምምነት ጋር በመጠኑ የተያያዘ እንደሚመስለው ሁሉ ፣ በራስ መንገሻ የተነሣውም አድማ ራስ መንገሻን ኢጣልያኖቹ ስለከዷቸው ብቻቸውንም የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመመለስ ስለማይችሉ ፣ መቸገራቸውን በመገመት በዚህ ችግር ጠላቶቻቸው ለመጠቀም አስበው ይሆናል ።

አድማውን የወጠኑት ፣ የትልቁ የራስ አርአያ ልጆች እነደጃች ቦጋለ ናቸው ። የራስ አርአያ ቤት ትክለኛ ባላባትነቱ በእንደርታ ስለሆነ ፣ ለሹም ተምቤን ምርጫ ቤትም ሆነ ለአጋሚው ለደጃች

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ፣ ገጽ 197 ፣ የብላቴን ጌታ ኅሩይ ሳይጠረዝ የቀረው የታሪክ መጽሐፍ ገጽ 99 ።

ሰባጋዲስ ቤትም መግዛት እንደማይወድ ከዚህ በፊት አመልክተናል። ደጃች ደብብ አርአያ፣ ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ከግብጾችም ከኢጣልያኖቹም ጋር ሆነው ዐፄ ዮሐንስን ሲያስቸግሩ የኖሩትና አሁንም ከራስ መንገሻና ከራስ አሉላ ጋር ሲዋጉ የሞቱበት ሰበብ ይኸው ነው። ወንድማቸው ደጃች ቦጋለ አርአያና ያጐታቸው የደጃች ማሩ ልጅ መሸሻ፣ ግዴታም ሆኖባቸው ካፄ ዮሐንስ ጋር መተማ ዘምተው ነበር። ካፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ የመንገሻን አልጋ ወራሽነት በሰሙ ጊዜ አኩርፈው፣ ጓዛቸውን ከነራስ መንገሻ ጓዝ ለይተው ወደ እንደርታ መጥተው ነበር። ባለፈው ደጃች ደብብ ከነራስ መንገሻ ጋር ተዋግተው የሞቱ ጊዜ ደጃች ቦጋለ አብረው ከወንድማቸው ከደጃች ደብብ ጋር ሆነው ተዋግተው ነበር።

አሁንም እኚሁ ደጃች ቦጋለ፣ ደጃች ብሩ የደራው፣ ደጃች ሐጎስ የገራልታው፣ ደጃች ጐርፉ የእንደርታው፣ ፊታውራሪ መሸሻ የተምቤኑ ሆነው ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ለመግደል አድመው ሳለ አድማውን ከመከከላቸው የቅርብ ዘመድ አውጥቶ ለነራስ መንገሻ ነገራቸው። በዚህ ጊዜ ደጃች ቦጋለ፣ ደጃች ብሩ፣ ደጃች ሐጎስና ደጃች ጐርፉ ተይዘው ታሰሩ። ደጃች ቦጋለ በመካከሉ ከእስር ቤት አምልጠው ወደ ሸዋ መጥተው ላፄ ምኒልክ ገቡ። ራስ መንገሻን ለመግደል ተመድበው የነበሩት ፊታውራሪ መሸሻ፣ እጅና እግራቸው እንዲሁም መላሳቸው ተቆርጦ ከተኙበት ዘመዳቸው የደጃች ዋህድ ልጅ ደጃች ካህሳይ እንሥተው ወደ መቀሌ ወስደው በቤታቸው እንዳስተኟቸው ሞቱ።[1]

በዚህ ዓይነት ራስ መንገሻ፣ አድመኞቻቸውን አጥፍተው ለመንገሥ ማሰባቸውን ሐውዜን ላይ ለሕዝብ ከገለጹ በኋላ ኢጣልያኖቹ ስለ ከዷቸው፣ የራሳቸውም ኃይል የንጉሠ ነገሥቱን ጦር ለመመለስ እንደማይችል በመገንዘብ በ1886 ዓ.ም. ላይ ባለፈው ሥራቸው ተጸጽተው፣ "ይማሩኝ ልግባ" የሚል ደብዳቤ ጽፈው በሹም አጋሜ ተስፋዬ እጅ አሲዘው ወደ ዐፄ ምኒልክ ላኩ። ንጉሠ ነገሥቱም ደብዳቤውን አንብበው፣ "ቀድሞውንም ቢሆን የኢትዮጵያ ጠላቶች አስመስለው ቢነግሩት ይሆናል እንጂ፣ እርሱ ከልቡ አንቅቶ ይኸን ሥራ እንዳልሠራው ዐውቃለሁ" ብለው፣ "ባለፈው ጥፋትህ ሁሉ ምሬሃለሁና ወደ አዲስ አበባ እንድትመጣ ይሁን" ብለው መልሱን ላኩባቸው። ቀጥሎም አንዳንድ ሽፍታ ተነሥቶ በመንገድ ማስቸገሩን ስለ ሰሙና የፋሲካን መቃረብም ተመልክተውና አጢነው ንጉሠ ነገሥቱ፣ "ፋሲካን

1 Italia ed Etiopia . . . p. 79.



ውለህ እንድትመጣ" የሚል መልስ አሲዘው እኚሁኑ ተስፋዬን መልሰው ላኩዋቸው።[1]

"የኢትዮጵያ ጠላቶች አስመስለው ቢነግሩት ይሆናል እንጂ፣ እርሱ ከልቡ አንቅቶ ይኸን ሥራ እንዳልሠራ ዐውቃለሁ" ብለው የተናገሩትን ስናስታውስ፣ ይኸን የመሰለውን የዘዴ አነጋገር ምኒልክ ብዙ ጊዜ ሲጠቀሙበት ይታያል። ጋንዶልፊ ከራስ መንገሻ ጋር መረብ ላይ በተዋዋለ ጊዜ፣ "እንደዚህ ያለውን ሥራ የምጥዋ አገረ ገዥዎች ይሆናሉ እንጂ፣ ወዳጄ የኢጣልያ ንጉሥ ያደርጉታል ብዬ አልጠራጠርም" ብለው የጻፉትን ከዚህ በፊት ያነበብነው ትዝ ይለናል። ከ1880—81 ዓ. ም. ምኒልክ ባፄ ዮሐንስ ላይ በሸፈቱ ጊዜ በደብዳቤ ሲወቃቀሱ፣ "ይኸን ሁሉ እያደረገ እናንተንና እኔን ሰይጣን ሆኖ የሚያፋጀን በጌምድሬ መሸሻ ወርቄ የሚባል መከር አበጅታችሁ የተንኮሉ ሁሉ ምንጭ እርሱ ነው እንጂ፣ ከንጉሥም ከናንተም ይኸን ያህል ተንኮል እንደሌለ ዐውቃለሁ" ብለው ዐፄ ዮሐንስ ለራስ ዳርጌ የጻፉትን ስናስታውስ፣ ይኸ ዓይነቱ የአነጋገር ዘዴ ባፄ ምኒልክ ብቻ ሳይሆን በሌሎቹም ዘዴኛ ነገሥታት በብዙ ይሠራበት እንደነበረ እንገነዘባለን። ዘዴውም የሸፈተውን ልብ ወደ ሰላማዊነት ለመሳብ የሚረዳና አብሮ በሰላም ለመኖር የሚያግዝ መሆኑ ነው።

በእርግጥም፣ የኢትዮጵያ ጠላቶች፣ እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አባባል፣ ከሮማ መጥተው፣ "ሸፍትና አንተው ንገሥ፣ የኢጣልያ መንግሥት ትደግፍሀለች" ብለው በመገፋፋት መንገሻን ከመቀሌ፣ ጋንዶልፊን ከምጥዋ መረብ ድረስ አስጉዘው ያዋዋሉትን ኔራሲንንና ደ ማርቲኖን ወይም ራስ መንገሻን ወደዚህ ጉዳይ ገፍተው ያገቧቸውን የትግሬ መኳንንቶችን ወይም ሁለቱንም ወገኖች ይሆናል። በተለይም ያፄ ዮሐንስ ባለሟልና የልብ ወዳጅ የነበሩት አሁን ክብራቸውና ጥቅማቸው ወደ እጨጌ ገብረ ሥላሴ የተዛወረባቸው ሽማግሌው እጨጌ ቴዎፍሎስ መንገሻን ከምኒልክ በማለያየቱ ተግባርና ከኢጣልያ በማስማማቱ ጉዳይ ከሁሉም የበለጠ እንደ ነበሩበት የታወቀ ነው።[2]

ራስ አሉላ፣ በመረቡ ስምምነትና መሐላ እስከዛሬ ሲዋጉዋቸው ለኖሩት ለኢጣልያኖች ወዳጅነት እታመናለሁ ማለቱ ቀፏቸው፣ "ለራስ መንገሻ ብቻ እታመናለሁ" ሲሉ፣ የውሉ ለት ያረጋገጡትን ባለፈው አንብበናል። አሁንም ራስ መንገሻ ሹም አጋሜ ተስፋዬን የዕርቅና

1 ታሪከ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . .ገጽ 212፣ ሳይጠረዝ የቀረው የብላቴን ጌታ ኅሩይ መጽሐፍ ገጽ 173—175።
2 ያልተጠረዘው የብላቴን ጌታ ኅሩይ ጽሑፍ፣ ገጽ 175።

የምሕረት ጥያቄ ደብዳቤ አሲይዘው ወደ አዲስ አበባ ላፄ ምኒልክ ሲልኩ ራስ አሉላ በነገሩ አልተስማሙበትም ። ራስ መንገሻ መቀሌ ሆነው ካፄ ምኒልክ ጋር ሲላላኩ በዚህም ጉዳይ የጸለምቱ ገዥ ራስ ሐጎስ ተስማምተው አብረው ባሉበት ሰዓት ፣ ራስ አሉላ ደግሞ የራስ መንገሻን ወደ ሸዋ መሔድ በመቃወም ራስ ስብሐትን ይዘው በራስ መንገሻ ላይ አድማ ዝምረው ነበር ። ለዚሁም እጨጌ ቴዎፍሎስ እንዲደረቡ ገፋፍተዋቸው ነበር ። ሽማግሌው እጨጌ ግን ፣ ሲደረቡ አልፈለጉም ። በኋላ ግን ፣ ራስ አሉላ የኢጣልያ ደጋፊነት ከቀረ ባንድ ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱም ፣ ከራስ መንገሻም መጣላቱ የማያዋጣ መሆኑንና በርሳቸውም የመለየት ዓላማ የቀረው አለመተባበሩን ሲረዱት፣ "ከመረብ ወዲህ ባለው አገር ይሾሙኛል ብዬ ሳይሾሙኝ ስለቀሩ ቅር ብሎኝ ነው እንጂ ፣ ጌታዬን ራስ መንገሻን ዐፄ ምኒልክንም አልካድሁም" ብለው የአክሱምን ካህናት አማላጅ ልከው ፣ ድንጋይ ተሸክመው ፣ ምሕረት ጠይቀው ለራስ መንገሻ ገቡላቸው ።

ራስ መንገሻም ፣ ምንም በጠቅላላው ምሕረት ቢያደርጉላቸው በራስ አሉላ የመጨረሻ ሁኔታ ቅርታቸው በርክት ብሎ ነበርና ከመቶ ባለጠመንጃ በቀር የቀረውን የራስ አሉላን ጭፍራ ገፈውና ወደ ሌላ ደልድለው ፣ ከግዛታቸውም ቆራርጠው ለነደጃች አምባዬ በመስጠት እርሳቸውን በአንዲት ወረዳ ብቻ ወሰኑዋቸው ። እንደዚሁም በቅርቡ የራስነት ማዕረግ የሰጡቸው ራስ ስብሐት ከራስ አሉላ ጋር በግልጽ ከመሸፈታቸውም በላይ እንዲያውም ፣ "አሉላ እርሳቸውን በራስ መንገሻ እግር ለማንገሥ አስበዋል ፤ ራስ ስብሐት ደግሞ ራስ መንገሻን ለመውጋት ከዋግሹም ብሩና ከራስ ወሌ ጋር ተላልከዋል" ተብሎ ተወርቶ ነበርና ለማናቸውም ለንጥጥር መቀሌ ድረስ ጠርተዋቸው ከመጡ በኋላ ፣ የጦር መሣሪያቸውን በሙሉ ተቀብለው ራስ ስብሐትን ከልጃቻቸው ከደጃች ደስታና ከደጃች አስገዶም ፣ ከወንድማቸው ከደጃች አባይ ጋር በአምባ ሰላማ አሰሯቸው ።[1]

እንደዚህ አድርገው ራስ መንገሻ ፣ የቤታቸውን ጣጣ ከጨረሱና ካደላደሉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት ተዘጋጁ ። ካፄ ምኒልክም ዘንድ የላስታው ገዥ ዋግሹም ብሩ ፣ የበጌምድሩ ገዥ ራስ ወሌ ፣ የወሎው ገዥ ራስ ሚካኤል ፣ የወረይሉው የንጉሠ ነገሥት ቤተ መንግሥት አዛዥ ቢትወደድ አጥናፌ በመቀባበል እያስተናገዱ ራስ መንገሻን እንዲሸኙ ታዘው ነበርና ፣ በዚህ ዓይነት ራስ መንገሻ ለትግሬ ጥብቅ ገዥ የዓይባውን ደጃች ተድላን ትተው ታላላቅ መኳንንቶቻቸውን

1 Italia ed Etiopia, pp. 89 - 91.



ራስ አሉላን ፣ ራስ ሐጎስን ፣ ራስ ወልደ ሚካኤል ሰሎሞንን አስከትለው በሚያዝያ ወር ከትግሬ ተነሥተው በላስታ ፣ በየጁና በወሎ አድርገው ፣ በግንቦት ወር አዲስ አበባ ገቡ ። የአክሱም ካህናትም ለምልጃና ለማስታረቅ ሥዕለ ማርያምን ይዘው አብረው መጥተው ነበር። በጉዞው ጊዜ ፣ "አዲስ አበባ ስንደርስ ተይዘን እንታሰር ይሆን ወይስ ሁላችንንም አዲስ አበባ የቁም እስር አድርገው በትግሬ ሌላ ይሾሙ ይሆን" የሚል ጥርጣሬ በአንዳንዶቹ ላይ ሲያድር ፣ ራስ መንገሻ ደግሞ ፣ "ንጉሠ ነገሥቱ ካዲስ አበባ ወጣ ብለው ባንደኛው ከተማቸው ላይ ሆነው ይቀበሉኛል" የሚል እምነት ነበራቸው ይባላል። ይሁን እንጂ እስራቱም ፣ ግዞቱም ፣ በሙሉ ምሕረት መለወጡንና ንጉሠ ነገሥቱም ከአዲስ አበባ ከቤተ መንግሥታቸው አለመነቃነቃቸውን አዲስ አበባ ሲደርሱ ተረዱት ።

ስለ አቀባበሉ ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴ ከሰጡት ዝርዝር ሐተታ ውስጥ እንደዚህ የሚል ይነበባል ።

> ...ዐፄ ምኒልክ በሥርዓተ መንግሥት ሆነው ከዙፋንዎ (ከዙፋናቸው) ተቀምጠው ራሶችም ራስ ዳርጌ ፣ ራስ ሚካኤል ፣ ራስ ወሌ ፣ እነዚህ ራስ ወርቅ አድርገዋል ። ሊቀ መኳሰቹም እንደ ሥርዓታቸው ሆነዋል ። ካህናቱም ካባ ለብሰው በቀኝና በግራ ሆነው መንበረ መንግሥቱን ያጥናሉ ... በዙፋኑም በድንኳኑም ... ያለው የወርቅ ምንጣፍ የወርቁ መከዳ ያስፈራል ። በዙፋኑም ስይፈ ዣግሬዎች ባለወርቅ መከድ* ሰይፍ መዘው ግራና ቀኝ ቆመዋል ።... ደጃዝማቾቹም መኳንንቶቹም አጊጠው የነደደ እሳት መስለው ባዳራሹ መልተው ቆመዋል ... የውጭውም ሠራዊት እንደ ማዕረግ እንደ ማዕረጉ የጦር መሣሪያውን እየለበሰ ፣ ሰንደቅ ዓላማውን እየያዘ ፣ ካዳራሹ ደጃፍ ዝምሮ የመዋቲ ወንዝ (አቧሬ አጠገብ) ተሻግሮ እየተነባበረ ፣ እየተጨናነቀ ተሰልፎ ነበር ። ከዚህም ሁሉ መሣሪያ በወርቅና በብር እያጌጠ ያንበሳ ጋማ ያሰረው ፣ ጐፈር የደረበው ከጌጡ ሁሉ እሱ ይደምቃል ። በዚህ ቀን እንኳን ሰውና መሬቲቱ አጌጠች ። ሰውም ወዲያና ወዲህ እንዳይል የግባቱ ተኩስ እንዳይመታው ተከልክሎ ነበር ...

ይኸውም ሁሉ ከተፈጸመ በኋላ ፣ ራስ መንገሻ ወደ አዳራሹ መጣ። አክሱሞችም ሥዕለ ማርያምን ይዘው ካራስ መንገሻ በኋላ ነበሩ ። ያባቱም መኳንንቶች እነራስ ሐጎስ ዐፄ ዮሐንስ ከሞቱ ከዐፄ ምኒልክ ከፊትዎ አልደረሱም ነበርና ድንጋይ ተሸክመው የቀረውም መኳንንት ሁሉ እንደዚሁ ሆኖ ወደ አዳራሹ ገቡ ። ድንጋዩንም እንደ ተሸከሙ ወደቁ ። ዐፄም ምሬአችኋለሁ አሏቸው ። አጋፋሪዎቹም ድንጋዩን ከላያቸው አነሡላቸው እነዚያም እጅ ነሥተው መሬቱን ስመው ቆሙ ። በዚህም

* መከድ ምርጥ ሰይፍ

ወቅት 31 ጊዜ መድፍ ተተኮሰ ። ያም የተሰለፈ ሰው ጠመንጃውን ሙሉ ግባት ቢተኩሰው ፣ ጢሱ ከተማውን እንደ ጉም አለበሰው ። የተ ኩሱም ብዛት ይህን ይመስላል አይባልም ።. . . ከዚህ በኋላ ግብር ገብቶ ሲበላ ሲጠጣ ውሎ ራስ መንገሻ ተሰናብቶ ወደ ሰፈሩ ተሻገረ[1]

በዚህ ዓይነት ፣ ብዙ ደም ሊያፋስስ ይችል የነበረውና በዚሁ ደም ላይ ተራምዶ ግዛቱን ለማስፋፋት ይጠባበቅ የነበረው የኢጣልያ ምኞት፣ በዳግማዊ ምኒልክ ትዕግሥትና የፖለቲካ ስልት ፣ በራስ መንገሻም እርቅ ተቀባይነት የተነካ በፍጹም ተሰናከለ ። ራስ መንገሻ ያዔ ዮሐንስ የአሳብ አልጋ ወራሽ ሲሆኑ ፣ የዐፄ ምኒልክ አልጋ ወራሽነት በተግባር የዋለ ነው ። ነገር ግን ፣ ራስ መንገሻን ሰምን ዙፋን ተመኙ? በምን ምክንያት ዐፄ ምኒልክን ከዱ ? ብሎ መውቀስ አይቻልም ። በእርሳ ቸው እግር ያለ ማንም መስፍን አልጋ ወራሽ ከተባለ በኋላ ሊያደር ገው የሚችል ነው ። እንዲያውም እንደ ደጃች ደብብ ወይም እንደ ደጃች ሥዩም አባ ኃያል ያለ መስፍን ቢሆን ኖሮ ፣ አቅሙ እንደማይ ችል ቢያውቀውም ፣ ለእልሁ ሲል ከንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር ተዋ ግቶ በከንቱ የብዙ ሰው ደም ሊያፋስስ ይችል ነበር ።

አሁን ግን ፣ ራስ መንገሻ ምሕረት ጠይቀው ከገቡላቸው በኋላ ፣ ዐፄ ምኒልክም ከልባቸው ምሕረት አድርገውላቸው ሐያ ቀን ያህል አዲስ አበባ በቆዩበት ጊዜ ከንጉሠ ነገሥቱም ከእቴጌ ጣይቱም ጋር በፍቅር ፣ በደስታ ፣ በታላቅ መስተንግዶና መንከባከብ ሰን ብተው ፣ በመጨረሻም ንጉሠ ነገሥቱ ከዘውድ በቀር ለንጉሥ የሚገባ ሙሉ ሽልማት ሸልመው ፣ ሹመታቸውንም አጽድቀው አሰናበቷ ቸውና በሰኔ ወር ከአዲስ አበባ ተነሥተው ወደ መቀሌ ሔዱ ። ራስ አሉላ ግን ፣ ከራስ መንገሻ ጋር ቅሬታ ገብቷቸው ነበርና ፣ "ከዚሁ ከአደባባይዎ ደጅ እየጠናሁ መቆየት ይሻለኛል" ብለው ለንጉሠ ነገሥቱ አመልክተው አዲስ አበባ ቀሩ ።

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ . . . ገጽ 214—215





ራስ መንገሻ ዮሐንስ ፣ ከዐፄ ምኒልክ ምሕረት ለመጠየቅ አዲስ አበባ የገቡበት
ለቱር ዲሞገድ

# ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት

## የኮሎኔል ፈሬዲሪክ ፒያና መላክና ምንም ፋይዳ ሳያገኝ ወደ መጣበት መመለስ

በኢጣልያ አገር ፡ ምጥዋ ከተያዘበት እ.ኤ.አ. ከ1885 ዓ.ም. ዥምሮ ዶ ፕሬቲስ አጉስቲኖ 1885—1887 ፣ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ 1887—1891 ዲሩዲኒ አንቶኒዮ 1891—1892 ጂዎሊቲ ጂዎቫኒ 1892—1893 እንደገና ክሪስፒ 1893—1896 እየተከታተሉ በተቀራረበ ጊዜ ውስጥ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነዋል ።

ባለፈው እንዳመለከትነው ፣ ጂዎሊቲ ጁዎቫኒ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ቤኔዲቶ ብሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ ፒሎ ሉዊጂ የጦር ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ ፡ ምኒልክን ትተው ከመንገሻ ጋር መረብ ላይ ተዋዋሉ። "እርሱን መደገፍ በማናቸውም ረገድ አያዋጣም" የሚለው አሳብ ከአንቶኔሊ ፣ ከካፒቴን ቺኪና እንዲሁም ከአንቶኔሊ ወዲህ ነገሩን እን ጦጦና አዲስ አበባ ተቀምጦ ከተከታተለው ከዶክተር ሌዎፖልድ ትራ ቬርሲ እየተሰነዘረ ጸድቆ ነበር ። በበኩላቸው ዐፄ ምኒልክም ፣ እ.ኤ.አ በየካቲት 16 ቀን 1893 ዓ.ም. በይፋ ውሉን መሰረዛቸውን ገልጠ ዋል ። ይሁን እንጂ ፡ ኢጣልያኖች ስለቅኝ አገር ፍለጋ ያላቸው ምኞት የጋለ ከመሆኑ የተነሣ ፡ ጂዎሊቲ ተሽሮ ታኅሣሥ 15 ቀን 1893 ዓ.ም ያው ቅኝ አገር ፈላጊው ክሪስፒ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲመለስ፣ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ባሮን አልቤርቶ ብላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ ሞቺኒ ስታኒስላኦ የጦር ሚኒስትር ሆኑ ። በቅኝ አገር ጉዳይ ያለውን በቀጥታ የሚመለከተው እነዚህን ሦስቱን ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ነው ። እነሱም ፡ "ለኢጣልያ እንደ እንግሊዝ ፣ እንደ ፈረንሳይ ሰፊ ግዛት እናተርፋለን" የሚለውን ዓላማ በመከተል በም ክር ቤቱም "ቅኝ አገር ይቅርብን ፣ አገራችን ይበቃናል ፤ ይኸንኑ መሬ ታችንን እናቅና" ከሚሉት ወገኖች ጋር በይፋ እየተከራከሩ ፣ የቅኝ አገር የማግኘቱን ዓላማ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ታጥቀው የተነሡ ናቸው ።

በዚሁ ጊዜ ፣ በነዚህ በሦስቱ ባለሥልጣኖች ስምምነት የኢት ጵያን ጉዳይ በዝርዝር ያውቃል ተብሎ አንቶኔሊ በውጭ ጉዳይ

ሚኒስቴር ውስጥ ምክትል ሚኒስትር ሆኖ የደረጃ ዕድገት አግኝቶ ተሾመ ። ነገር ግን ፣ ምንም ያህል ጊዜ ሳይቆይ ተሽሮ በርሱ ምትክ አዳሞሊ የሚባለው ተሾመ ።

እነዚህ ሦስት ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ፣ የፊተኞቹ ባለሥልጣኖች ስለቅኝ አገር መስፋፋት የተከተሉትን የመገታትና የጥንቃቄ አሠራር በመነቃቀፍ እንደገና ባዲስ የኃይል መንፈስ ፣ "የውጫሌ ውል ይርጋ ወይም ቢለወጥም ቃሉ ይሻሻል ፤ አለዚያም በዚህ ፈንታ ኢትዮጵያ በሰሜን ሰፋ ያለ ግዛት ለኢጣልያ መልቀቅ አለባት ። ለጊዜው ግን ፣ በኤርትራ የኢጣልያ የግዛት ወሰኑ መረብ ወንዝ መሆን አለበት" ብለው ባዬ ምኒልክና ባካባቢዎቻቸው የተጠላውን አባባል ፀነሱ ። ዋናው የኢጣልያ ፍላጐት ግን ፣ በዚህ ፅንሰ አሳብ ቆይቶ ጊዜውና ወቅቱ እንዳመቸ በተለይ ካለፈው የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ ተገነዘቡት ፣ የውስጥ ጦርነት በኢትዮጵያ መቀስቀሱ ስለማይቀር በዚያን ጊዜ ፣ መላዋን ኢትዮጵያን በውስጣቸው ለማስገባት ነበር ። ያዬ ምኒልክ አሳብ ደግሞ ፣ "በውጫሌ ውል ከተጠቀሰው አውራጃ አልፈው አገር ቢይዙ እዋጋለሁ ። ይኸን ወደጐን አድርገው ቢተዉ የንግድ ሽቀጥ በወዳጅነት እየተለዋወጥሁ በሰላም እኖራለሁ ። በብዙ ጊዜ የርስ በርስ ጦርነት የተጎዳከመችውን አገሬን የአውሮፓን ሥልጣኔ በማስገባት አለማለሁ" የሚል ነው ።

በዚህ ተፃራሪ በሆነው አሳብ ላይ ንጉሠ ነገሥቱና የኢጣልያ ባለሥልጣኖች ፣ እውነተኛ ስሜታቸውን በገሃድ ሳይገላለጡ ውስጥ ለውስጥ የሚያደርጉት የድብብቆሽ የፖለቲካ ሽኩቻ ፣ አሁን ካለንበት ዘመን ስንመለከተው ነገሩ ለኢትዮጵያ አደገኛ የሞትና የሕይወት ጉዳይ ሆኖ ይታያል ። አደጋውም የሚታየው ከመሳፍንቱ የሥልጣን ምኞት ጋር የተያያዘና ጊዜው የቅኝ አገር የወረራ ዘመን በአውሮፓዎች ዘንድ የተፋፋመበት ስለሆነ ፣ ወቅቱ ለወራሪ አውሮፓዊ እንጂ ለተከላካይ ጥቁር አመቺ አልነበረም ።

ስለዚህ ፣ በዚህ አስቸጋሪ ወጥመድ ውስጥ የሚገኙት ንጉሠ ነገሥት ፣ በራስ መንገሻም ከኢጣልያኖች ጋር መስማማት የተነሣ አደጋው ፍጥጥ ብሎ ታይቶአቸው ነበር ። ራስ መንገሻ እስኪገቡላቸው ድረስ ለኢጣልያው መልክተኛ ለዶክተር ትራቬርሲ ያነጋገር ወዝ እየሰጡ ፣ የፈገግታ መልክ እያሳዩ ፣ "ሁሉም ነገር በሰላምና በወዳጅነት ያልቃል" በሚል ባልተወሰነና በአወላዋይ ዘይቤ ፣ በአንደበት ከመደለል በቀር ፣ "መንገሻን ከዳችሁ የኔን ወዳጅነት ብታጸኑ ይኸን አደርግላችኋለሁ" ብለው በጽሑፍም ፣ በቃልም ምንም ዓይነት ግልጽ የሆነ ተስፋ አልሰጡም ። ኢጣልያኖቹም ፣ ምኞታቸው ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ



በወረራ ዓላማቸው ኃያሉ እንግሊዝ ተባባሪ ስለሆነ ፣ "መንገሻን ብንከዳልዎና የመረቡን ስምምነት ብንሰርዝልዎ ይኸን ያደርጉልናል" ብለው የውስጥ ምኞታቸውን ገልጸው ፣ በመንገሻ ክዳትና በኢጣልያ የጦር ኃይል የሠጉትን ንጉሥ ግዴታ ለማስገባት አልደፈሩም ።

እንደሚመስለው ፣ አሳባቸው ያተኮረው ደከም ብለው የታዩዋቸውን ፣ "ራስ መንገሻን ከደን ከኃይለኛው ከምኒልክ ጋር የኖረ ወዳጅነታችንን ካጸናንና አሰብ ላይ ለግልግል መያዣ ሆኖ የቆየውን ሁለት ሚሊዮን ጥይት ከአስረከብን ፣ ከዚያ ወዲያ ምኒልክ የውጫሌውንም ስምምነት ፣ የመረቡንም ወሰን ዐውቀው በይሉኝታ ይቀበሉታል ። ሳይቀበሉት ቢቀሩ መሳፍንቱን ከፋፍለን በምኒልክ ላይ ከማስነሣት ጋር ባለን የተዘጋጀ ኃይል በመጠቀም ፣ በማናቸውም ረገድ የወረራ ዓላማችን እግቡ መድረስ አለበት" የሚል ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱም ፣ ራስ መንገሻ እስኪገቡ ፣ ከፈረንሳይ አገር በነሸፍነ በኩል በሚያስቸኩል ያዘዙት መድፍና የጦር መሣሪያ እስኪደርስ ፣ በመስኮቦች በኩል ተስፋ ያደረጉት ዕርዳታ መጠኑ እስታወቀ ድረስ ነገሩን የዲፕሎማሲ ዘዴ በተሞላበት ለዘብታ አቆዩት ። ራስ መንገሻ ከታላላቅ ስመ ጥር የጦር አለቆች ከራስ አሉላ ፣ ከራስ ወልደ ሚካኤል ፣ ከራስ ሐጎስ ጋር ከገቡላቸው በኋላ ፣ ከፈረንሳይ አገር የሚጠብቁት ዘመናዊ መድፍ ቢደርሳቸውም ፣ አሁንም የርጋታና የትዕግሥት ጠባያቸውን ሳይለውጡ ፣ ለኢጣልያ ባለሥልጣኖች በውጫሌ ውል 17ኛ አንቀጽና በወሰኑ ላይ ያላቸውን የጠጠረ አቅዋም ይገልጹ ገሮመር ። ትራቬርሲ ባለበት የስማቸው ምልክት "ም" ያለበት ከፈረንሳይ አገር የመጣላቸውን 30 ዘመናይ መድፍ ጐብኝተው ሲጨርሱ ፣ "እንግዲህ የመጣው ይምጣ ፤ አይመጣም እንጂ ቢመጣማ በዚህ እናሳየዋለን"[1] ብለዋል ።

ቀጥለውም ከወዳጆቻቸው ከነሙሴ አልፍሬድ ኢልግ ፣ ከነሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ ፣ ከነሙሴ ሽፍነ ፣ ከነሙሴ ሳቩሬ ጋር በጉዳዩ በመመካከር ፣ እንዲሁም በአካባቢያቸው መሳፍንትና መኳንንት በተለይም ከባለቤታቸው ከእቴጌ ጣይቱ ጋር አሳብ ለአሳብ እየተለዋወጡ ፣ አከራካሪዋንና አዋራጅዋን 17ኛ አንቀጽ ራሳቸው ኢጣልያኖቹን እንዲሠርዙ ጠየቁዋቸው ። እነሱም የንግግር ወዝ እየሰጡ ጉዳዩን በማራዘማቸው ፣ በበኩላቸው ምኒልክ መሠረዛቸውን እ.ኤ.አ. በየካቲት 16 ቀን 1893 ዓ.ም. ለየመንግሥታቱ አስታወቁ ። ቢሆንም ዶክተር ትራቬርሲ

1 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ ገጽ 85—86 ።

እነአንቶኔሊ ያበላሹትን በመረቡ ስምምነት የደፈረሰውን የወዳጅነት ግንኙነት ከሥፍራው እመልሳለሁ ብሎ ከመድከም ላይ ይገኛል ።

ነገር ግን ፣ በሮማ ያሉት አዲሶቹ ባለሥልጣኖች ካለፈው መንግሥት መሪዎች ጋር በመስማማት ትራቬርሲ የሠራውን በመንቀፍ ፣ አዲሱንና የወረራ ምኞታችንንም በምኒልክ ዘንድ ለማስቀበል የትራቬርሲ ችሎታውም ፣ አቅሙም ፣ ማዕረጉም ያነሰ ነው በማለት ከርሱ በማዕረግ ከፍ ያለ ሰው እንዲላክ ሲታሰብ ፣ ምርጫው ኮሎኔል ፍሬዲሪክ ፒያኖ ከሚባለው የጦር መኰንን ላይ ወደቀ ። ይኸው መኰንን የኢጣልያ ጦር ምጥዋ ከገባ ዠምሮ ልዩ ልዩ የሰላምና የወታደርነትም ሥራ የፈጸመ ነው ። ገና ባፄ ዮሐንስ ጊዜ ከራስ አሉላ እጅ ለማምለጥና ለስለላ እንዲመቸው ፣ "መሐንዲስ ነኝ እንጂ ወታደር አይደለሁም" ብሎ በሐሰት ተናግሮ እስከ መታሰር ደርሶ ነበር ። ራስ መኰንንም ከሮማ ሲመለሱ አገረ ገዥው ዤኔራል አሬሮ እንዳይቀበላቸው ያደረገው እርሱ ነበረ ። ኮሎኔሉ ወደ ምጥዋ ሲመጣ ነገሩ በምስጢር ሆኖ ስሙና ማዕረጉ በሐሰት ፣ "ኮማንዳቶሬ ባካላሪ አሲያስ የፖስታ እንስፔክተር"[1] ተብሎ ነው ።

እርሱም አዲስ አበባ የገባው ወዲያው ራስ መንገሻ ከንጉሠ ነገሥቱ ልባዊ ምሕረት አግኝተው ፣ ሹመታቸውን አስመርቀውና በኢጣልያ ላይ ቂማቸውን በልባቸው ይዘው ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ ነው ። የኮሎኔል ፍሬዲሪክ ፒያኖ ከኢጣልያ መንግሥት ተልኮ መምጣት ፣ በትራቬርሲ አማካይነት ለንጉሠ ነገሥቱ ተገልጾላቸው ስለነበረ በርሳቸው ግምት ይኸው የጦር መኰንን የ17ኛውን አንቀጽ መሠረዝ የሚገልጽ ደንበኛ የንጉሡን የኡምቤርቶን ማኅተም ይዞ የሚመጣ መስሏቸው ነበር ። ስለዚህም መልካም አቀባበልና መስተንግዶ ተደርጎለት ነበር ።

ኮሎኔሉ በመጣ በዐሥረኛው ቀን ፣ እ.ኤ.አ. ሰኔ 26 ቀን 1894 ዓ.ም ከዶክተር ትራቬርሲ ጋር ሁለቱንም እቴጌ ጣይቱ ባሉበት ንጉሠ ነገሥቱ በቤተ መንግሥታቸው ተቀብለው የሰላምታው ጉዳይ ካለቀ በኋላ ፣ "17ኛውን አንቀጽ እንሠርዛለን እያላችሁ በማነህ ማነህ ነገሩ

1 Gli Italiani in Africa - Angelo del Boca, pp. 500- 507.



እስካሁን እንደዚሁ ተጎተተ ። መሬት አልፋችሁ እስከ መረብ ድረስ ባንዲራችሁን ተከላችሁ" ብለው ወቀሳ በማስቀደም ፣ አሁን ስለነዚህ ዓበይት ጉዳዮች ከመንግሥቱ ወረቀት ይዞ እንደሆን ቢጠይቁት ፣ ከጄኔራል ባራቲዬሪ ተልኮ ስለሁሉም ጉዳይ ለመነጋገር መምጣቱን ገልጾ ክርክር ከተደረገ በኋላ ፣ በመጨረሻ ከመንግሥቱ የተሰጠውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ፣ "በ17ኛው አንቀጽ ለኛ የከለከሉትን የጠባቂነት መብት ለሌላ ኃያል መንግሥት እንደማይሰጡ ቃል ይግቡልንና ይሠረዝ" የሚል አሳብ ወረወረ ። በዚህም የርስ በርስ ውይይት ከተደረገ በኋላ ፣ "ይኸ የኛ ጉዳይ ነው እንጂ ፣ የኢጣልያን መንግሥት የሚያገባው ጉዳይ አይደለም " የሚል ቃል ከእቴጌይቱ ሲወረወር ፣ ንጉሡም ይኸንኑ ሲያጸድቁት ቃሉ ተተርጉሞ ተነገረው ።

ከዚህ ቀጥሎ ኮሎኔሉ አሳቡን ለማስቀበል የሚያነበንበውን ከንቱ ንግግር በጽሞና ካዳመጡ በኋላ የሰጡት መልስ ፣ "መቼ ወዳገርህ ትመለሳለህ?" የሚል ጥያቄ ሆነ ። እርሱም ፣ "ግርማዊነትዎ ሲፈቅድ እመለሳለሁ" አለ ። "መልካም ነው" ብለው ሁለቱንም ለዘለቄታ አሰናበቷቸው ። የልጥ ማረፊያውን ጣቢያ በቤተ መንግሥትና በሌላም የመሐንዲስነት ሥራው በንጉሡ ዘንድ ለጊዜው ሞገስ ያላጣው እንጂኒዬር ሉዊጂ ካፑቺ የሚባለው የኢጣልያ ተወላጅ ተረከበ ። ይኸም መሐንዲስ ወደፊት እንደምናብራራው ዋና የኢጣልያ ሰላይ መሆኑ ተገልጾበት ከመታሰር ደርሷል ። ኮሎኔል ፒያኖና ትራቬርሲም አሳባቸውም ፣ ምኞታቸውም በፍጹም ከሽፎ በሐረር በኩል አድርገው እየተናደዱ ወደ አገራቸው ተመለሱ ። ከሁለቱም የበለጠ ከእንኮበር ዠምሮ በእንጦጦም ፣ በአዲስ አበባም ብዙ ዘመን በመቀመጥ እንደ አንቶኔሊ "የንጉሡንም የመሳፍንቱንም ልብ አገኘሁ ፤ የኢጣልያን ይዞታ በኢትዮጵያ ላይ አጠነክራለሁ" ብሎ ተማምኖ የነበረው ዶክተር ትራቬርሲ ፣ አሁን ከንጉሠ ነገሥቱም ከእቴጌዪቱም ፣ ከቀሩትም ባለሥልጣኖች ከፍ ያለ ተቃውሞ ገጥሞት ባዶ እጁን ወደ አገሩ በሚመለስበት ጊዜ በንዴት እንደ ተሞላ ፣ "አዲስ አበባን ለቅቄ ስሔድ ምኒልክን ከነአገሩ ከነሕዝቡ አቃጥዬው በሔድሁ " ብሎ መመኘቱን በኋላ በጻፈው መጽሐፉ ያረጋግጣል ።

ትራቬርሲ እላይ እንዳልነው ፣ ብዙ ጊዜ ባጠገባቸው ተቀምጦና ጠባያቸውን ተመራምሮ በተረዳው መጠን ፣ ንጉሡን እናታልላለን ባሉ ቁጥር ፍጻሜውን ራሳቸው መታለላቸውን ፣ ከፄ ዮሐንስ ጋር ይዋጉልናል ብለው በመጓጓት መሣሪያ ሰጥተዋቸው ከተቀበሉ በኋላ ላስታርቃችሁ ያሉትን ፣ ወደኋላው ተመልሶ እያመዛዘነ ሁኔታውን ከገመገመ በኋላ ሚላኖ ላይ በ1931 ዓ.ም. ባሳተመው መጽሐፉ እንደዚህ ይላል ።

“ . . . ውስጡን ብንስማማም ፣ ሰጦታም ብንሰጥ ፣ እርዳታም ብናደርግ የምኒልክ ሁኔታ ሁልጊዜ አጠራጣሪና ውልውል ያለበት ነው። በየደብዳቤው ልውውጥ ሁሉ በመካከል ሆኜ ላስታርቅ ፣ በክርስቲያኖች (ኢጣልያና ዐፄ ዮሐንስ) መካከል ደም አይፍሰስ ከማለት በቀር ከዚህ በላይ የሚጨመር ነገር የለም ። በእውነትም ይሁን በሐሰት የሰለሞን ተወላጅ የሚባሉት ራሳቸውን አደጋ ላይ ሳይጥሉ ምቹ ጊዜ ለማግኘት የሚጥሩ ብልህ ዲፕሎማት ናቸው . . . ”

ከዚሁ አያይዞ ፡ አሁን በመጨረሻ ዐፄ ምኒልክ ፣ የኢጣልያን መንግሥትና ራስ መንገሻን ፡ በመሐላ መረብ ላይ የተስማሙትን ፣ አለያይተው ራሱ ትራቬርሲ ለዚህ መለያየት መሣሪያ ሆኖ ለኢጣልያ መንግሥት ምንም ነገር ሳያተርፍ ከኮሎኔል ፒያኖ ጋር ባዶ እጁን መመለሱ እየቆጠቆጠው የተታለለበትን ሁኔታ እንደዚህ ሲል እውነቱን ለመግለጽ ተገደ.ል ።

እኛ የማኪያቬሊ* ተወላጆች የምንባለው የበለጠ በዚህ ንጉሥ ተታለልን ። ጥፋቱም የኛ የቂልነታችንና የእምነታችን ዋጋ ነው ። በፖለቲካ ውስጥ የአሠራር ዘዴ እንጂ የሕሊና ስሜት ዋጋ የለውም ። ያገር ጉዳይ አደጋ ላይ ባለበት ሰዓት ውለታንና ወዳጅነትን ማውራት ባዶ ቃል ነው ።[1]

ብሏል ። ሌላው ቤላቪታ የሚባለው የጦር መኰንን ደግሞ በበኩሉ ፣

ብልህና የሚጨበጥ ነገር ብቻ የሚፈልጉት ምኒልክ አውሮፓውያን በትክክል አሳባቸውን ስለማይገልጹ ፣ እነርሱም የሚያደርጉት ሁሉ ለርሳቸው ጥቅም አለመሆኑን ስለተረዱት ፣ ማናቸውንም በጥርጣሬ እያመዛዘኑ ነገሩን ሁሉ ላልተወሰነ ጊዜ ያስተላልፉት ነበር ። መስኮቦቹም ፣ ፈረንሳዮቹም ፣ እንግሊዞቹም ፣ ጣልያኖቹም የሚሉትን በጥሩ መልክ ያዳምጣሉ ። የሚያደርጉት ግን ለርሳቸው የሚጠቅመውን ብቻ ነው . . . .[2]

ሲል ጽፏል ።

በዚህ አስተያየት ፣ ከትራቬርሲ የበለጠ ቤላቪታ የሚለው ትክክለኛ ነው ። ባለፈው ከምጥዋ ወረራ ዠምሮ እስከ ውጫሌ ውል ድረስ ኢጣልያኖች አንድም ቀን እውነተኛ የወረራ ምኞታቸውን ገልጸው አያውቁም ። ወዳጅ ነን ከማለትና ገጸ በረከት ከማቅረብ በቀር

---

* ኒኮላ ማኪያቬሊ የፌሬንሴ (ኢጣልያ) ተወላጅ ነው ። ፕሪንቺፒ (መስፍኑ) በሚባለው መጽሐፉ ውስጥ “ማናቸውንም አድርገህ (ወንጀልም ቢሆን) ጉዳይህን ፈጽም እንጂ በሃይማኖትና በሕሊና ወይም በይሉኝታ ሰበብ ዓላማህን አትተው” በማለት በፍልስፍና መልክ አቀርቦታል ።

1 Let Marefia - L. Traversi PP. 301—304

2 Adua - Belltavita, P 474.



እውነተኛ አሳባቸውን በትክክል ተናግረው አያውቁም ። ምጥዋን በወረሩ ጊዜ ፣ “በቱርክና ባፄ ዮሐንስ ፈቃድ ነው” ብለው በሐሰት ለሕዝቡ አስታወቁ ። የመሪዎቹንና የሕዝቡን ልብ ለማርጋት ሲሉ ፣ “ኢጣሊያ ወዳጅነትንና ንግድን ከማስፋፋት በቀር መሬት አትፈልግም” ብለው ማወጃቸውን ፣ በዚያው ሰዓት የሐባብንና የቦጎስን ሕዝብ ወይም ካፄ ዮሐንስ የሸፈተውን ሁሉ እያስታጠቁ ፣ መቀስቀሳቸውና ራሱ የውጫሌ ውል 17ኛው አንቀጽ በተንኮልና በማጭበርበር ከስምምነቱ ውል ላይ ሊሠፍር መቻሉ ባለፈው ተገልጿል ።

ስለዚህ ፣ ትራቬርሲ በአባባሉ ኢጣልያ በገርነትና በየዋህነት በምኒልክ ተታለለች ያለው ፍሬ ቢስ ነው ። በመዠመሪያ ላይ በኢጣልያ የተታለሉ ዐፄ ምኒልክ ናቸው ። ተንኮላቸውን በትክክል ከተረዱት በኋላ ግን ፣ እርሳቸውም ተንኮላቸውን በተንኮል በመመለስ በመጨረሻ አሸንፈዋቸዋል ቢባል ትክክለኛ መልስ ይመስለኛል ።

የሆነ ሆኖ የወዳጅነቱም ፣ የፖለቲካውም መስመር ስለ አልተሳካ፣ ገጸ በረከት መበተኑም ከንቱ ሆኖ ስለቀረ ፣ መሳፍንትን አባብሎና አታሎ ማሸፈቱም ስለ አልያዘ ፣ በሁለቱም ወገኖች መካከል ያለው አለመግባባት የሚወሰነው በጦርነት ብቻ መሆኑ ከዕለት ወደዕለት እየታየ መጣ ። ስለዚህም ሁለቱም ወደ ድል ጉዳና የሚመራቸውን የጦር መሣሪያ ያዘጋጁ ዠመር ።

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## የደጃች ባሕታ ሐጐስ ከኢጣልያኖቹ ጋር በኃይላ ተዋግተው መሞት

ራስ መንገሻ ፣ አዲስ አበባ ላይ ከንጉሠ ነገሥቱ ታርቀው ፣ ከእቴጌ ጣይቱና በፊት ከማያውቋቸው መኳንንትና መሳፍንት ከነራስ ዳርጌ ጋር ተዋውቀው በክብርና በደስታ ከሰነበቱ በኋላ ፣ በሰኔ 7 ቀን 1886 ዓ. ም. ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰናብተው ፣ ወደ አገራቸው በሚጓዙበት ጊዜ በየሠፈሩበት መጥን (መብልና መጠጥ) እየታዘዘ ግብሩ ሳይጐድል እስከ ወሎ ደረሱ ። በወሎና በየጁ ሲያልፉም ፣ የራስ ሚካኤልና የራስ ወሌ ሰው እያስተናገደ በክብር እስከ ግዛታቸው እስከ ትግራይ አደረሰ ።

ምንም እንኳን ዝርዝሩ ተጽፎ ባይቆየን ፣ ከኢጣልያ ጋር ጦርነት በምንም አኳኋን እንደማይቀር በመገመት ፣ ንጉሠ ነገሥቱና ራስ መንገሻ በግልጽም ፣ በስውርም የተወያዩበት ነገር እንደሚኖር አይጠረጠርም ፡ ከዚህ መካከል እንደኛው ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ክሪስፒ የኢትዮጵያን መሳፍንት ከምኒልክ ለመለያየት እንደ ተመኘው ዓይነት ፣ ራስ መንገሻና ዐፄ ምኒልክም በኢጣልያ ውስጥ ያሉትን መኳንንትና የባንዳ አለቆች በተቻለ መጠን ለማስከዳት አሳብ እንደሚኖራቸውና እንደ ተነጋገሩበት አይጠረጠርም ።

ስለዚህ ፣ ራስ መንገሻ ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ ፣ ክሪስፒ የላከበትንና እርሱም አምኖ የተቀበለውን የማስከዳት መመሪያ ወደ ፍጻሜ ለማድረስ በዠኔራል ባራቴዬሪ የበላይ መሪነት ፣ ዓድዋ ተቀማጭ የሆነው የኢጣልያ የፖለቲካ ወኪል ቴኔንቴ ሙላዚኒ ራስ መንገሻ አሉበት መቀሌ ድረስ እየመጣ ጠብ እርግፍ እያለ ልባቸውን ለማግኘት ደጅ ይጠና ነበር ። እርሳቸውም ለርሱ ፊት ሳይነሡ በበኩላቸው በነርሱ ውስጥ ከብዙ ጊዜ ዠምሮ የሚያገለግሉትን እንደነ ደጃች ባሕታ ሐጐስ ያሉትን ውስጥ ለውስጥ እየተላላኩ ለማስከዳት ይጣጣሩ ጀመር ።

ባሁኑ ጊዜ ፣ ከኢጣልያኖች ጋር ካሉት ዓይነተኛ መኳንንት መካከል ደጃች ሐጐስ ተፈሪና ደጃች ባሕታ ሐጐስ ይገኛሉ ። ራስ መንገሻ ከኙሁ ከደጃች ባሕታ ሐጐስ ጋር ውስጥ ለውስጥ በተላላኩት

መሠረት ባሕታ ከኢጣልያኖች ጋር ሲዋጉ የሞቱበት ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

ደጃች ባሕታ ሐጐስ የአካለ ጉዛይ ተወላጅ ናቸው ። በአምባ ጓሮ የትልቁን የራስ አርአያን ልጅ አምባዬን ከገደሉና ከሸፈቱ ወዲህ በፊት ከደጃች ደብብም ፣ ከራስ መንገሻም እየተጣሉና እየተዋጉም በሐባብ በረሃ ይኖሩ ነበር ። በመጨረሻ ለኢጣልያኖቹ ገብተው የባንዶች አለቃ በመሆን ብዙ ጊዜ ዋና መቀመጫቸውን አከለ ጉዛይ አድርገው ለኢጣልያኖቹ ሲያገለግሉ ኖረዋል ። እዚያ በሚገኙት የላዛሪስት ሚስዮን አግባቢነት እርሳቸውም ፣ ቤተሰባቸውም ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ገብተዋል ። በማናቸውም አንድነታቸውን ከኢጣልያኖቹ ጋር ስለ መሠረቱ ፣ እነርሱም ከኢጣልያኖቹ በታች ከሐበሾች በላይ አድርገው በከበሬታ ይዘዋቸው ነበር ። ኢጣልያኖች በመገናኘሪያው ጊዜ ደጃች ደብብንና ደጃች ባሕታን ባንድነት አስማምተው በሁለቱም መኳንንቶች ለመጠቀም እንደ ፈለጉ የታወቀ ነው ። ዳሩ ግን ደጃች ደብብ ከወንድማቸው ከደጃች አምባዬ ገዳይ ጋር መስማማት ስለማይሆንላቸው ፣ በዚህም ላይ ሁለቱም ከመረብ ወዲያ በተለይ የአከለ ጉዛይን ግዛት ስለሚፈልጉና በዚሁ ስለሚዋጉ ፣ ሁለቱን አስማምቶ ወደፊት ኢትዮጵያን ለመውረር ለወጠኑት አሳብ መሣሪያ ለማድረግ ለኢጣልያኖቹ አልተሳካላቸውም ።በመጨረሻም ደጃች ደብብ ከኢጣልያኖቹ ከሸፈቱና ዐፄ ዮሐንስም ከሞቱ በኋላ ፣ ኢጣልያኖቹ ደጃች ባሕታ ሐጐስን አቅፈው በማናቸውም እያስደሰቱ በርሳቸው መሪነት ካሉበት ቦታ ወደፊት እየገፉ ሰገነይቲንና አካባቢውን ሁሉ ያዙ ። በሰገነይቲም ቲኔንቲ ሳንጉይኔቲ የሚባለውን ሾመው የደጃች ባሕታም ግንኙነት ከዚሁ ከቲኔንቲው ጋር ሆኖ የርሳቸውም መደበኛ ሥፍራ ይኸው ሰገነይቲ ሆነ ።

ይሁን እንጂ ፣ በመጨረሻ ኢጣልያኖች እያደር አገር እየያዙ ፣ የአገር ተወላጅን እያዋረዱ ፣ ክብርንና የበላይነትን ለኢጣልያኖች ብቻ ሲሰጡ በመመልከት ልባቸው ከኢጣልያኖች ሸፈተ ። ባለፈ ሥራቸውም መጸጸት ጀመሩ ። ከዕለታት አንድ ቀን ፣ ኢጣልያኖቹ አንዱን ኢትዮጵያዊ አስተኝተው ሲገርፉት እዚያው ነበሩና በልባቸው እየተናደዱ ፣ "የሀገሬ ሰው እንደዚህ እየተዋረደ ከማየው ሞት ይሻለኝ ነበር" ብለው አጠገባቸው ለቆሙት ተናገሩ ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ፣ ራስ መንገሻም ተስማምተው ኢጣልያን ለመውጋት የሚዘጋጁበት ጊዜ መሆኑን ያውቁ ስለነበረ ፣ ላዩን ከኢጣልያኖች ጋር ሆነው ውስጥ ውስጡን ከራስ መንገሻና በርሳቸው አማካይነት ካፄ ምኒልክ ጋር ይላላኩ ጀመር ። የዚህንም ምስጢር



ኢጣልያኖቹ በመጨረሻው ሰሙት ። ከዚያ ፣ "አዘንግተን ይዘን ወደ አሰብ ልከን እናስረዋለን" እያሉ ተመካከረው ወሰኑ ። ጣልያኖች የደጃች ባሕታ ሐጐስን አሳብ ከሰላዮቻቸው እንዳገኙት ሁሉ እንደዚሁም ባሕታ ሐጐስ የነሱን ምክር ባንድ ያገር ተወላጅ ካቶሊክ ወዳጃቸው በኩል ተገነዘቡት ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ፣ ኢጣልያኖቹ አላይ ስሙ የተጠቀሰውን ያገር ልማድና ባህል የሚያውቀውን ቲኔንቲ ሳንጉይኔቲ የሚባለውን በሰገነይቲ ሬዚዲንቲ (ምስለኔ) አድርገው በሹመት አስቀምጠው ነበር ። የርሱም አስተርጓሚ ስመ ጥሩው ገብረ እግዚአብሔር ነበሩ ።*

ስለዚህ ፣ ደጃች ባሕታ ሐጐስ ፣ ብዙ ጊዜ ካስተርጓሚው ከገብረ እግዚአብሔርና ከዚሁ ከምስለኔው ከቲኔንቲ ጋር የሥራና የወዳጅነት ግንኙነታቸውን በሚቀጥሉበት ጊዜ ፣ "ኢጣልያኖቹ ሳይቀድሙኝ ልቅደማቸው" ብለው እ. ኤ. አ. ታኅሣሥ 14 ቀን 1894 (ታኅሣሥ 5 ቀን 1887 ዓ.ም.) የተለመደ ጉብኝት አስመስለው ወንድማቸውን ደጃች ሠንጋልንና ባሻ ተሱ (ተስፋ) የሚባለውን ሹማቸውን አስከትለው ወደ ሳንጉይኔቲ መኖሪያ ቤት ሔደው የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጡ ፣ በኋላ መጠጥ ቀርቦ ጭውውት ተጀመረ ። ከዚያ ባሕታ ሐጐስና ሠንጋል ፣ የኢጣልያኑን ሹም ሳያስብ በድንገት ያዙትና ተናንቀው አስተኙት ። እሱም ለመንጠቅ ሲፍጨረጨር ባሕታ ሐጐስ ደረቱን ከመሬት ጋር በጉልበታቸው ይዘው እጆቹን በእጆቻቸው እንደጨበጡ ያኛው ከሥር ዐይኑን አፍጦ ፣ "ኢጣልያ ታላቅ ናትና እግዚአብሔር ሳይቀጣህ አይቀርም" ቢላቸው ፣ እርሳቸውም ከላይ ሆነው ፣ "ኢትዮጵያ ደግሞ ከኢጣልያ የበለጠች ታላቅ ናት" ብለው መለሱለት ። በዚህ ጊዜ ገብረ እግዚአብሔር በሩጫ ደርሰው ሳንጉይኔቲን ለማስጣል ወይም ለመገላገል ሞክረው ነበር ።ነገር ግን ወዲያው አስቀድሞ እንደ ታሰበው የደጃች ባሕታ ሐጐስ አሽከሮች ገብተው ምስለኔውን ከደጃች ባሕታ እጅ ተቀብለው ፣ ወደ ውጭ አውጥተው ፣ እጅና እግሩን አስረው ባንድ ቤት አስቀመጡት ።

በዚህ ጊዜ በደጃች ባሕታ ሐጐስና በገብረ እግዚአብሔር መካከል በሳንጉይኔቲ መታሰር የተነሣ ክርክር መነሣቱን ደሎሊባር እንደዚህ ሲል ጽፎታል ።

---

* ገብረ እግዚአብሔር ከዓድዋ ጦርነት ወዲህ በኢትዮጵያ አፍቃሪነት ተጠርጥረው እንደ ታሰሩ ከታሰሩበት ከናኩራ አምልጠው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ናቸው ። ብላታ ተብለው በፊት ላፄ ምኒልክ ቀጥሎም ወደ ሐረር ሔደው ከራስ መኰንን አማካሪዎች አንዱ ነበሩ ።

ገብረ እግዚአብሔር—ይህ የሠራኸው ሥራ መልካም አይደለም ።”

ደጃች ባሕታ ሐጐስ— . . . የኔን ሥራ አንተ ትነቅፈው እንደሆነ እንጂ ፤ ሥራዬስ ደንበኛ የፍርድና የበቀል ሥራ ነው ። ይኸም በኔ ብቻ ሳይወሰን አገሩ ሁሉ ባንድነት ተነሥቶ እነዚህን የሰው አገር ነጣቂዎች ካገራችንና ከምድራችን ሳናስወጣቸው አንቀርም ። እኛንም ራስ መንገሻና ራሳቸው ምኒልክ የአሣውርታና የደርቡሾች ተወላጅ ሁሉ ይደግፈናል ። ብረት የያዘው ያገር ተወላጅ አሽከር ከነመሣሪያው ሲዞር ኢጣልያኖችን አጥፍተን የአገራችን ጌታ እኛው እንሆናለን ። ስለዚህ አንተም ከኛው ጋር ሁን ፤ ከፈረንጆች ጋር በመኖር ባገኘኸው ሥልጣኔ ታገለግለናለህ ፤ እኔም ፈረስና የጦር መሣሪያ ጨምሬ የበታች ሹም አደርግሀና ያሰብኸውን ከፍተኛ ደረጃ ታገኛለህ ።

ገብረ እግዚአብሔር—“አላደርገውም እነዚህን መልካም ያደረጉልህን አንተ እንደ ከዳኻቸው እኔ አላደርገውም ። ካፒታኖ ቤቲኒ ለኔ እንዳባቴ ነበር ። ሌሎችም ሹማምንት ሁሉ ለኔ በጎ ያደረጉልኝ ወዳጆቼ ናቸውና አሁንም በሕይወቴ እሰሁ ድረስ ቴኔንቲን (ሳንጉይኔቲን) አልለየውም ።”

ደጃች ባሕታ ሐጎስ—“እንግዲያውስ ከኛ ጋር መሆን ካልፈቀድህ በነገሩ አትግባ ፤ የዠመርነውን እኛው እንወጣዋለን ፤ አንተ ግን እርጊት የታወረች እናት በአሥመራ አለህና ከበቅሎዎቹ አንዲቱን ተቀምጠህ የምሰጥህን ገንዘብ ለናትህ ውሰድላትና ከርሷ ጋር እዚያው ተቀመጥ ።”

ገብረ እግዚአብሔር—“ቴኒንቲ ሳንጉይኔቴን ካልለቀቅኸው አልሔድም ።”

ደ. ባሕታ—“በፍጹም እርሱ አይለቀቅም ።”

ገብረ እግዚአብሔር—“እንግዲያውስ እኔም ከርሱ አልለይምና አብረህ እሰረኝ ፤ ብትገድለውም እኔ ልቀብረው እፈልጋለሁ ።”

ደ. ባሕታ — “ራስህ እንደ ብረት ጥጥር ነው ። ደግ ነው አስርሃለሁ ።”

ብሎ ባንድ ቤት ውስጥ ለብቻው አሰረው ፤ በማግሥቱ አስጠራና ጠጅ ከፊቱ አቅርቦ ፤ ቢጠይቀው “ትላንት የነገርኩህን አሁንስ አላሰብህበትምን” ብሎ “ትናንት ከመለስሁልህ የተለየ ሌላ መልስ የለኝም” ብለው ገብረ እግዚአብሔር በአሳባቸው መጽናታቸውን ጸሐፊው ያመለክታል ።

ከዚህ በኋላ ገብረ እግዚአብሔር ፤ እዚያው ቴኔንቲ ሳንጉይኔቲ ዘንድ ይታሰሩ ተብለው እንደሔዱ ፤ የታሰረውም ጣልያን ባያቸው ጊዜ አንገታቸው ላይ ወድቆ ሳማቸው ። ከዚያም አብረው ሳሉ የጣልያኑን መታሰር አይተው ፤ “እንዴት ሳይሰርቅ እንደ ሌባ ይታሰራል” ብለው ከአሳሪዎቹ ጋር ተከራክረው በኋላም ወደ ደጃች ባሕታ ተላልከው (የእግር ብረት) እስራቱን አስቀሩለት ።



ደጃች ባሕታ ፤ በሰገነይቲ የኢጣልያ መንግሥት ያስቀመጠውን ምስለኔውን ቲኔንቲ ሳንጉይኔቲን ከሦስት የስልክና የቴሌግራም ሠራተኞች ጋር አሰሩ ። ሰገነይቲን ከአሥመራና ከምጥዋ ጋር የሚያገናኘውን የስልክ መስመር በጣጠሱ ። በቶሎ ወደ ዓድዋ መጥተው ከራስ መንገሻ ጋር በመደባለቅ ፈንታ ከገብረ እግዚአብሔር ጋር እየተከራከሩ በሰገነይቲ ውለው አደሩ ።

በዚህ ጊዜ ፤ በኤርትራ የኢጣሊያ ጦር ዋና አዛዥ ጄኔራል ባራቲዬሪ በከረን ይገኝ ነበርና ፤ እ. ኤ. አ. ታኅሣሥ 15 ቀን 1894 ዓ. ም. “ከሰገነይቲ የሚያገናኘው የስልክ መስመር ተቋርጧል” ማለትን በሰማ ጊዜ ፤ “ ነገሩ የስሕተት ይሆን ወይስ ተበላሽቶ ይሆን” እያለ ከሹማምንቱ ጋር እየተነጋገረ ሲወያይ ፤ ሁሉም “ነገሩ ምን ይሆን ?” እያለ ሲጨነቅ ፤ በመጨረሻ የባሕታ መክዳትና የሳንጉይኔቲ መታሰር ወሬው በትክክል መጣለት ።

ከዚህ በኋላ ፤ አሥመራ የሚገኘው ማዦር ቶዜሊም ጦሩን ከአሥመራ ወደ መሕረባ ይዞ መጣ ። ይቺ መሕረባ የምትባል መንደር ለሰገነይቲ ቅርብ ነበረችና ቶዜሊ በዚች መንደር ገብቶ ከአሥመራ የሚያገናኘውን የስልክ መስመር አስቀጥሎ ሌላ ጦር እንዲጨመርለት እየተጠባበቀ ፤ ባንድ ወገን ደግሞ ተጨማሪው ጦር እስኪደርስለት ድረስ “ቴኔንቲ ሳንጉይኔቲንና ሦስቱን የቴሌግራምና የስልክ ሠራተኞች መልሰልኝና እንስማማ ” የሚል መላክተኛ ወደ ደጃች ባሕታ ላከ ። ይኸንም ማለቱ ተጨማሪው ጦር ከደረሰለት በኋላ ፤ በድንገት አዘንግቶ ደጃች ባሕታን ወግቶ ለመያዝ እንጂ ፤ በእውነቱ እስረኞቹን ቢልኩለት ለመስማማት ወይም ነገሩን በዚሁ አቁሞ ደጃዝማቹን በሰላም ለመተው አልነበረም ።

ደጃች ባሕታ በበኩላቸው ፤ ወደ ራስ መንገሻ እንዲደርሱላቸው ወይም ረዳት ጦር እንዲመጣላቸው እየተላላኩ ለርሱ አወላዋይ መልስ ሰጡ ። በመካከሉ የርሱን ጦር ይዞ መጠጋት በሰሙ ጊዜ ፤ እስረኞቹን ለራስ መንገሻ ለመላክ አስቀድመው እርሳቸው ሰገነይቲን ትተው ከያለበት የተሰበሰቡትን 1600 የሚያህል ጦራቸውን እንደያዙ በሰገነይቲ አቅራቢያ የሚገኘውን በሐላይ ያለውን የኢጣልያኖቹን ምሽግ ለመውጋትና ለመያዝ ጉዞ አደረጉ ። በዚያም እንደ ደረሱ ካፒቴን ካስቴላዚ ከነጭፍራው መሽጐ የተቀመጠበትን ቅጥር አስከበበው ፤ “ የያዝኸውን የጦር መሣሪያና ዕቃ አስረክበኝና በነጻነት ከነሰዎችህ እንድትሔድ ልፍቀድልህ ” ብለው ላኩበት ። ካፒቴኑም ከውጭ የሚጠብቀው የቶዜሊ እርዳታ እስኪደርስለት ድረስ አጠገቡ ባሉት በአገር ተወላጅና በውጭ አገር ሚሲዮኖች ካቶሊኮች አማካይነት

“እርሱ ከነሰዌ ካልነካኝ እኔም መሣሪያውንና ዕቃውን አስረክበዋለሁ”
ብሎ ወደ ደጃች ባሕታ ላከ ። እርሳቸው ም እውነት የሚያስረክብ መስ
ሎአቸው ከሰዎቻቸው ውስጥ ደህና ደህናውን መርጠው ላኩለት ።
እነርሱም ወደ ቅጥሩ ውስጥ እንደገቡ ካፒቴኑ እጅ እጃቸውን እየያዘ
በሰንሰለት አሳሰራቸው ።

ከዚህ በኋላ ፣ የነርሱን አለመመለስና የካፒቴኑን ክዳት በተረዱት
ጊዜ ፣ ደጃች ባሕታ በቅጥሩ ላይ ተኩስ ገምረው ከውስጥም ያሉት
መልሰው እየተኮሱ ደንበኛው ጦርነት ተገመረ ።ከሰባት ሰዓት እስከ
ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በቀጠለው ተኩስ ባሕታ ሐጐስ አሸንፈው ቅጥሩን
ለመጣስና ለመግባት ሲያስቡ ፣ የተኩሱን ጩኸት ይሰማ የነበረው
ማገርር ቶዜሊ በሩጫ እየገሠገሠ ከነጦሩ በድንገት ደረሰና ደጃች ባሕታ
ሐጐስን ከኋላቸው እየተታኮሰ ይወጋቸው ገመር ። ደጃች ባሕታም
ምንም እንኳን ከኋላ በማገርር ቶዜሊ ፣ ከፊታቸው በካፒቴን ካስቴላዚ
በሁለት ወገን በሁለት ጦር መካከል ቢሆኑም ፣ ባሉበት ሥፍራ ሆነው
በቆራጥነት እየተታኮሱ ከሰዎቻቸው ጋር 11 ሰው ገድለው 20 የሚሆ
ሆኑ አብዛኞቹን ያገር ተወላጆች ወታደሮች ከአቆሰሉ በኋላ በመትረ
የስ ሩምታ ተኩሰው ጣሉዋቸውና ሞቱ ።[1]

ምናልባት ፣ በኢጣልያኖች ዘንድ እንዳለው የመሰለ የስልክና የመ
ገናኛ ድርጅትና ግንኙነት በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ቢኖር ኖሮ
በወዲያ ማገርር ቶዜሊ በፍጥነት ለካፒቴን ካስቴላዚ እንደ ደረሰለት
ሁሉ ፣ ራስ መንገሻ ወይም አንድ የጦር መኮንናቸው ወደ ምሽጉ በግ
ሥጋሜ ይደርሱ ነበር ።አገርና ወገን ወዳድ የሆኑት ደጃች ባሕታ ሐጐ
ስም ፣ በዚህ ዓይነት አሳዛኝ ሞት አይሞቱም ነበር ። ከሁሉ የበለጠ
ደግሞ የሚያሳዝነው ፣ ባሕታ ሐጐስ ከሞቱ በኋላ ቶዜሊ ሬሳቸው እን
ዳይቀበር ከልክሎ ለቀሩት መቀጣጫ ወይም ምሳሌ ይሆናል ብሎ
ያደረገው እብሪት ጨርሶ የሚያበሳጭ ነው ።

ይኸ ሁሉ ሲሆን ፣ ራስ መንገሻ ከአዲስ አበባ ተመልሰው በዓድ
ዋና በመቀሌ እየተዘዋወሩ ፣ ከደጃች ባሕታም እየተላላኩ ግዛታቸውን
ሲያጸኑ ቆይተዋል ። ደጃች በሕታና ማገርር ቶዜሊ ሐላይ ምሽግ በሚ
ዋጉበት ጊዜ እርሳቸው እንትጮ ነበሩ ። ምንም እንኳን ውስጡን ከደ
ጃች ባሕታ ሐጐስ ጋር በደብዳቤና በመልእክት ንግግር ቢኖራቸውም ፣
ላዩን እስከ ኮዓቲትና ሰንዓፌ ጦርነት ድረስ ከኢጣልያኖች ጋር በጉ
ርብትና ለመኖር የወዳጅነት መልክ የማሳየት ፖለቲካ ነበራቸው ።

---

1 Douze ans en Abissinie - Paul de Lauribar, Chap. 26 PP. 338 - 394 -; Gli Italiani in Africa Orientale - A. Del Boca, PP. 521 - 529.



ካዲስ አበባ ሲነሡም ፣ እኛ እስክንመጣ ድረስ ተዘጋጅ እንጂ ጦርነት
አትገምር የሚል ያፄ ምኒልክ ትእዛዝ ያለ ይመስላል ። ራሳቸውም
ባለፈው ዓመት ጣልያኖቹ መረብ ላይ በመስቀልና በወንጌል የተማ
ማሉትን መሐላ ስለ አፈረሱባቸው ፣ ቂማቸው ገና ያልበረደ ሳይሆን
አይቀርም ። ስለዚህም አዲስ አበባ ከንጉሠ ነገሥቱ እንደ ተስማሙ ፣
ከደጃች ባሕታ ጋር ውስጡን እየተላላኩ አሁንም እንትጮ ላይ ሆነው
ጣልያኖቹን ለመውጋት ወታደርና የጦር መሣሪያ ማደራጀት ላይ
ይገኛሉ ። ያለዚያ ግን ፣ ከዚሁ ጦራቸው ከፍለው ለደጃች ባሕታ ልከው
ቢሆን ኖሮ የሐላይ አሸናፊነት ለርሳቸው ይሆን ነበር ። ደጃች ባሕታ
ንም ከነሰዋቸው ሲያገኙ ወደፊት ለሚያደርጉት ለኮዓቲት ጦርነት
ያግዙዋቸው ነበር ። ነገር ግን ፣ እላይ ከጠቀስነው ከመገናኛው ጉድ
ለት በቀር ሌላውን በዚያን ጊዜ የነበራቸውን ችግር ዛሬ ማወቅና መፍ
ረድ አይቻልም ። የራስ መንገሻን ሁኔታ በዚህ ዓይነት ስንመለከት
እንደዚሁም የቲኔንቲ ሳንጉይኔንቲንና ያስተርጓሚውን የብላታ ገብረ
እግዚአብሔርን ፍጻሜ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን ።

ሰገነይቲ ላይ ምስለኔው ሳንጉይኔቲና ሦስቱ ስልከኞች እንደታ
ሰሩ ፣ በደጃች ባሕታ ሐጐስ ትእዛዝ ሹማቸው ባሻ ተስፋ ማርያም
ዐርባ የሚሆኑ ጭፍሮችን እንደያዘ እስረኞቹን ይዞ ለራስ መንገሻ
ለመስጠት ወደ እንትጮ ይጓዝ ነበር ። በመንገድም ኢጣልያኖቹ ምንም
የልብስና የጫማ ፣ የራብና የጥም ችግር ቢደርስባቸውም ፣ ጣልያኖ
ቹን ለማገልገል ቁርጠኛ የሆኑት ገብረ እግዚአብሔር በማናቸውም
ከባላገርም ፣ ከዘበኞቹም እየለመኑ ፈረንጆችን እያበሉና እያጠጡ ጉዞ
ቸውን ይቀጥሉ ነበር ። በጉዞውም ጊዜ ገብረ እግዚአብሔር ዘበኞ
ቹን አባብለው ወይም ሌሊት በተኙበት ጊዜ የሚወዱት ሳንጉይኔቲ
የሚያመልጥበትን መንገድ ሲፈልጉለት ነበር ይባላል ። ነገር ግን ፣ ከዕ
ለታት አንድ ቀን ጉዞቸውን በሚቀጥሉበት ጊዜ ፣ ገብረ እግዚአብሔር
የራስ መንገሻና የደጃች ባሕታ ሐጐስ ሰው መስለው ፣ የባላገር ወሬ
ሲጠያይቁ የሐላይን ጦርነት ፣ የደጃች ባሕታን መሞት እርግጠኛውን
ሰሙና ለሳንጉይኔቲ ነገሩት ። እርሱም ይኸንኑ በሰማ ጊዜ ፣ “ የባሕ
ታን ሞት ከሰማሁ በኋላ ከእንግዲህ ወዲያ እኔ ብሞት ግድ የለኝም።
ይልቅስ እናንተ በኔ ምክንያት ጉዳት እንዳይደርስባችሁ በየአገራችሁ
ተመለሱ ” ብሎ እነ ገብረ እግዚአብሔርን መከራቸው ። ነገር ግን
አንድ ጊዜ ከሰገነይቲ ገምሮ ከርሱ ላለመለየት የቆረጡበት ነገር
ነውና ፣ በዚሁ በገመሩት ሃይማኖት ጸንተው ፣ ነጻው ሰውዬ ከእስረ
ኛው ጋር አብረው ጉዞቸውን ቀጥለው ፣ ማታ ከሰፈር ላይ ዘበኞቹን
ተሰብሰቡልኝ ብለው እንደዚህ አሏቸው ። “እስረኞቹን ወስዳችሁ ለራስ
መንገሻ ለመስጠት ማሳባችሁ ሞኝነት ነው ። ምክንያቱም ራስ መንገሻ

የኢጣልያኖች ወዳጅ ስለሆኑ፤ ከናንተ የተቀበሉትን እስረኛ መልሰው የሚያስረክቡዋቸው ለኢጣልያኖቹ ነውና በዚህ እናንተን የሚያመሰግናችሁ የለም ። ይልቅስ እናንተው ራሳችሁ መልሳችሁ ለኢጣልያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ብትሰጧቸው ምስጋናም ዋጋም ታገኙበታላችሁ ።”

የዘበኞቹ አለቆች ይኸን ከሰሙ በኋላ፤ ምንም እንኳን ምክሩ በልባቸው ቢገባ ለጊዜው እሺ ሳይሉ እንደዚሁ ነገሩን እያመዛዘኑ ቆይተው፤ ሌሊትም ብርድ ነበርና እሳት ነዶ እየሞቁ ተጋድመው ሳለ፤ የዘበኞቹ ሹም ባሻ ተስፉ ገብረ እግዚአብሔርን ለብቻቸው ጠርቶ የኢጣልያ መንግሥት በኛ ላይ ክፉ እንዳያደርግብን ሳንጉይኔቲ በመስቀልና በወንጌል ይማልልንና ወደ ሰገነይቲ ተመልሰን ከወገኖቹ ጋር እንደባልቀው” ብሎ ነገራቸው ። እርሳቸውም ይኸንኑ ነግረው ምስለኔው እሳቡን በደስታ ተቀብሎ ቃሉን በመሐላ ከሰጠ በኋላ፤ በመጡበት መንገድ በችግርና በድካም እንደገና ወደ ሰገነይቲ ተመልሰው፤ ሳንጉይኔቲ ከወገኖቹ ተደባልቆ በዚያው ዓመት በኮዓቲት ላይ በራስ መንገሻና በኢጣልያኖች መካከል ጦርነት የተደረገ ዕለት ሲዋጋ ሞተ ። ገብረ እግዚአብሔር ግን፤ እስከ ዓድዋ ጦርነት ድረስ ኢጣልያኖቹን በአዲኳላም፤ በአሥመራም በአስተርጓሚነትና በምክር ሲያገለግሉ ኖሩ ። የዓድዋ ድል ከተፈጸመ በኋላ፤ ሬሳ ለማስቀበር የቅድሚያ ፈቃድ ለመጠየቅ ማዦር ቶማሶ ሳልሳ ወዳጼ ምኒልክ ሰፈር የመጣ ጊዜ አብረው ለአስተርጓሚነት መጥተዋል ።

በመጨረሻ ግን፤ እያደር ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ኢጣልያኖቹን የመጥላት፤ አገራቸውን ኢትዮጵያን የመውደድ ስሜት ስላደረባቸውና ስለታየባቸው ተጠርጥረው በናኩራ ደሴት ታሰሩ ። ከዚያም ከጓደኛቸው ከአቶ ኢያሱ ዳንኤል ጋር ከናኩራ አምልጠው ወደ አዲስ አበባ መጥተው ጥቂት ጊዜ ለንጉሠ ነገሥቱ መካር ሆነው ከቆዩ በኋላ፤ ቀጥሎ ወደ ሐረርጌ ተዛውረው በአማካሪነት ሲሠሩ ኖረው ሞቱ ።



## ምዕራፍ ዐሥራ ስምንት

### በኢትዮጵያ የተሠራጨው የኢጣሊያኖች የስለላ ሥራ

በኢጣልያ ንጉሡም፡ ባለሥልጣኖቹም፤ የጦር መኮንኖቹም ጭምር እ.ኤ.አ. በ1860 ዓ.ም. የአገራቸውን አንድነት መመሥረታቸው ይታወቃል ። በፊት በአውስትሪያ ውስጥ ሲገዙ፤ የጀርማኒክን ሥልጣኔ በመውረስ ከኢጣልያንኛው ጋር አዋህደው የያዙ ነበሩ ። በኋላም ወደ ወገኖቻቸው ወደ ኢጣልያ ገብተው ከአውስትሪያ ጋር በተደረገው ጦርነት የተካፈሉ ስለ ነበሩባቸው፤ ባሁኑ ጊዜ ያገኙት የነጻነት ስሜትና ያገር ፍቅር እያቃጠላቸው በማናቸውም ግንባር አገራቸውንና መንግሥታቸውን የሚያገለግሉት ባዲስ ያገር መውደድ መንፈስና በጋለ ስሜት ነው ። የጠፋ ዕቃ መልሶ ሲገኝ ከመጥፋቱ በፊት ከነበረው ከባለቤትነት ስሜት የበለጠ ደስታ እንደሚሰማ፤ ኢጣልያኖችም ባሁኑ ሰዓት ደስታቸው የዚያን ያህል ነው ። ሁኔታው እኛ ኢትዮጵያውያን ነጻነታችን (1928—33 ዓ. ም.) ለአምስት ዓመታት ተጽዕኖ ሥር ወድቆ በ1933 ዓ.ም. ከዚህ በተላቀቅንበት ጊዜ ከነበረን የጋለ የሥራ ናፍቆትና ያገልግሎት ስሜት ጋር የሚመሳሰል ነው ።

ስለዚህ፤ አዲስ የተቋቋመው የኢጣልያ መንግሥት፤ በኢትዮጵያ ላይ መስፋፋትን መሠረታዊ ዓላማ አድርጎ ሲነሣ ከሁሉ አስቀድሞ በአገሪቱ በየአውራጃው ባሉት መሳፍንት ዘንድ፤ ባገር ጕብኝነትና በንግድ እያስመሰለ ሰላዮችን ያስቀምጥ ነበር ። ለዚህም ሥራ አብዛኛውን ጊዜ የሚመረጡት የሕክምና፤ የመሐንዲስነት ወይም ያናጢነት ዕውቀት ያላቸው ነበሩ ። ኢትዮጵያ እንደ ሌላው የአፍሪካ አገር ዘመናዊ ሥልጣኔ ያልገባባት፤ ሕዝቧ በበሽታ የሚሠቃይና መታከምን የሚፈልግ፤ በሕንፃ ቤት መኖርንና ወንዝን በድልድይ መሻገርን የሚፈልግ ነበር ። ነገር ግን፤ አገሪቷ ራሷ መሥራት የማትችል ስለሆነች ሰላዮች በሕክምና ወይም በመሐንዲስነታቸው ሰበብ ወደ ነገሥታቱና ወደ መሳፍንቱ ከተጠጉ በኋላ፤ ወዳጅነት ቋጥረው ወጭ ገቢና ባለሟል በመሆን የተላኩበትን የስለላ ሥራ ለማከናወን እንደቻሉ ቀደም ሲል ተወስቷል ።

እነዚህም፤ ዐፄ ዮሐንስ ዘንድ የነበረው የመቀሌን ቤተ መንግሥት የሠራው ናሬቲ ገርሴፔ የተባለው አናጢ፤ ወደ ዐፄ ምኒልክ የተላኩት

ሊዎፖልድ ትራቬርሲና ቬንቼንሶ ራጋሲ ሐኪሞች ፥ አውጉስቶ ሳልም
ቤኒና ሊዊጂ ካፑቺ መሐንዲሶች ናቸው ። በተለይ ራስ መኰንንን ካፄ
ምኒልክ ለማስከዳት የተላከው ማዦር ቺዛሬ ኔራሲኒ ሐኪም ሲሆን
ፒዬትሮ ፌልተር ነጋዴ ነው ። እንዲሁም ለራስ መንገሻ የተላከው
አንጀሎ ደ ማርቲኖ ሐኪም ነው ። ሐኪም ወይም መሐንዲስ ባይሆ
ንም ፥ አገሌ የእገሌን አውራጃ ባህልና ቋንቋ ያውቃል ፥ ከዚያ ወረዳ
መስፍን ወይም መኰንን ጋር ተወዳጅቷል ሲባል ወደዚያ አገር
ይመደባል ። ለምሳሌ ፥ ካፒቴን ሳልቫቶሬ ፒርሲኮ የዐረብኛ ቋንቋና የእስ
ላሞችን ባህል ያውቃል ተብሎ አውሳ ወደ መሐመድ አንፋሪ ዘንድ
ተልኮ ነበር ። እርሱም ከአውሳ ወደ ዋጀራት ወደ ራያና ወደ አዘቦ
እየተመላለሰ በራያና በአዘቦዎች ዘንድ የተከበረውን ሼክ ጦልሀ ቤን
ጃፋርን ፥ ባንድ ወገን መሐመድ አንፋሪን ፥ በሌላው ወገን ከወሎ ገዥ
ከራስ ሚካኤል ጋር በማዛመድ እስላም ነክ የሆነው አገርና ሕዝብ
ባንድነት ባፄ ምኒልክ መንግሥት ላይ እንዲነሣ ከጓደኛው ከቴኔንቲ
ጂያኒኒ ጋር ሆነው በገንዘብ ከማባበል ጋር በትጋት ይሠሩ ነበር ።
መሣሪያቸው ያደረጉት ሼክ አብዱራህማን ቤን ዩሱፍ የሚባለውን ለዚህ
ተልዕኳቸውም ነው ። ይህ ሰው በመዠመሪያ ያፄ ምኒልክ አሽከርና
ባለሟል ሆኖ በመላላክ ያገለግላቸው ነበር ። በዚህም የራሳንና የጦጦ
ሴን ፥ የጥሙጋን ወረዳዎች ሰጥተውት ሲያስተዳድር ሳለ ፥ በመካከሉ
ከነዚሁ ከኢጣልያ ወኪሎች ከነፒርሲኮና አዲስ አበባ ከሚቀመጠው
ከአንቶኔሊ ጋር ተገናኝቶ ከአውሳ ወደ አዲስ አበባ እየተመላለሰ
እነርሱን በመምራት ተላምዶ ነበር ። እርሱም የመሐመድ አንፋሪን
ልጅ ስለአገባ ፥ በርሱ አማካይነት ኢጣልያኖቹ ከመሐመድ አንፋሪ ጋር
በጣም ተዛምደው ለሁለቱም ገንዘብም መሣሪያም ያፈሱላቸው ዠመር ።
ሁለቱም ባፄ ምኒልክ ታማኝነታቸውን እያደር ከደው ለኢጣልያ መን
ግሥት መሣሪያ ሆኑ ። ዋናው ባላባት መሐመድ አንፋሪ በያመቱ
3,000 በኋላም 4.000 ጥሬ ብር ሲቀበል ፥ አብዱራህማን ትጉኅ ሠራ
ተኛ ስለሆነላቸው የወር ቀለቡ በመዠመሪያ 90 ብር የነበረው ፥ በኋላ
አነሰኝ ብሎ ተከራክሮ ወደ 200 ከፍ አስደረገ ። ቀለቡም ከፍ ባለ
መጠን የርሱም የአማቹም አገልግሎት እያደገ ሔደ ። በተለይ በዚያን
ጊዜ ዐፄ ምኒልክ ይኸን ያህል ቀለብ እየሰጡ ፥ ማስተደደር የመንግ
ሥታቸው የኢኮኖሚ አቅም ስለማይፈቅድ ከቀለቡ ብዛት ጋር በኢጣ
ልያኖቹ ተንኰል አብዱራህማን ፈጽሞ ከዳ ። መሐመድ አንፋሪንም
አስከዳ ።

በዚህ ዓይነት ፥ ከፕሮፓጋንዳው ስልትና ዘዴ ጐን የኢጣልያ መን
ግሥት በሀብቱ ጭምር ይጠቀም ነበር ማለት ነው ። ባፄ ምኒልክ ዘንድ



የአብዱራህማን ቤን ዩሱፍ ክዳትና አድራጎቱ በትክክል ሲታወቅ
ከሹመቱ በይፋ ተሽሮ የርሱን የወረዳ ግዛቶች የኤፍራታው ገዥ
ደጃች ወልዴ አሻግሬና ደጃች መኰሪያ ገርማሜ ተካፈሉት ።[1]

ሼክ ጦልሀ የሚባለው ደግሞ ፥ የተወለደው በዶዶታ (ወረባቦ)
ውስጥ ነው ። በራያና በአዘቦ ፥ በወሎም የታወቀ የሃይማኖት መሪ
ነው ። ከዚህ በፊት እንዳመለከትነው ፥ ዐፄ ዮሐንስ የወሎንና የራያን
እስላሞች በክርስትና እንዲጠመቁ ባዘዙ ጊዜ እምቢ ብሎ ሌሎቹንም
የሃይማኖት ወገኖቹን ይዞ ፥ ብዙ ጊዜ ካፄ ዮሐንስ ጋር ተዋግቶ በመ
ጨረሻ ወደ ሱዳን ሔዶ ከደርቡሾች ጋር በማበር በሣር ውሀ ከንጉሥ
ተክለ ሃይማኖት ፥ በመተማ ካፄ ዮሐንስ ጋር ተዋግቷል ። ሌሎቹንም
እየመራ አዋግቷል ።

ከዐፄ ዮሐንስ ሞት በኋላ ፥ ይኸው ጦልሀ ወደ አገሩ ተመልሶ ከአብ
ዱራህማን ጋር በመተባበር ለኢጣልያ መንግሥት መሣሪያ ሆኖ የራ
ያንና የአዘቦን ኦሮሞዎችና አፋሮችን እያስተባበረ ክርስቲያኖቹን እያስ
ጠቃ ከራስ ወሌም ጦር ጋር በየጁ ተዋግቷል ። የኢትዮጵያና የኢ
ጣልያ ጠብ እየከረረ ሲሔድ በኢጣልያኖቹ ውስጥ ጦሩን አዘጋጅቶ
በአላጌ ሲዋጋ ወደፊት እንመለከታለን ። ከዓድዋ በኋላ በሼክ ዑመር
ኑሬ አማካይነት አዲስ አበባ መጥቶ ከንጉሠ ነገሥቱ ምሕረት ተቀ
በለ ። ቢሆንም ወዳገሩ በመመለስ ፋንታ በአንኮበሩ አዛዥ ወልደ
ጻድቅ ውስጥ የጨኖን ግዛት ተቀብሎ ተቀምጦ በኋላም ከልጅ ኢያሱ
ጋር ባለሟልነት ወጥኖ ነበር ። ልጅ ኢያሱ በወደቁበትም ጊዜ ደግሞ
መልሶ እስራት አግኝቶታል ።[2]

በዚሁ ዓይነት ፥ ከኢጣልያ መንግሥት ውስጡን ለስብከት ላዩን
ለሥራ አስመስለው ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ተልከው የነበሩት
ጐስታቮ ቢያንኪና በሸዋ የታወቀው አውግስቶ ሳሊምቤኒ ናቸው።
ጐስታቮ ቢያንኪ ከፔሌግሪኖ ማቲውች ጋር ወዳፄ ዮሐንስ ተልኮ
መጥቶ የነበረ መሆኑን ፥ በኋላም ከመቀሌ የደንከልን በረሀ አቋርጨ
ልሒድ ብሎ በበረሀ በደንከሌዎች እጅ ሕይወቱ አልፏል ። ከመሞቱ
በፊት በ1867 ዓ.ም. ባፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ከኢጣልያ ንጉሥ
ኒሻንና ልዩ ልዩ ገጸ በረከት ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ይዞ በመም
ጣት ፥ "አባይ ላይም አንድ ድልድይ እንሠራልዎታለን" ብሎ በማስደ
ሰት መልካም ግንኙነት ፈጥሮ ነበር ።

---

1 ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ምዕ 61.
Crispi e Menelich Nel.Diario del Conte Salimbeni, PP. 34, 54 - Italia ed Etiopia, PP. 159 - 160

2 Italia ed Etiopia . . PP. 468 - 469.

ኢጣልያኖቹ ፡ መሳፍንቱን የሚሸነግሉበት ዋናው ስጦታ ስለሆነ ወደኋላ ተመልሰን ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተላከውን ኒሻንና ገጸ በረከት ስንመለከት ሌሎቹም እንደ ደረጃቸው የሚላክላቸው መሆኑን እንገነዘባለን ። ከስጦታው ጋርም መስፍኑ የሚመኘውን ፍላጐት እንደ ሚያሚሉ ያሳያሉ ። ለምሳሌ ፡ በአባይ ወንዝ ላይ ድልድይ መዘርጋት ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ታላቅ ምኞት ስለሆነ ፡ ሳሊምቤኒ ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት የተጠጋው የአባይን ድልድይ እሠራለሁ የሚል የሚያጓጓ የተስፋ ቃል ሰጥቶ ነበር ።

ንጉሥ ተክለ ሃማኖት ፡ ኒሻኑና ገጸ በረከቱ ከደረሳቸው በኋላ ለኢጣልያ ንጉሥ የላኩት ደብዳቤ የሁሉንም ሁኔታ ከዚህ እንደሚከተለው ያብራራል ።

ንጉሥ ቀዳማዊ ኡምቤርቶ ከኢጣልያ ንጉሥ ፡ የተላከ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖት . . . . የእርስዎ ወረቀት ደረሰኝ 5 የእርስዎ ሽልማት የርስዎ በረከት በጐስጣቦ ቢያንኪ . . . እጅ ደረሰኝ . . . እኔም ከርሱ ጋር ሁሉንም ተጫወትሁ ፤ ሁሉንም አደረግሁ ፤ እርስዎ እንደ ጻፉልኝ . . . የእርስዎ ወዳጅነትዎና ፍቅርዎ ለኔ እጅግ መልካም ነውና እጅግ ደስ አለኝ አቶ ጐስጣቦ ቢያንኪ የኢጣልያ ዘውድ መስቀል ሽልማት ባንገቴ አደረገልኝ። የርስዎ ሁለት የዝሆን ጠበንጆች ደግሞ ሁለት አፍ ሁለት ጠበንጆች እሊህ አራቱን የርስዎ ጠበንጆች ። ደግሞ አንድ የርስዎን የአልማዝ ቀለበት የእርስዎን መነጥር የርስዎን ቀይ ሐር ጥላ የርስዎን አንድ ጊዜ የምትተኰስ ሽጉጥ ወርቅ ቅብ የጐራዴ መታጠቂያ ሁለት መስቀል የአልማዝ ዓይነት ተቀበልሁ አንድ ለኔ አንድ ለምሽቴ ይኸን ሁሉ የሰደዱልኝን በጐስጣቦ ቢያንኪ እጅ ተቀበልሁ ። ለዚህም ሁሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ. . . እንግዲህ አንድ ድልድይ እንሠራለን አባይ ላይ . . . እኔም አሁን ስለርስዎ በረከት እንዳላሰናዳ ቀኑ አጠረብኝ የኔ ሀገር እንደርስዎ ሀገር አይደለም ሁሉ ቶሎ ቶሎ አይገኝበትም ። አቶ ቢያንኪ ሲመለስ በረከቱን አሰናድቼ እቆያለሁ የኔ በረከት ለርስዎ ትንሽ ነገር ነው ። . . . አቶ ቢያንኪ በጅሮንድን ሠራተኛውን መሣሪያውን ስለ አመጣልኝ ፡ እኔም አባይ ከድልድዩ አጠገብ አንድ ሀገር እሰጣለሁ ብያለሁ ። ከሸዋ ልጥ ማረፊያ የሚበልጥ ሀገር ነው . . . የፈቀዱልኝም እንደሆነ እኔም የድልድዩን ሥፍራ ድልድዩንም ወምበርቶ አዳል አሰኘዋለሁ የድልድዩን ነገር ካቶ ቢያንኪ ጋር ስንነጋገር የኔ ስም አዳል ነበረ ። . . . ተጽሕፈ በደብረ ማርቆስ ከተማ ኅዳር 13 ቀን 1876 ዓ.ም. በዘመነ ዮሐንስ በዕለተ ሐሙስ ።[1]

ከመጀመሪያው ላይ በኢጣልያ ወዳጅነት ዮሐንስ ፡ ምኒልክ ፡ ተክለ ሃይማኖትና ሌሎችም መሳፍንትና መኳንንት እንደምን እንደ

1 Documenti Amharina - I GNAZIO Guidi - Roma 1891.



ተቃለሉ ይህ ደብዳቤ ያስረዳል ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በኒሻኑና በገጸ በረከቱ ከመደሰታቸው በቀር ፡ የድልድዩ ሥራ በጣም ያማልላቸው ስለነበር ፡ ድልድዩ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ የድልድዩ መጠሪያ ስም ኡምቤርቶ አዳል ተብሎ በቀድሞ ስማቸውና በኢጣልያኖቹ ንጉሥ ስም እንዲሠየም አስበው ነበር ። ነገር ግን ፡ በኢጣልያኖቹ በኩል የድልድዩ ሥራ ለመግቢያ እንዲረዳ ምክንያት ነው እንጂ ፡ ሠርቶ ጨርሶ ለማስረከብና በዚህ ሥራ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት እንዲጠቀም አይደለም ። ስለዚህ ፡ ምክንያት እየፈጠሩ በወሬ ከማራዘም በቀር ዐሥር ዓመት ሙሉ ሥራው አልተጀመረም ።

ብዙ ጊዜ ፡ ምክንያት በመፍጠር እንደ ሳሊምቤኒ ፡ እንደ ኔራሲኒና እንደ አንቶኔሊ ያሉት ባንድ ስፍራ በአዲስ አበባ ተቀምጠው በመሥራት ፈንታ ወደ ትግሬ ፡ ወደ ጎጃም ፡ ወደ ወሎና ወደ ሐረርጌ እየተዘዋወሩ ወሬ በመልቀም ፡ በፊተኛው ጊዜ ሳሊምቤኒ ካፄ ዮሐንስ፣ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ካፄ ምኒልክ ጋር ፡ ኔራሲኒ ከራስ መንገሻና ከራስ መኰንን ጋር ሠርተዋል ። ስለዚህ አሁንም ካፒቴን ፒርሲኮ፣ መሐመድ አንፋሪንና ሼክ አብዱራሀማንን በቃል ስብከትና ገንዘብ በመበተን ሰበዋቸው ፡ የኢትዮጵያን አቅዋም ለማድከም ከመጣር ላይ ናቸው ።

ካገር ተወላጅ ውስጥ በስውር እየመለ መሉ ለስለላ ሥራ ይቀጥራሉ ። መኳንንቱን ፡ ባለሟሎቹን ፡ አስተርጓሚዎቹን ፡ በአዲስ አበባ የሚቀመጡትንና በሥራ ምክንያት ወደ ንጉሡ ቀረብ የሚሉትን አርመኖቹንና ግሪኮቹን በቀጥታ ስላይ ባያደርጓቸውም ፡ በስጦታና በግብዣ እየሳቡ ወዳጅ በማድረግ ወሬ ያጠራቅሙ ነበር ። በተለይ ደግሞ ፡ የንጉሡ ነገሥቱን ዋና አማካሪዎች የስዊሱን ተወላጅ ሙሴ ኢልግንና መሰሎቹን ለኢጣልያ መንግሥት መሣሪያ እንዲሆኑ በግብግብና በዘዴ ያባብሏቸው እንደነበር የሚታወስ ነው ። አሁንም ይኸንኑ ተግባራቸውን በልዩ ልዩ መንገድ ከመቀጠል አላረፉም ።

ዶክተር ሊዎፖልድ ትራቬርሲ ፡ እ.ኤ.አ. በኅዳር 12 ቀን 1890 ወደ ቤተ መንግሥቱ ሔዶ በደጅ ጥናት ሲጠባበቅ ለዋናው አስተርጓሚ ለግራዝማች ዮሴፍ አንድ መቶ ብር ጉቦ መስጠቱን ፡ ግራዝማቹም ስጦታውን በቸልታ መቀበላቸውን ፡ በተቀበሉትም ጊዜ ፡ “ባይቸግረኝ ኖሮ አልቀበልም ነበር ። እንዲያውም ለጣልያኖች ተገዝተሀል ተብዬ ታምቻለሁ” ብለው እንዳዋዩት ያወሳል ። በሌላ ቦታ ደግሞ “ለሌላው አስተርጓሚ ላቶ ገብርኤል ወደኔ ለመሳብ ስል የጠየቀኝን 300 ብር በሦስት ዓመት ውስጥ በሚመለስ ብድር ስም ሰጠሁት ።

በዚሁም እጋጣሚ ስለወሰኑ ጉዳይ ላነጋግረው ቻልሁ . . .”[1] ይላል ። የመስኮቡ ተወላጅ ሙሴ ኒኮላ ሌዎንቴፍ ያፄ ምኒልክ ባለሟል ሆኖ የደጃዝማችነት ማዕረግና ግዛትም ተቀብሎ የነበረው ለመልከት ወደ መስኮብ አገር ሔዶ ሳለ ፣ ከኢጣልያ አምባሳደር ከኮንት ማፎይ ጋር ንግግር ባደረገበት ጊዜ ፣ “ከምኒልክ ጋር በምናደርገው የሰላም ንግግር እርዳንና 2 ሚሊዮን ሊሬ እንስጥህ” ቢሉት ፣ ስለ ኢትዮጵያ ፍቅር ሲል “እምቢ” ማለቱን ገልጾለት ፣ አምባሳደሩም ይኸንኑ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ገልጿል ።[2]

በውጫሌ ውል በ17ኛው አንቀጽ ምክንያት ፣ እንደዚሁም የኤርትራ የግዛት ወሰናችን እስከ መረብ ይድረስ በማለት ጠቡ እየከረረ በሔደበት 1882—87 ዓ.ም. ጊዜ ውስጥ ኢጣልያኖች የኢትዮጵያን መኳንንትና መሳፍንት ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ለመለየትና እርስ በርሱ ለማዋጋት ያላደረጉት ጥረት የለም ። ራስ መንገሻን ከራስ አሉላ ጋር ካፄ ምኒልክ አናጥሎ የማዋጋቱ ጉዳይ ከከሸፈ በኋላ ፣ ንጉሠ ነገሥቱም 17ኛውን አንቀጽና የመረብን ወሰን አልቀበልም ካሉ ወዲህ ክሪስፒ ለባራቲዬሪ በላከው ምስጢራዊ መመሪያ መሠረት ፣ ሁሉንም መሳፍንት በተለይ ደግሞ ፣ ራስ መንገሻንና ራስ መኰንንን በዐፄ ምኒልክ ላይ ለማስነሣት ልዩ ልዩ ሙከራ ተደረገ ። ራስ መንገሻ ከአዲስ አበባ ወደ መቀሌ ተመልሰው በግዛታቸው ተደላድለው እንደ ተቀመጡ ዓድዋ ያለው የኢጣልያ ወኪል ከጄኔራል ባራቲዬሪ አዲስ መመሪያ ተቀብሎ እሳቸው አሉበት መቀሌ ድረስ እየተመላለሰ ፣ ያለፈው ሁኔታ እንዲረሳና አዲስ የወዳጅነት ግንኙነት እንዲፈጠር በልዩ ልዩ ዘዴ ሞከረ ። ነገር ግን ፣ ባለፈው መሐላ አፍርሰው ያታለሉዋቸውን ስለ አልዘነጉት ራስ መንገሻ አሁን የቀረበውን የማታለል ወዳጅነት በምንም ዓይነት ተቀብለው በምኒልክ ላይ ለመሸፈት መንገድ አልሰጡም ።

በሐረር በኩል ራስ መኰንንን ለማስከዳት የተመደቡት ከዚህ በፊት ካፄ ዮሐንስ ጋር ተዋውቆ የነበረውና በኋላም ከጓደኛው ከዶክተር ደ ማርቲኖ ጋር ሆኖ ፣ ራስ መንገሻንና ጄኔራል ጋንዶልፊን መረብ ላይ አገናኝቶ ባፄ ምኒልክ ላይ ያስማማው ማጆር ቺዛሬ ኔራሲኒና በንግድ ስም የተቀመጠው ፒዬትሮ ፌልቴር ናቸው ። ሁለቱም በወዳጅነት መልክ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት በማቅረብ ወደ ራስ መኰንን እየተጠጉ ፣ በጥሩ አነጋገር እያታለሉ ፣ ጠላትነቱ የታወቀውን

1 La Prima Guerra d' Africa - Pal. Crispi, PP. 369 - 370; Crispi e Menelich Nel Diario . . ,PP. 130, 210

2 La Prima Guerra d' Africa . . P. 370



የኢጣልያን ወዳጅነት እየሰበኩ ራስ መኰንንን ካፄ ምኒልክ ለመለየት ከፍ ያለ ጥረት አድርገዋል ። የማባበያው መሣሪያም ከገጸ በረከት ፣ ከጥሩ ጥሩ የእጅ ጠመንጃና የወገብ ሽጉጥ ስጦታ አልፈው ወደ መጨረሻው ግድም ፣ “እርስዎም ፣ እንዳፄ ምኒልክ የንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ልጅ ስለሆኑ ከምኒልክ ተለይተው በሐረር ንጉሥ ቢባሉ ፣ የኢጣልያ መንግሥት ማናቸውንም እርዳታ ያደርግልዎታል” የሚል ነበር ።

ለዚህም የነበረው ማባበያ ወይም ማስፈራሪያ ፣ የኢጣልያ መንግሥት የዘይላን ወደብ ከእንግሊዝ መንግሥት አስፈቅዶ በዚህ ወደብና በጅልዴሳ በኩል የኢጣልያን ጦር ሐረር አምጥቶ በወዳጅነት ጊዜ ለመርዳት ፣ በጠብም ጊዜ ለማጥቃት እንደሚችሉ በመግለጽ ነበር ። ኃያሉ የእንግሊዝ መንግሥት በፍጹም ወዳጃቸው ስለሆነ ፣ በዘይላ ወደብ እንደ ልባቸው ለመጠቀም እንደሚችሉ እያጭበረበሩ ራስ መኰንንን ለማግባባት ይሞክሩ ነበር ። ካሁኑ ጊዜ ላይ ሆነን ስንመለከተው ኢጣልያኖቹ ለማጭበርበር በጣም የረዳቸው ፣ በዚያ ዘመን ኢትዮጵያ ከዓለም መንግሥታት ጋር የነበራት የግንኙነት ደካማነት መሆኑ አይጠረጠርም ። በሮማ ፣ በበርሊን ፣ በፓሪስ ይልቁንም በሎንዶን የነዚህን አገሮች ትክክለኛውን የፖለቲካና የወታደር አቅዋም የኢጣልያንንም ደካማ ጐን የሚገልጽ ወኪል ስለሌላት ፣ የተሠራጩት የኢጣልያ ሰላዮችና ባለሥልጣኖቹ እንደ ልባቸው በመሳፍንቱና በመኳንንቱ ፊት የሆነ ያልሆነውን እየቀባጠሩ የማይችሉትን እንደሚችሉ እያደረጉ ያወሩ ነበር ።

የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባሮን ብላን ፣ ለባራቲዬሪ እ.ኤ.አ. ጥር 4 ቀን 1895 ዓ.ም. ባደረገው ቴሌግራም ፣ “ወደ ሐረር የሚያስገባውን የዘይላን በር እንድንጠቀምበት እንግሊዞች ፈቅደዋል ። ነገር ግን እስካሁን ወረራውን ያልፈጸምነው መኰንንን በማክበር መሆኑን እንዲያውቅ አድርግ ። ይኸን ወረራ የምንፈጽመው ጠላታችን መሆኑን በግልጽ ያወቅን ዕለት ብቻ ነው ። ጊዜው ቁርጠኛ ስለሆነ ስለ መጪው ዕድሉ ማሰብ አለበት ። አንድ ቀን ሊሞት ከሚችለው ከምኒልክና ዘለዓለማዊና ኃያል ከሆነችው ከኢጣልያ መምረጥ አለበት”[1] ሲል አስተላልፎለታል ።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደ ክሪስፒ ፕላን ፣ የኢትዮጵያውያንን ጠባይ ፣ የኢትዮጵያንም መኳንንት ውስጣዊ ሁኔታ ከጭፍሮቹ በሚላከለት ራፖር ላይ ከጨረፍታ ንባብ በቀር በትክክል የሚያውቀው አይመስልም ። ኢትዮጵያውያንም ሞራል የሌላቸው በቀላል

1 Memoire d' Afrique - O. Baratieri, P. 358.

ልብከትና ተስፋ አቋማቸውን የሚለዋዉጡ ይመስለዋል ። የዘለዓለማዊት ኢጣልያን መኖር ሲያምን ፣ በራስ መኰንን ዘንድም የዘለዓለማዊት ኢትዮጵያ ህልውና እንደአለ ፈጽሞ ከአእምሮው ፍቆታል ማለት ነው ። እንደ ክሪስፒ ግምት ራስ መኰንን ላዔ ምኒልክ ምን እንደ ሆኑ ፣ እንደምን እንዳሳደጓቸው በሁለቱ መካከል ያለውን ልባዊ የአባትና የልጅ ፍቅር እያውቀውም ። ይኸን የመሳሰለውን በመስማትና ሌላውንም የኢጣልያኖች ሁኔታ እየተመለከቱ በመገረም ከዕለታት አንድ ቀን ራስ መኰንን ፣ "እነዚህ ጣልያኖች ሞኞች ናቸውን ኧረ በል አፈወርቅ አንተ የነበርህበት አገር (ኢጣልያ) እንደ ኔራሲኒ ያለ ደላጎ (ሞኝ) ያበቅላልን"[1] ብለው ነጋድራስ አፈወርቅን ጠየቁ ይባላል ።

እነዚህ ሁሉ የስለላ ወኪሎች ያጠናቀሩትን ፣ ለነርሱ በተገዛ ያገር ተወላጅና የውጭ አገር ሰው እጅ አንዳንድ ጊዜ በግልጽ ጽሑፍ ሌላ ጊዜ በምስጢር ወይም በተስማሙበት የቁጥር ቃል ፣ ግማሾቹ አሥመራ ለነበረው ለጄኔራል ባራቲዬሪ ሲያስተላልፉ ፣ እንደነ ኔራሲኒና እንደነ አንቶኔሊ ያሉት ደግሞ ፣ በቀጥታ ወደ ሮማ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያስተላልፉ ነበር ። በኤርትራ ሆነው ወሬ ከየሰላዮቻቸው እያጠራቀሙ ለዋንኛው ለጄኔራል ባራቲዬሪ ከሚያቀርቡት የጦር መኰንኖች ውስጥ ቲኔንቲ አሌሳንድሮ ሳፔሌ የሚባል የባንዶች አለቃ የነበረው ይገኛል ። ይህ ሰው አርጅቶ በ1935 ዓ. ም. የማይጨው ጦርነት ዋዜማ ላይ ባሳተመው የማስታወሻ መጽሐፉ ፣ "ከደብረ ኃይላ ጦርነት ወዲህ ስለ ሸዋ ጦር ሠራዊት ቁጥርና ድርጅት ከኤርትራ ፣ ከትግሬ የሰበሰብሁትንና ከአዲስ አበባ እንጂኒዬር ካፑቺ በሰፊው በቁጥር ቃል የላከውን የቁጥሩን ቃል ፈትቼ ላገሬ ገዥው (ባራቲዬሪ) ያቀረብሁት ትክክል ነበር"[2] ይላል ።

በዚሁ ዓይነት ፣ ሁሉም በየተሠማራበት አውራጃና ከተማ ፣ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ ጋር ፣ የእጅ ጥበብ ሥራና የሕክምና አገልግሎቱን በማበርከት ፣ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደ ተላከው ዓይነት ባይሆንም ፣ ከዚያ ዝቅ ያለ ልዩ ልዩ ገጸ በረከት በማቅረብ ይወዳጅ ነበር ። መሳፍንቱና መኳንንቱም አንዳንዶቹ የጉዳዩን ሁኔታ በግልጽ ሳይረዱ ለያንዳንዱ የኢጣልያ ወኪል ፣ "ያንተም የኢጣልያም ወዳጅ ነን" እያሉ ከልብም ይሁን ካፍ የሚገልጹለትን በልቡ ይተማመንበትና ይኸንኑ በቶሎ ወደ ኤርትራ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ሲያስተላልፍ

1 ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ — ገጽ 94—95
2 Memorie d' Africa - A. Sapelli, P. 93



እርሱም በፋንታው ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ "መሐመድ አንፋሪ በፍጹም የኛው ነው ። ራስ ሚካኤል ታማኝነታቸውን ለኢጣልያ ገልጸዋል ። ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መልእክተኞቼን በደስታ ተቀብለው አስተናግደዋል ። በከሰላ ደርቡሾችን ያሸነፍሁ ጊዜ ፣ እንኳን ደስ አለህ ብለው የደስታ መግለጫ ልከውልኛል ። ዋግሹም ብሩ ከራስ ሚካኤል የበለጠ ግልጥ በሆነ መንገድ ለኛ ታማኝነታቸውን አረጋግጠዋል ። በሐረር ራስ መኰንን ጦርነቱን በምትጀምሩበት ጊዜ ወደ ናንተ እንደረባለን ብለዋል ። እጨጌ ቴዎፍሎስና የአክሱም ካህናት የኛ መሣሪያ ናቸው . . ."[1] እያለ ሰፊ ራፖሩን ሲያስተላልፍ ሮማ ያሉት መሪዎች ልባቸው ለመደንደን ቻለ ።

ወደፊት ሲፈጸም እንደምናየው ፣ በእውነቱ ኢጣልያኖችን እደፋፍሮ መረብን አልፈው ራስ መንገሻን በመውጋት እስከ አምባ አላጌ ድረስ ያስገሠገሣቸው ይኸ ሁኔታ ነው ። ከዚህ ከተወራው ሁሉ አብዛኛው ከንቱ ተስፋ ሲሆን ፣ የአውሳው የመሐመድ አንፋሪና የዋግሹም ብሩ በስውር ከኢጣልያኖቹ ጋር መሳላክ እርግጠኛ ነው ። እንደዚሁም የአክሱሙ እጨጌ ቴዎፍሎስ ባንድ ወገን ምኒልክን በመጥላት ፣ በሌላ ወገን ባራቲዬሪ በስጦታ ስላሰከራቸው ፣ ልባቸውን ለጣልያኖቹ መስጠታቸው በሰነድ የተረጋገጠ ነው ። በኢጣልያም ጐን ሌሎቹ ኃያላን መንግሥታት ፈረንሳይ ፣ መስኮብ ፣ እንግሊዝ በአዲስ አበባ የወኪል ሰላይ ማስቀመጣቸው አልቀረም ። ወኪሎቹ ሁሉ በየበኩላቸው ለየመንግሥታቸው ጥቅም ሲሠሩ ገጸ በረከትም ማቅረባቸው የታወቀ ነው ። ነገር ግን ፣ ከሁሉም ይበልጥ በኢትዮጵያ ላይ ገዥነቱን ለመመሥረት ያተኮረው እንደ ሌሎቹ ቅኝ አገር ያልደረሰው የኢጣልያ መንግሥት ስለሆነ ፣ የንጉሡ ነገሥቱ ትግል ከዚሁ መንግሥት ጋር መሆኑ ግልጽ ነው ። ኢጣልያኖቹም ፣ ሌሎቹም ይኸን ሲሠሩ ያዔ ምኒልክ አያያዝ ምን እንደነበር ታዋቂው ጸሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ ባጭሩ እንደዚህ ሲል ገልጦታል ።

> ምኒልክ ምክር ያዳምጣሉ ፤ ስጦታን ይቀበላሉ ፤ ራሳቸው ከመጠንቀቅ በቀር በማናቸውም ላይ ሳይተማመኑ በአጠራጣሪው ለሚደርሰው ፣ የጦርነት ዝግጅታቸውን ይቀጥላሉ. . . የጦር መሣሪያ ይሰበስባሉ . . . በወሎ ጐተራ እህል ያከማቻሉ . . . ለመሣሪያ መግዣ የመሬቱ ግብር አልበቃ ስላለ ፣ በከብት ላይ ልዩ ቀረጥ አውጥተው በሁለት በሬ አንድ ብር ያስከፍሉ ነበር ። . . .[2]

1 Memoire d' Afrique - O. Baratieri; Chap. 18, PP. 247 -256, Chap. 27. PP. 356 - 358.
2 Italia ed Etiopia . . .PP. 108 - 109

ይኸም አባባል እውነት ነው ። የወደፊቱ ጦርነት የማይቀር መሆኑን ደህና አድርገው የገመገሙት ንጉሠ ነገሥት ፣ ከእቴጌ ጣይቱና ከቅርብ የባለሥልጣን አማካሪዎቻቸው አሳብና ምክር እያዳመጡ ሁሉም ነገር ማለትም ፣ ለጦርነት አብነት የሆነው የጦር መሣሪያና ስንቅ እንዲዘጋጅ ማድረጋቸው የኢጣልያንንም ያለፈ ብድር ለመክፈል ገበሬው ሁሉ በየአንዳንዱ በሬ የገንዘብ ቀረጥ እንዲከፍል የጭራ ግብር ማወጃቸው እርግጥ ነው ።



## ምዕራፍ ዐሥራ ዘጠኝ

### የዠኔራል ባራቲዬሪ ዓድዋ መምጣትና መመለስ—ራስ መንገሻና ኢጣልያኖች ኰዓቲትና ሰንዓፌ ላይ ያደረጉት ጦርነትና የራስ መንገሻ መሸነፍ

ያጋሜው ራስ ስብሐት ፣ ቀደም ሲል በራስ አሉላ አማካይነት ከራስ መንገሻ ጋር ታርቀው ገብተው የራስነት ማዕረግ ከርሳቸው ተቀብለው ሳለ ፣ በኋላ ከራስ አሉላ ጋር ሆነው የዓድማ ነገር ስለ ተገኘባቸው ራስ አሉላ ግማሽ ግዞት ሲያገኛቸው ፣ ራስ ስብሐት በአምባ ሰላማ እንዲ ታሰሩ የሚታወስ ነው ። ራስ አሉላም በራስ መንገሻ ቅሬታ ስለ ገባቸው ፣ ራስ መንገሻም ከሸዋ ወደ ትግሬ ሲመለሱ እርሳቸው አዲስ አበባ መቅረታቸውን ከዚህ በፊት አመልክተናል ። ራስ መንገሻ ፣ ራስ ስብሐትን ካሰሩ ወዲህ የአጋሜን ግዛት ሹም አጋሜ ተስፋዬ አስኝተው ለደጃች ተስፋዬ (የእንጣሎው) ሰጧቸው ። በአንድ ወገን በአጋሜ ባላባትነት ያላቸው ደጃች ሐጎስ ተፈሪም የራስ ስብሐትን መታሰር ፣ የደጃች ተስፋዬን መሾም ሲመለከቱ ከነጭፍራቸው ለኢጣልያኖች ገብተው ተቀመጡ ።

በዚህ ዓይነት ፣ ከራስ መንገሻ የሸፈተው ወደ ኢጣልያኖች ሲገባ ፣ ኢጣልያኖች ሐማሴንንና አከለ ጉዛይን ሁሉ እያለፉ እስከ መረብ ድረስ ተጠጉ ። የራስ መንገሻና የኢጣልያኖችም ጦርነት የማይቀር ሆነ ። በዚህ ጊዜ ዤኔራል ባራቲዬሪና ራስ መንገሻ ውስጡን ጠላቶች ሆነው ፣ ላዩን እንደ ወዳጅ ደብዳቤ እየተጻጻፉ ፣ ሁለቱም ወታደር እየመለመሉ የጦር ድርጅት ከማድረግ ላይ ይገኛሉ ። በራስ መንገሻ ዘንድ ብዙ መኳንንትና ወታደር ከነመሣሪያው ቢኖርም ፣ በኢጣልያኖችም ዘንድ እነደጃች ተስፋ ማርያም ፣ እነደጃች ሐጎስ ተፈሪ ፣ እነደጃች አሊ የእንዳመሆኔው ከነጭፍራቸው አሉ ። ከነዚህ ደግሞ የበሰጡት የወር ቀለብ እየተቀበሉ ፣ ደንበኛ የጦር ትምህርት እየተማሩ ፣ የወታደር ልብስ እየለበሱ ከውስጣቸው ሙንጣዝ ፣ ቡልቅባሻ ፣ ሹምባሽ ፣ ቡዝባሽ እየተባሉ በሚሾሙ ሥር ሆነው የሚተዳደሩ ያገር ተወላጅ ወታደሮች ይገኛሉ ። እነዚህ ከኢጣልያ ከመጡት የነጭ ወታደሮች ጋር ሆነው የፈረሰኛውና የእግረኛው ጦር ፣ መድፈኛውና ባለጠመንጃው በድልድል ተደራጅቶ ለወደፊቱ ጦርነት

ይጠባበቃል ። ለኢጣልያም ጦር ከአክለ ጉዛይ ፤ ከሐማሴን ፤ ከሰንዓፌው የባንዳ ጦር በቀር ከምዕራብ በኩል የሱዳን ፤ የቤን አሚር ፤ የብሌን ፤ የሐባብ ፤ የቦጎስ ፤ የከረን ተወላጅ ለወታደርነት እየተመለመለ በአተኳኮስ እየሠለጠነ ለኢጣልያኖች ጕራቸውን አጠንክሮላቸዋል ።

በዚህ አኳኋን ፤ የኢጣልያ ጦር ዝግጅቱን ቢጨርስም በቶሎ መረብን ተሻግሮ ከራስ መንገሻ ጋር ጦርነት አልገጠመም ። ጦሩ ከዚህ ቀደም ከነደጃች አበራ ፤ ከነደጃች ባሕታ ሐጎስ ጋር በሐላይ በአደረገው ውጊያ እንዲሁም በከሰላና በአቆርዳትም በኩል በአከናወነው ጦርነት ለጊዜው ስለቀናው ፤ "የኢጣልያን ጦር የሚችለው የለም" የሚል ስብከት በሕዝቡ ዘንድ ተነዝቶ ነበር ። አሁንም ጄኔራል ባራቲዬሪ ያለ ጦርነት ዝም ብዬ መረብን ተሻግሬ ዓድዋ ብገባ ሕዝቡም፥ መኳንንቱም አሜን ብሎ ይገባልኛል ፤ የዐፄ ምኒልክን መንግሥት የጠሉት እነእጨጌ ቴዎፍሎስ አገሩን ለብከው ከራስ መንገሻ እየለዩ ወደኔ ያመጡታል ። ከዚያ በኋላ የራስ መንገሻም ጦር ምንም ማድረግ ሳይችል ይሸሽና የኢጣልያን ግዛት በሙሉ ትግሬ ላይ በሰላም አስፋፋለሁ " የሚል ምኞት አደረበት ። ለአጋሜ ሰዎች ደግሞ "ግድ የላችሁም ቢቻል በሰላም ያለዚያም ከራስ መንገሻ ጋር ተዋግቼ ባላባታችሁን ራስ ስብሐትን አስፈትቼ አመጣላችኋለሁ" እያለ ሰበካቸው ። ባንድ ወገን ደግሞ ራስ መንገሻን ለማዘናጋት ፤ "ወደ ዓድዋ መጥቼ ከዚህ ቀደም መረብ ላይ ተዋውለን በፈረሰው ውል ተወቃቅሰን እንደገና ወዳጅነታችንን እናድሳለን" የሚል ሐሰተኛ መልእክት አስቀድሞ እየላከ በማታለል ፤ መልስ ሳይጠብቅ ከሠራዊ ተነሥቶ ወደ ዓድዋ ተጓዘና በታኅሣሥ 21 ቀን 1887 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ በስምንት ሰዓት ዓድዋ ከተማ ገባ ። ሕዝቡም መኳንንቱም ነገሩ ገርሞት የበረታና የቆረጠው ራስ መንገሻ ወዳሉበት እየሔደ ተጠቀለለ ። የቀረው በየስፍራው ሆኖ የሚመጣውን ነገር ዝም ብሎ ይጠባበቅ ጀመር ።

የዓድዋ ካህናትና ቀሳውስት ግን ፤ በእጨጌ ቴዎፍሎስ መሪነት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ፤ መስቀል ይዘው ፤ እንዳንድ የሽመግሌ ሰዎች ጨማምረው ፤ ተሰልፈው ተቀበሉት ። እርሱም እንደ ደረሰ ከፈረስ ወርዶ የእጨጌ ቴዎፍሎስንና የቀሳውስቱን መስቀል በስብከት መልክ ተሳልሞ ንግግር ያደርግ ጀመር ። ራስ መንገሻ እላይ እንዳልነው ፤ በዚህ ጊዜ ከነጦራቸው ከዓድዋ ወደኋላ ሆነው ይጠባበቁ ነበር ። በዓድዋም ጐበዝ ጐበዙ ሁሉም ከተማውን ትቶ ወደ ራስ መንገሻ ሆኖ የዓድዋ ከተማ ከሴትና ከሽማግሌ ፤ ከካህናትና ከቀሳውስት በቀር ባዶ ነበረች ። ጄኔራል ባራቲዬሪ አዘናግቶ ራስ ስብሐትን ከታሰሩበት ለማስፈታት የሚችልበትን መንገድ እያሰበ ግማሽ ጦሩን ወደ አክሱም ሰመላክ ሲጀምር ፤ የራስ መንገሻ ጦር ወደ ዓድዋ እየተጠጋ መከበብ



ጀመረ ። በዚህም አሳቡ ስለ ተሰናከለበት ፤ ጌም ብሎ ከራስ መንገሻም ጋር ፊት ለፊት እንዳይዋጋ ያመነታ ጀመር ። በዚሁም ላይ ፤ "ከራስ መንገሻ ጋር ሲዋጋ ደርቡሾች እንደገና በከሰላ በኩል የከረንን ፤ የሐባብን ግዛት ሊወሩብኝ ይችላሉ" ብሎ ተጠራጠረ ። ዓድዋ ሲደርስ ፤ "ሰው ሁሉ ከነመኳንንቱና ከነባላባቱ ጭምር እየመጣ እንደ አገሩ ልማድ እጅ እየነሣ ይገባልኛል ፤ ራስ ስብሐትንም አስፈትቼ እመለሳለሁ"ብሎ ተስፋ አድርጎ የነበረው ሳይሳካለት ቀረ ። እንዲያውም ፤ እርሱ ዓድዋ ላይ እንዳለ ወደ መጣበት ለመመለስ ሲሞክር የራስ መንገሻ ጦር ከቦ መንገድ ከለከለው ። ይልቁንም እርሱ ከነእጨጌ ቴዎፍሎስ ጋር በሚነጋገርበት ጊዜ ፤ የሐማሴንና የሰንዓፌ ባንዶችና ወታደሮች በከተማው በየሰላማዊው ቤት እየገቡ ያገኙትን መዝረፋቸው ፤ ሕዝቡንም ማጉላላታቸው ስለ ተሰማ ፤ የራስ መንገሻ ሰዎች ከበው ለውጊያ ተዘጋጁ ። በኋላ ግን ፤ አጠገቡ ያሉትን ወታደሮቹን አስልፎ ፤ "ለማናቸውም ተጠንቀቁ" ብሎ እርሱ በፈረስ እንደ ተቀመጠ ወደ ቀሳውስቱ ወደ እነ እጨጌ ቴዎፍሎስ ሔዶ ፤ "እኔ የመጣሁት እርቅና ሰላም ለማድረግ እንጂ ለጦርነት አልነበረም ። አሁንም እርቁን ካልፈለጉት በሰላም ይልቀቁኝና ወደ አሥመራ ልመለስ "ብሎ አመለከተ ። በዚህ ጊዜ ከርሱ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት አድርገው የቆዩት ባለወርቅ ጥልፍ ካባና ቀሚስ ሌላም ገጸ በረከት እየላከ አስደስቷቸው የነበሩት እጨጌ ቴዎፍሎስ ፤ "እርሱ እንደዚህ ሰላማዊ ሆኖ ፍቅር ሲያሳያችሁ እናንተ ለምን በጠብ ትፈልጉታላችሁ" ብለው ምክርም ፤ ተግሣጽም እየጨመሩ ለራስ መንገሻ ሰዎች ስለነገሩዋቸው ፤ ተስማምተው ለቀቁትና በቀጥታ ጄኔራሉ ከዓድዋ ወደ አዲ ኳላ ተመለሰ ።[1] ከዚህ ቀጥሎ ራስ መንገሻ ጦራቸውን ይዘው ከዓድዋ ወደ መረብ ተጉዘው ፤ ከዚያም ወንዙን እየተሻገሩ የዛማን ሜዳ አልፈው አከለ ጉዛይ አውራጃ ገቡ ። በዚህ ጊዜ ጄኔራል ባራቲዬሪ ሹማምንቱን ከነወታደሩ በየአለበት ለጦርነት አሰለፋቸው ።

ማዦር ቶዜሊ የሚባለው ፤ የራሱን የባታዮ ጦር ይዞ በአከለ ጉዛይ በባንዶች አለቃ በቲኔንቲ ሳንጉይኔቲ እየተረዳ በፍጥነት መጥቶ ኮአቲትን ያዘ ። ዓድዋ እንደ ቆንሲል ሆኖ ይቀመጥ የነበረው ቲኔንቲ ሙላዚኒ የሚባለው የራስ መንገሻ የፊተኛው አያያዛቸው አስፈርቶት ይዘው እንዳያስሩት ከዓድዋ ሸሽቶ መጥቶ ባሁኑ ጊዜ የሠራዬን ባንዳ ያዝ ነበርና እርሱም ባንድ ወገን መጥቶ ለማዦር ቶዜሊ ረዳት ለመሆን ኮአቲት ደረሰ ። ከማዦር ቶዜሊ ጦር በግራ በኩል ማዦር ጋልያኖ ፤ ከኋላ ደጀን ማዦር ሄዳልጎ ሆነው በኮአቲት የራስ መንገሻና

---

1 Memoire d' Afrique - O. Baratieri. Chap.6

የኢጣልያኖች ጦር ቅርብ ለቅርብ ተሰልፎ አደረ ። በማግሥቱ ጥር 6 ቀን (እ.ኤ. አ. 13 ጥር) ሊነጋጋ ሲል ፣ ለማንጣጠር እሚመች ስፍራ ላይ ሆኖ ካፒቴን ቺኮዲኮላ የመጀመሪያውን የመድፍ ጥይት በራስ መንገሻ ሰፈር ላይ በመተኮስ በጩኸቱ የጦርነቱን መጀመር አስታወቀ ። ወዲያው ኢትዮጵያውያኑ ወደየሰፈራቸው ተሯሩጠው መሣሪያቸውን ይዘው ተግን እየያዙ መልሰው እየተኮሱ ይዋጉ ጀመር ። ቀኑን ሙሉ እየጋለም ፣ እየበረደም ሲዋጉ የመሬቱ ወጣ ገባነት ፣ የጫካውና የእሾሁ ፣ የዳገቱና የቁልቁለቱ ሁኔታ ለኢትዮጵያውያኑ ሲረዳ ፈረንጆቹ ስለ ተቸገሩ ፣ የዚህ ቀን ጦርነት ለራስ መንገሻ ጦር የድል ተስፋ ከፍቶለት ነበር ። የኢጣልያንንም ጦር ለመከበብ ግራና ቀኝ ሲዘዋወሩ እነዚያም እንዳይከበቡ ግራና ቀኝ እየተራራቁ ሲከላከሉ ጊዜው ስለመሸ እንደዚሁ በያሉበት አዳር ሆነ ። በማግሥቱ ጦርነቱ ተጀምሮ በሚቀጥልበት ጊዜ የኛዎቹ ስንቅና ውሀ ስለ አለቀባቸው ከኮአቲት ወደ ሺምዛና አፈገፈጉ ። "ራስ መንገሻ ወደኋላ ያፈገፈጉት ቁጥሩ እጅግ የበዛ ጦር ለጣልያኖች ደረሰላቸው ማለትን ከሐሰተኛ ሰው ስለሰሙ ነው" ይባላል ። የሆነ ሆኖ ፣ ራስ መንገሻ ከኮዓቲት ከነ ጦራቸው በሺምዛና በኩል አድርገው ወደ ሰንአፌ ሔደው ሰፈሩ ። ኢጣልያኖቹ ግን ፣ የዚህን የኮዓቲትን ጦርነት እንደ አንድ ዠብዱና ድል በማድረግ ቆጥረውታል ። የራስ መንገሻንም ከኮዓቲት ወደ ሰንዓፌ መሔድ እንደ ሽሽት ገምተውታል ። ነገሩም የሚመስል ነው ።

በዚህም ጦርነት ከራስ መንገሻ ወገን ደጃች ተድላ አይባ ፣ ወንድማቸው ደጃች አርአያና ልጃቸው ቀኛዝማች ተፈሪ ፣ የራስ ኃይለ ማርያም ልጅ ደጃች ግዛዌ ሞቱ ። ሹም አጋሜ ተስፋዬም ቆሰሉ ። ከተራው ወታደር የሞተውና የቆሰለው አይታወቅም ። ከኢጣልያኖቹም ወገን ደጃች ባሕታ ሐጎስ ማርከው ያሰሩት ቴኔንቲ ሳንጉይኔቲ በዚህ ቀን ቆስሎ ቆይቶ ሞተ ። ከባንዳና ከደንበኛ የኢጣሊያን ጦር ግን ፣ የሞተው 90 የቆሰለው 227 ይደርሳል ።[1] በዚህም በሌላውም ጦርነት ለኢጣልያኖቹ መሣሪያ በመሆን እፊት እየቀደሙ ከወገናቸው ጋር በመዋጋት የሚያልቁት እነዚያው ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እንረዳለን ። የራስ መንገሻ ጦር ከኮዓቲት ወደ ሰንዓፌ አፈግፍጎ ከሔደ በኋላ ፣ ማታውኑ የራስ መንገሻ ሰዎች ማርከዋቸው የነበሩት የባንዳ ወታደሮች ከማራኪዎቻቸው አምልጠው ወደ ኢጣልያኖቹ በመመለስ ፣ "የጠላት ጦር ተዘበራርቆ ወደ ቶኮንዳ ይጓዛል" የሚል ወሬ ለኢጣልያኖቹ አመጡላቸው ። ይህም ውጊያውን ለመቀጠል ሞራላቸውን ከፍ አደረገላቸው ።

1 Douze ans en Abissinie - De Lauribar, Chap. 28,PP. 365 - 381.



በዚህ ጊዜ ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ከሌሊቱ በ9 ሰዓት ስብሰባ አድርጎ ከሹማምንቱ ጋር ተመካክሮ ፣ "ወፍ ጭጭ ሲል ተነሥቶ የጠላት ጦር አለበት ድረስ ተከታትሎ ማጥፋት ነው" የሚል ውሳኔ ተደረገ ። ከዚህ በኋላ ወታደር ሁሉ ያራት ቀን ስንቁን እንደያዘ ጉዞ ጀመረ ። የጉዞውንና የጦርነቱን ሁኔታ ጦርነቱን የተካፈለው ደ ሎሊባር እንደዚህ ይላል ።

መንገዱ ውጣ ውረድ የበዛበት ስለነበረ ጉዞው አስቸጋሪ ነበር ። አዴ አዌይ ስንደርስ አበሾቹ ጥለዋቸው የሔዱትን ቁስለኞች አገኘን ። ከዚያ ወዲያ የመንገዱ መጥፎነት እየባሰበት ሔደ ። ደንጋያማ ተራራና ሸለቆ የበዛበት ሸለቆው ደግሞ ቆንጥር እሾህ የሞላበት ስለሆነ በዚያ ሲታለፍ በእሾህ መነከስ አለ ። አንድ ቦታ ስንደርስ ብዙ ጦር ያለፈበት ሥፍራ አገኘን ። ከዚያ የዳሪሲያንን ተራራ ወጥተን ወደ እምባሻላይ ተዘቅዝቀን ወደ እኩለ ቀን ላይ ቶኮንዳ ደረስን ። ከዚያ ከትንሽ ጊዜ በፊት ራስ መንገሻና ጦራቸው ከዚያ አልፈው ወደ ሰንዓፌ መሔዳቸውን ሰማን ። ምግብና ውሀ ያለበትን ለውጊያም የተመቸ ሥፍራ ያለበትን ቶኮንዳን አልፈው በመሔዳቸው ፍርሐት እንዳደረባቸው ተገነዘብን ። ስለዚህ አሁኑኑ የወታደራችን ሞራል ከፍ ባለበት ሰዓት በመጠቀም ያንድ ሰዓት ዕረፍት ብቻ ካደረግን በኋላ ግሥጋሤአችንን ቀጠልን ። ከቶኮንዳ ቀጥሎ ወዳለው ተራራማ ሥፍራ ሲወጣ ጉብታቸው የፈጠጠው የሐላይ ፣ የዓድዋ ወረዳዎች እንደዚሁም የመረብን ወንዝ የሚያካብቡት የተራራ ሰንሰለቶች እስከ ሐዶ ድረስ ወሰል ብለው ይታያሉ ። ይኸን ጉብታ አልፈን ወደ ከስከሴ ደረስን ። ከዚያ ደንጋያማ ሸለቆና ጉብታ የሆነውን ለቀን ወሀ ያለበትን ደልዳላና ሜዳማ ሥፍራ ተመለከትን ። ጊዜውም ፀሐይ የምትጠልቅበት ወቅት ስለነበረ ፣ ጠላቂዋ ፀሐይ የወረወረችው የማታ ጮራ ልምላሜ ያለውን ቀበሌ በቀይ ቀለም አሸብርቆት ነበር ።

. . . በሜዳማው ሥፍራ ራስ መንገሻና ጦራቸው እንደ ሰፈሩ ተመልከተን መድፋችንን በጥድፊያ ጠምደን ተኩስ ከፈትን ። ወዲያው ራስ መንገሻ ከድንኳናቸው ወጥተው ጦራቸውን ሰብስበው ለማዋጋት ማበረታታት ጀመሩ ። በመጀመሪያ የተተኮሰው መድፍ የራስ መንገሻን ድንኳን በታትኖ ብዙ መኳንንት ገደለ ። በዚያው ሰዓት ዠንበር ስለ ጠለቀችና ወዲያው የኛንም የነርሱንም ሰፈር ጨለማ ስለሸፈነው ፣ የጦርነቱን ጊዜ ለማግሥቱ አስተላለፍነው ። በማግሥቱ ወደ ሜዳው ተዘቅዝቀን ብንወርድ ፣ ጠላት ሌሊቱን በጥድፊያ ተዘበራርቆ ሸሽቶ ኖሮ ባዶ ሰፈር አገኘን . . . ካለ በኋላ

ከዚሁ አያይዞ ፣

ወደ ራስ መንገሻ ድንኳን ብንገባ በመሬት ላይ ልብስ ወረቀት የቤት ዕቃና ምግብ መሥሪያ በያይነቱ ተዝረክርኮ ይታያል ። መከዳቸው በሐር ልብስ ተሸፍኖ በርሱም ላይ የሸቶ ብልቃጥና አንድ በብረት የተለበደ ጥሩ የጸሎት መጽሐፍ ጄኔራል ባራቲዬሪ ልኮላቸው የነበረ የወርቅ ሰዓት ከባሕታ ሐጐስና ከምኒልክ እንደዚሁም ከፈረንሳዊ ክላዛሪስት ሚሲዮን አለቃ ጋር የተጻጻፉት ደብዳቤ በሙሉ ተገኘ ።

> በዚህም ባሕታ ሐጐስን ያስከዱ ራስ መንገሻ መሆናቸውን በነገሩም የላዛሪስት ሚሲዮኖች ተስማምተው እንደ ገፋፉት ተረዳን ።

ካለ በኋላ ፣ ጽሑፉን በመደምደም ይኸው ደ ሎሊባር የሚባል ጸሐፊ ባለፈው በኮዓቲት በጀግንነት የተዋጉት ትግሬዎች በዚህ በሰንዓፌው ጦርነት እንደሚገባ ሳይዋጉ ስለሸሹ ፣ ምን እንደ ነካቸው አለማወቁን ያመለክታል ።[1]

የሆነ ሆኖ ፣ ኢጣልያኖቹ በሐላይ በደጃች ባሕታ ሐጎስ ላይ ባገኙት ድልና አሁንም በዚህ በኮዓቲትና በሰንዓፌ በአገኙት አሸናፊነት እየተደሰቱ በትምክህትና በኩራት መረብን አልፈው ወረራቸውን ቀጠሉ ። ጄኔራል ባራቲዬሪም ፣ ለጊዜው ሰንዓፌ ላይ ማዦር ጋልያኖን አስቀምጦ ፣ የኮዓቲትን ጦርነት ለተካፈሉት ለደጃች ሐጎስ ተፈሪ አጋሜን ሰጠ ። እርሱ ወደ ምጥዋ ሔዶ ፣ የድል አድራጊነቱን በዓል በደስታ አክብሮ ፣ ከዚያ እንደገና ወደ አሥመራ ተመልሶ የአገር ወረራውን አሳብ ያውጠነጥን ጀመር ። ራስ መንገሻም ከያዙት ከ14 ሺ ባለጠመንጃ ፣ ከ4ሺ ባለጦርና ባለጋሻ ወታደር ውስጥ በኮዓቲትና በሰንዓፌ ጦርነት ከአንድ ሺ የበለጡ ከደህና ደህና መኳንንቶች ጋር ቢሞቱባቸውና ሁለት ሺ የሚሆኑ ቢቆስሉባቸውም ፣ ከተረፈው ጦራቸው ጋር ወደ ኋላ ወደ መቀሌ መጡ ። እዚያም ሳሉ የሆነውን ሁሉ ወዳጄ ምኒልክ ልከው የእርዳታ ጦር ከሸዋ እንዲደርስላቸው አመለከቱ ። ነገር ግን ፣ መላከተኛው ገና አዲስ አበባ ሳይደርስና መልሱን ሳያመጣ ከዚህ በፊት እንዳልነው ፣ ጄኔራል ባራቲዬሪ ከአሥመራ ትእዛዝ እያስተላለፈ ፣ ማዦር ቶዜሊ የደጃች ሐጎስ ተፈሪን ባንዳ ይዞ የአጋሜን ከተማ አዲግራትን እንዲይዝ ፣ ማዦር አሚሊዮ ያገር ተወላጅ ያምስተኛ ባታዮን ጦር ይዞ ዓድዋን እንዲይዝ አድርጎ የቀረው የጄኔራል አሪሞንዲ ጦር ደግሞ ራስ መንገሻን እንዲከታተል አደረገ ። ራስ መንገሻም ከሸዋ ጦር ሳይመጣ የተደራጀውን የኢጣልያን ጦር ብቻቸውን መውጋት ትርፉ ሰው ማስጨረስ መሆኑን ስለገመቱ ፣ ከመቀሌ ወደ እንጣሎ ፣ ከእንጣሎም ወደ ደብረ ኃይላ ተጓዙ ።[2]

ጄኔራል ባራቲዬሪ ፣ በኮዓቲት ጦርነት ቆስሎ ለሚያጣጥረው ለቴኔንቲ ሳንጉይኔቲ እተኛበት ድረስ ሔዶ ፣ “ድሉ የኛ ሆኗል” ቢለው ፣ “ይኸን ሰምቼ ብሞትም ግዴለም” የሚል ቃል ከወረወረ በኋላ ወዲያው አንገቱን ዘለስ አድርጎ ሞተ ። ጄኔራል ባራቲዬሪ የኮዓቲትንና

---

1 Douze ansen Abyssinie ... Chap. 19, PP. 385 - 389.
2 Ibid. Chap. 28 - 29



የሰንዓፌን ጦርነት እያጋነነ ድል ማድረጉን ወደ ኢጣልያ አገር ቴሌግራም አስተላለፎ ነበርና ንጉሡ ኡምቤርቶ ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክርስፒ ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ባሮን ብላን ፣ የጦር ሚኒስትሩ ሞቼኒ ወሬውን እንደሰሙ በበኩላቸው በደስታ ተቀብለው እንኳን ደስ አለህ የሚል የደስታ መግለጫ አከታትለው ላኩለት ። የሁሉንም እዚህ ላይ ማስፈር ስለማይቻል ፣ የንጉሡንና የጠቅላይ ሚኒስትሩን ብቻ እንመልከት ።

ሮማ 18 ቀን 1895 ዓ . ም

> በኮዓቲትና በሰንዓፌ የኢጣልያ ጦር ማሸነፍ ፣ ሥልጣኔ በአረመኔ ላይ ያገኘው አዲስ ድል ነው ። ብልህነት በላለው አመራርዎ የደስታዎ ተካፋይ ነኝ ። ሦስት ቀን ሙሉ ቁጥሩ 3 እጅ ከሚበልጠው ጠላት ጋር በደስታ ራሳቸውን ሠውተው ጦርነቱን ለተካፈሉት ለበላይና ለበታች መኰንኖች ለወታደሮችም ባለውለተኛ መሆኔን እንዲያስረዱልኝ ። እርስዎን የመሰለ ጀግናና ብልህ መሪ ሲመራቸውና እነዚህን የመሰሉ ወታደሮች ሲኖሩ ፣ በመጭው ጊዜ ቅኝ ግዛታችንን ምንም ዓይነት ተንኮልና አደጋ ሊያስፈራው አይችልም ።

ኡምቤርቶ

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ደግሞ በበኩሉ ፣

> በአበሾች ላይ በተገኘው ድል ካንተና ከኢጣልያ ጋር የደስታ ተካፋይ ነኝ ። የወታደሩን ጀግንነት ብቻ ሳይሆን በጋሪባልዲ አርአያ በትንሽ ጦር ኃይለኛውን ጦር ለማሸነፍ የቻለው የመሪው ችሎታ ነው ። እንግዲህ የትግሬ አገር ለኢጣልያ የተከፈተ ነው ። ሳንይዘው ብንቀር የኛ ስንፍና ነው ።[1]

ክሪስፒ

በዚህ ዓይነት ፣ በኮዓቲትና በሰንዓፌ ጦርነት ባንድ በራስ መንገሻ ላይ ያገኙት ጊዜያዊ ድል ከንጉሡ ጀምሮ የኢጣልያን ባለሥልጣኖች አርክቶአል ። እንደዚሁም ይኸው ድል ተጋኖ በኢጣልያ ጋዜጦች ስለተጻፈ ፣ ሕዝቡም ሁሉ በደስታና በኩራት ተሞላ ። ከዚህ በኋላ ፣ በጄኔራል ባራቲዬሪ ይልቁንም በምክትሉ በጄኔራል አሪሞንዲ ትእዛዝ እነጋልያኖ ፣ እነቶዜሊ በየመስመሩ ወደ ዓድዋ ፣ ወደ መቀሌና ወደ አዲግራት እየገሠገሡ ፣ በየከተማው እየመሸጉ መደላደል ፣ በየወረዳው ሹም ሽር ማድረግ ያዙ ። ይኸን ሁሉ ሲያደርጉ ከሸዋና ከተቀረው ኢትዮጵያ በንጉሠ ነገሥቱ ተመርቶ ወደፊት የሚመጣው ጦር ፣ ይኸን የደስታ

---

1 Adua Bellavita - PP. 185 - 186; Italiani in Africa Orientale -A. DelBoca, PP.531-561.

ሁኔታ እንደሚለውጠው ሮማም ሆነ ምጥዋ ያሉት ባለሥልጣኖች ደህና አድርገው አላጤኑትም ። በመንግሥት ደረጃ በትንሹ ድል የሚታለሉና የሚደሰቱ የዋሃንና አዙረው ተከታዩን የማይመለከቱ እንደ ኢጣልያ ባለሥልጣኖች ያሉ በዓለም ብዙዎች ናቸው ለማለት ያዳግታል ። ሆኖም አባቶቻቸው ሮማውያን ኃያላን ለዓለም ብዙ የሥልጣኔ ቅርስ ያተረፉ ፈላስፎችና ዐዋቂዎች እንደነበሩ ፤ አሁንም በመካከላቸው ቁጥራቸው ይነስ እንጂ ፤ ታላላቅና አስተዋዮች እንዳሉባቸውና ያሁኑም ጊዜያዊ ድል እምብዛም ያላስደሰታቸው የምክር ቤት አባላትና ጋዜጠኞች እንደነበሩ አይካድም ።



# ምዕራፍ ሐያ

## የጄኔራል ባራቲዬሪ ሮማ ደርሶ መመለስ

ከ1886—87 ዓ. ም. መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ መጀመሪያ በሐላይ ከደጃች ባሕታ ሐጎስ ጋር ፤ ቀጥሎም በኮዓቲትና በሰንዓፌ ከራስ መንገሻ ጋር በተደረጉት ጥቃቅን ጦርነቶች የኢጣልያ ወታደሮች ስለ ቀናቸው ፤ ባራቲዬሪ ራሱን እንደ ትልቅ ድል አድራጊ ቆጥሮአል ። ወሬውም በኢጣልያ ጋዜጦች እየተጋነነ ተጽፎአል ። ከሮማ የደስታ መግለጫ ከንጉሡና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድ ለጄኔራል ባራቲዬሪ የተላከለት ከመሆኑ በቀር ፤ ኒሻን ተሸልሞ ወታደራዊ ማዕረጉም ከማዦር ጄኔራልነት ወደ ሌተና ጄኔራልነት ከፍ ያለው በዚሁ ጊዜና ሰበብ ነው ።

የባራቲዬሪ ያሸናፊነት ጀብዱው ፤ የአጥቂነት ዘዴው በሮማ ጋዜጦች እየተጋነነ የተጻፈው እስከ ጀርመን አገር ድረስ አስተጋብቶ የቃል ኪዳን ጓደኞቻቸው የሆነው የጀርመን ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ጉዮም የደስታ መግለጫ ልኳል ። በተጨማሪም በቴሌግራም ወዳጁን የኢጣልያን ንጉሥ ኡምቤርቶን አስፈቅዶ ለባራቲዬሪ ከፍተኛ የጀርመን ኒሻን እስከ መላክ ደርሷል ።[1]

በዚህ ሁሉ ምክንያት ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ከባሪቲዬሪ ጋር በቅኝ አገር ወረራ ከመስማማታቸውም በላይ ፤ የፖለቲካ ትብብርና የግልም ወዳጅነት ነበራቸው ። በመሆኑም በኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን የመስፋፋት ጉዳይ ለመመካከርና ወዲያውም ሮማን በመጐብኘት የድል አድራጊነቱን የደስታ መግለጫ ከሕዝቡ እንዲቀበል ወደ ሮማ እንዲመጣ ጥሪ አደረገለት ። ስለዚህ ጄኔራል ባራቲዬሪ ፤ በዚሁ ዓመት (1887 ዓ.ም.) ከምጥዋ በመርከብ ተሳፍሮ በሐምሌ ወር ሮማ ሲደርስ ፤ ሰው ሁሉ ከመንገድ ላይ ወጥቶ በመሰለፍ በጭብጨባና በሆታ ላንድ ድል አድራጊ የሚገባ የክብርና የደስታ አቀባበል አደረገለት ።

---

1 La Prima Guerra d' Africa, Crispi, p. 297.

ከንጉሡና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ከተገናኘ በኋላ ፣ ወደ ዋናው
ምክር ቤት በገባ ጊዜ የምክር ቤቱ አባሎች ቆመው ስሙን እየጠሩ
በሆታና በጭብጨባ ተቀበሉት ። ከዚያ ቀጥሎ ሃምሳ ቀናት ያህል
በሮማና በኢጣልያ ዋና ዋና ከተሞች በተዘዋወረበት ጊዜ ፣ የተደረገ
ለት አቀባበልና በፊቱ የተነገረለት ዲስኩር የጄኔራሉን የኩራት መን
ፈስ አሟሙቀውለት ነበር ።[1]

በሮማ ፣ በዋናው ምክር ቤት ፣ ከኢትዮጵያ ጋር ስለ ተደረገው የው
ጫሌ ውልና በተለይም ስለ አጨቃጫቂው 17ኛው አንቀጽ የፈረን
ሳይና የመስኮብ መንግሥታት ኢትዮጵያን ደጋፊነት ፣ የኢትዮጵያም
ሕዝብ ስለ ነጻነቱ ያለው ተዋጊነት ፣ የምኒልክ ሰላም ፈላጊነታቸው
ባንድ ወገን ፣ የጦር ድርጅታቸው በሌላው ወገን እየተወሳ ብዙ ክርክር
ይደረግበት ነበር ። የንጉሡ የኡምቤርቶና የጠቅላይ ሚኒስትሩ የክሪ
ስፒ የቀኝ ክፍል ወገኖች ኢትዮጵያንም ፣ ንጉሡ ነገሥቱንም በንቀት
ዐይን እየተመለከቱ ጦርነቱ በቀላሉ ኢትዮጵያን እንደሚያንበረክክ ተማ
ምነዋል ። በዚህ አያያዝ ፣ "ይኸ ጦርነት አደገኛ ሁኔታ ላይ ሊጥለን
ይችላል" የሚሉትን የግራ ወገኖችና በጠቅላላውም ጦርነቱን የሚቃ
ወሙትን ሶሺያሊስቶችን ለማግባባት ይጣጣሩ ነበር ።

ባሁኑ ጊዜ ፣ እንደ ክሪስፒ ቅኝ አገር የጠማውና የኢትዮጵያንም
ጦር በቀላሉ ለማሸነፍ ይቻላል ብሎ ያመነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስ
ትሩ ሲኞር አልቤርቶ ብላን ነው ። በምክር ቤቱ ስለ ኢትዮጵያ
ጉዳይ ክርክር በተፋፋመበት ሰዓት ፣ ለተቃዋሚዎቹ ክፍሎች የውጭ
ጉዳይ ሚኒስትሩ የሰጠው መልስ እንደዚህ የሚል የእብሪት አነጋገር
ነበር ።

> . . .የቅኝ አገር ይዞታችን አደገኛጠባይ ቢኖረው ኖሮ አገረ ገዢው
> (ባራቲዬሪ) ወደ ቅኝው ግዛት አይመለስም ነበር ። የባራቲዬሪ ጉዞ
> የሚያጽናና እንጂ አሥጊ ነገር የለበትም ። መስኮብም በኢትዮጵያ ላይ
> ከሃይማኖት ግንኙነት በቀር ሌላ ጥቅም ስለሌለው በዚህም በኩል
> አሥጊ ነገር የለም ። የውጫሌ ውልም ምኒልክ እየቀለደ ባይቀበለውም
> የመጽናቱ ነገር ውልውል የለውም ። ምኒልክም በሸፈተበት አቅዋም
> የከፈተውን የጠብ አስተሳሰብ ኢጣልያ በመሰላት ጊዜና ምቹ ሁኔታ
> ታደላድለዋለች . . .

ይኸውም ማለት የሚገባውን ቅጣት እንሰጠዋለን ለማለት ነው ።

በዚህ ዓይነት ፣ ሲኞር ብላንና አለቅየው ክሪስፒ የኢትዮጵያን
ነጻነት በቀላሉ ገፎ ለኢጣልያ የቅኝ አገር ልብስ ለማድረግ ነገሩን

2 L'Italia ed Etiopia, Conti Rossini, PP. 143-146.



ሁሉ ቀላል አድርገው ተመልክተውታል ። ለዚህም አቅዋም ዋነኛው
ምክንያት ፣ በቅርብ ጊዜ በኮዓቲትና በሰንዓፌ በራስ መንገሻ ላይ
ባራቲዬሪ ባገኘው ጊዜያዊ ድል ነው ። ስለዚህም እላይ የተናገረውን
ዲስኩር በመቀጠል ፣ እንደዚህ ሲል ይደመድማል ።

> ኢጣልያ በአፍሪካ የመሸነፍ አደጋ ያገኛታል ብሎ ያሰበ ሰው እን
> ዳለ ሒሳቡን ተሳስቷል ። በከዳተኛውና በሽፍታው (በምኒልክ) አንጻር
> ኢጣልያ ወደፊት መገሥገሥና መስፋፋት ስትችል ፣ በቁጥብነትና በመ
> ከላከል አጋሚንና ትግሬን በመያዝ ብቻ ተወሰነች ። ኢትዮጵያ
> በዚህ በተንኮሏ ተግባር የጸናችበት እንደሆነ ለነዚህ አረመኔዎች የምን
> ሰጠው መልስ ይህ ነው ። "ከሸዋ ተነሥታችሁ ባሪያና ከብት እንዘር
> ፋለን ብላችሁ እስከ ትግሬ ዘልቃችሁ የኢጣልያን ቅኝ አገር የተ
> ነኮሳችሁ እንደሆነ ፣ በፈጣን መርከብ የሚገሠግሡት የባታዮ ተዋጊዎ
> ቻችን በፍጥነት በመድረስና ጄኔራል ባራቲዬሪን በመርዳት እናንተን
> አሸንፈው አዲስ ቅጣት ይሰጧችኋል ።

ይኸን የመሰለውን የድንፋታ አነጋገሩን በምክር ቤት ያሉት አባ
ሎች አብዛኞቹ በጭብጨባ ተቀበሉት ። ሁኔታውን ለጊዜው ሶሺያሊስ
ቶቹም ለመቀበል ተገደዱ ። በዚህ ዓይነት በደስታ የጋለ መንፈስ
ራሱ ባራቲዬሪ ፣ ምኒልክን ለመምታትና ለማሸነፍ 10,000 ወታደርና
ከ10 እስከ 15 ሚሊዮን ሊሬ እንደሚበቃው ገለጸ ። ይኸም ሁሉ ሲሆን
ምኒልክ ከሸዋ ወደ ትግሬ ተጉዘው የኢጣልያን ጦር ለመውጋት እን
ደማይደፍሩ ያምን ነበር ።

የሆነ ሆኖ ፣ ጄኔራሉ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ፣ ከመከላከያው ፣ ከውጭ
ጉዳዩና ከገንዘብ ሚኒስትሮቹ ጋር በየጊዜው ተገናኝቶ በአቆርዳት ፣
በከሰላ ፣ በኮዓቲት ጦርነቶች ላይ የተጓደለው የጦር መሣሪያም ፣ የሰ
ውም ፣ የጭነትም ከብት ቁጥሩ ከፍ ብሎ እንዲሟላ ጠየቀ ። በተለይ
ከመረብ በለሳ ሙና አልፎ ባሁኑ ጊዜ የኢጣልያ ግዛት ስለ ተስፋፋ
ለጠቅላላው ለጦርነቱም ዝግጅት ፣ ለሰላማዊ አስተዳደርም የሚያስ
ፈልገውን ወጭ ከዘጠኝ ሚሊዮን ሊሬ ወደ ዐሥራ አራት ሚሊ
ዮን* ከፍ አስደረገ ። በተረፈ ለዝርዝር ጉዳዮች ሙሉ የደጋፊነት ተስፋ
ከየባለሥልጣኖቹ ተቀብሎ በመስከረም ወር ተመልሶ አሥመራ ገባ ።

ራሱ ከዓድዋ ድል በኋላ በጻፈው መጽሐፍ ፣ ከሮማ ወደ አሥመራ
በተመለሰበት ጊዜ የነበረውን መንፈሱን በገለጸበት ምዕራፍ ላይ ፣

> . . . ወደ ምጥዋ ለመመለስ ተነሣሁ ። ካቢኔው (ሚኒስትሮቹ) ሁሉ
> እንደኛው ያገራችንና የቅኝ አገሩ ጉዳይ በልቡ እንዳለና ባገር ፊት
> ኃላፊነት እንዳለበት አምኜ ነበር ። መላዋ ኢትዮጵያ በክንዳችን ላይ

* በዚያን ጊዜ አንድ የማሪያ ቴሬዛ ብር 4 ወይም 5 ሊሬ ይመነዘራል ።

ስትወድቅ በኢጣልያ አገር ሁሉም የተሰናዳ ነው ብዬ በማመን እኔም
በጦር አለቆቼ እየተረዳሁ በምፈጽመው ሥራ የጠላትን ቁጥር ቀንሼ
ሰላም ለማስገኘት ይቀናኛል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር . . . ሲል
ጽፏል ።[1]

የዚህም አሳብ መደምደሚያው ፣ በኢጣልያ አገር ቅኝ ግዛትን
አስመልክቶ የርሱን ምኞትና ጥያቄ ለማሟላት ባለሥልጣኑ ሁሉ
ኃላፊነት እንዳለበት አምኖ ነበር ። በኢትዮጵያም ባያለበት የተሠራ
ጨው ስላይ ባቀረበለት የስነድ ማስታወሻ በመተማመን ሕዝቡን
ከነባላባቱ በመከፋፈል የኢትዮጵያን አቅዋም ለማዳከም ሞክሯል ።
የተዋጊውን ጠላት ቁጥር በውጊያም ፣ በዘዴም ቀንሶና የራሱን በማ
በርከት ድል አድራጊነት ለመጐናጸፍና ለኢጣልያ ሰፊ ግዛት አውርሶ
በሰላም ለመግዛት ነበር ።

በዚህም ጊዜ ፣ በኢትዮጵያ ኃይለኛ መሪና ጽኑ ተዋጊ ሕዝብ
አጋጥሞት ከሸፈበት እንጂ ፣ ይኸን የመሰለው ምኞትና ጉጉት
የርሱ ብቻ ሳይሆን ፣ የሁሉም የኢጣሊያ ባለሥልጣኖች አስተያየት
ነበር ። ይኸም ሁኔታ በሌላው ባልሠለጠነው የእስያ ፣ የደቡብ አሜሪ
ካና በተለይም በአፍሪካ ዓለም የተፈጸመ ስለሆነ ፣ አስተያየቱ በዚያን
ሰዓት ለማንም የታወቀ ነው ። በዚያን ጊዜ ሥልጡኖቹ አውሮፓው
ያን ባልሠለጠነው ክፍለ ዓለም እየተሻሙ ቅኝ ግዛት እንደ ቅርጫ
ሥጋ የተካፈሉበት ዘመን ስለሆነ ሊያስገርም አይችልም ። ባራቲዬ
ሪም አለቆቹም እንደ ሞኝ አይቆጠሩም ።

ዠኔራል ባራቲዬሪ ፣ ከኢጣልያ አገር ተመልሶ አሥመራ እንደ
ገባ ከርሱ በታች የኤርትራንና አዲስ የተወረሩትን ወረዳዎች ሲያ
ስተዳድር ከቆየው ከዠኔራል አሪሞንዲና ከቀሩትም የፖለቲካና
የጦር ሹማምንት ጋር ተገናኝቶ በሚነጋገርበት ሰዓት ፣ ራስ መን
ገሻ ከእንጣሎ በስተደቡብ ሆነው እንደገና ለውጊያ መዘጋጀታቸ
ውንና ከሸዋም እርዳታ ሊደርሳቸው ነው እየተባለ መወራቱን ሰማ ።
ይኸንኑ እንዲያውቁት ያህል ፣ ወደ ሮማ ላለቆቹ በቴሌግራም ካስታ
ወቀ በኋላ ራስ መንገሻንም ለመምታት ፣ ግዛቱንም የበለጠ ወደ ደቡብ
ክፍል ለማስፋፋት እንዲመቸው ዋና መቀመጫውን ከአሥመራ ወደ
አጋሜ ከተማ ወደ አዲግራት አዛውሮ በዚያ መሽጎ ተቀመጠ ።[2]

1 Memoire d'Afrique - Baratieri, Chap. XIV.
2 La Prima Guera d' Africa . . ., PP. 297 - 300. Adua, Bellavita, PP. 186 - 196
Gli Italiani in Afriea Orient - Angelo Del Boca, Chap. IX, PP. 531-558.



# ምዕራፍ ሐያ አንድ

## የደብረ ኃይላ ጦርነት

ዤኔራል ባራቲዬሪ ፣ ሮማ ሔዶ በሮማ ምክር ቤት በየከተሞ
ችና በየግብዣው ላይ እንደ ድል አድራጊ ዤኔራል ፣ ለኢጣልያ ሰፊ
ግዛት እንደሚያወርስ የጦር መሪ ተቆጥሮ ሲመሰገንና ሲወደስ ሰን
ብቶ ወደ አሥመራ ተመለሰ ። ወዲያውኑም መንግሥቱና ሕዝቡ በርሱ
ላይ የጣለውን እምነት ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ተዘጋጀ ። አሥመራም በደ
ረሰ ጊዜ የጦር ሹምምንቱ ዤኔራል አሪሞንዲ፣ ማዦር አሜሊዮ ፣ ማዦር
ቶዜሊ ፣ ማዦር ጋልያኖ ባለፈው የኮዓቲትና የሰንዓፌ የጦርነት ድል
የተደሰቱና ለወደፊቱ ጦርነትም የጓጉ ስለነበሩ ፣ የርሱና የነርሱ ምኞት
ባንድ ኢትዮጵያን የመውረር ዓላማ ላይ የተመሠረተ ነበር ። ይኸም
አገር ለጊዜው የኢትዮጵያ ሰሜናዊው ክፍል ትግሬና ትግራይ ፣ ወሎ
ጭምር ነው ። የቀረውም እንደ ጊዜው አመቺነትና ሁኔታ የሚፈጸም
ነው ተብሎ ተወስኗል ።

በዤኔራሉ አጠገብ ያለው ጦር ሠራዊት ፣ ለጊዜው ከዚህ እንደሚ
ከተለው ነው ። 116 የጦር መኰንኖች ፣ 672 የነጭ ወታደር ፣ 8065
በጦር ትምህርት የሠለጠነ ያገር ተወላጅ ወታደርና ሌሎች ቁጥራቸው
በብዙ መቶ የሚቆጠር ጀሌ ጦር ነበር ።

በዚሁ ጊዜ ፣ ራስ መንገሻ ደብረ ኃይላ ሆነው የወታደራቸው
ቁጥር ከ፬ሺ እስከ ፭ሺ ይደርስ ነበር ። በነዚህ ላይ ደግሞ ፣ አንድ ሺ
አምስት መቶ የሚሆኑ ከሸዋ መጥተው የተጨመሩና ከ፪ሺ እስከ ፫ሺ
የሚደርሱ ያገር ተወላጆች በከተት ዓዋጅ የተሰበሰቡ ነበሩ ። ከአዲስ
አበባ የተላከላቸውንም የጦር መሣሪያና ገንዘብ በከረጢት ለየሰዉ
እንደሚያድሉ ባራቲዬሪ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ በጻፈው ማስታ
ወሻ አረጋግጧል ። ከዚሁ እያይዞ ራስ መንገሻ ከደቡብ ክፍል ከየጁ
ከራስ ወሌ ፣ ከላስታ ከዋግሹም ጓንጉል ዘንድ እርዳታ ይጠባበቁ
እንደ ነበርም ገልጿል ። ዋና አማካሪያቸው ሹም አጋሜ ተስፋዬም ፣
(ከሰንዓፌ ጦርነት በኋላ የአጋሜው ግዛት የሔደባቸው) አብረው
እንደነበሩ ይጠቁማል ። በክረምቱ ጊዜ በነርሱ ሥልጣን ውስጥ
ያሉትን ሹማምንት ራስ መንገሻ ወደ ራሳቸው ለመሳብ ያባብሉ

እንደ ነበርና በዚሁ መሠረት ደጃች ተድላ አባ ጉበን ራስ መንገሻ አስረዋቸው ሳለ ፣ ከአራት ወር በፊት ማዦር አሜሊዎ ከእስራት አውጥቶ በማዦር ቶዜሊ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ተሰጥቷቸው የነበሩት በአሁኑ ጊዜ አምልጠው ከራስ መንገሻ ጋር እንደ ተደባለቁ ያስረዳል ። የቀሩትም በሁለት አሳብ ላይ በመዋለል ስለሚገኙ ፣ መንገሻን አዘንግቶ በመውጋት የሸዋ ጦር ወደ ሰሜን ከመድረሱ በፊት አንድ የጦር ግዳጅ ፈጽመን ኃይላችንን ለማስተማመንና ራስ መንገሻንም ውጊያ እንዲያደርጉ ለማስገደድ ስናስብ ፣ እርሳቸውም በበኩላቸው ፣ "ሕይወቴን እንደ ቴዎድሮስ እዚሁ እጨርሳለሁ እንጂ ፣ ሁለተኛ ከኢጣልያኖች ፊት አልሸሽም"[1] ማለታቸውን ከሰላይ እንዳገኘው ያረጋግጣል ።

ደብረ ኃይላ ፣ ባእንደርታና በሰለዋ መካከል እንጣሎ አጠገብ የሚገኝ ተራራማ ሥፍራ ነው ። ስለዚህ እንደ ዤኔራል ባራቲዬሪ ግምት በዚህ ተራራማ ሥፍራ ከነሠራዊታቸው የሚገኙትን ራስ መንገሻን አደጋ ጥሎ አንድ ጊዜ ለዘለቄታ በመደምሰስ የትግሬን ግዛት በእጁ ካስገባ በኋላ ፣ ከደቡብ የሚመጣውን ጦር በደንብ ለመቋቋም ነው ።

በወዲህ በንጉሠ ነገሥቱ በኩል ፣ ከወላሞ ዘመቻ መልስ የመስኮብ መንግሥት መልክተኞችን ተቀብለው ካስተናገዱና የራሳቸውንም መልክተኞች እነፊታውራሪ ዳምጠውን ከላኩ በኋላ ፣ የጦርነት ዓዋጅ ዓወጁ ። የክረምቱ ጊዜ በዚህ ዓይነት አለፈ ።

አንባቢ እንደሚያስታውሰው ፣ ከሰንዓፌው ጦርነት በኋላ ፣ ሹም አጋሜ ተስፋዬ የኮዓቲትንና የሰንዓፌን የጦርነት ወሬ ፣ የኢጣልያኖቹን ወረራ ለዐፄ ምኒልክ ነግረዋቸው ነበር ። እሳቸውም ከመተማ ጦርነት ወዲህ መጥተው በየዳር አገሩ በሹመት የነበሩትን የትግሬ መኳንንት እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን ሔዳችሁ ራስ መንገሻን እያገዛችሁ ቆዩ ፤ እኛም መጣን እንደርስባችኋለን አሏቸው ።

ባሁኑ ጊዜ ፣ ከራስ መንገሻ ጋር ያሉት የጦርና ያስተዳደር መኰንኖች በፊት ከነበሩት ከነሹም አጋሜ ተስፋዬ ፣ ከነራስ ሐጐስ በቀር አዳዲሶቹ ካፒቴን ቤቲኒን ገድለው ወደ ሸዋ የመጡት ደጃች አበራ ፣ ደጃች ተድላ አባ ጉበን ፣ ከሸዋ በቅርብ የመጡት ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ፣ ፊታውራሪ ንጉሤ ፣ ቀኛዝማች አንዳርጋቸው ፣ ግራዝማች ኃይለ ማርያምና ባላምባራስ በየነ አሉ ።[2]

1 Memoire d' Afrique . . Chap. 15, PP. 213 - 215
2 Ibid, P.218



በዚህም ጊዜ ፣ በዤኔራል ባራቲዬሪ ውሳኔ ከሦስት የተከፈለ ጦር በሦስት መስመር ከዚህ እንደሚከተለው ከአዲግራት ወደ ደብረ ኃይላ እንዲዘምት ተደረገ ።

፩ኛው የግራ ክፍል ጦር በማዦር ቶዜሊ መሪነት በአጽቢ በኩል ፣ ፪ኛው በመካከል የሚዘምተው ዋነኛው ጦር በጋልያኖ እየተመራ ግንባር ቀደም ሆኖ ከአዲግራት በአጉላዕ በኩል ወደ ይሎ ከዚያ በሽሊቆት በእንጣሎ በኩል ፣ ፫ኛው ያገር ተወላጅ ጦር ያለበት በማዦር አሜሊዎ የሚመራው በሐውዜን በኩል ተጉዞ እ. ኤ. አ. ጥቅምት 9 ቀን 1895 ዓ.ም. ደብረ ኃይላ ደረሰ ።

ዋናው አሳብ ፣ አዘንግቶ በድንገተኛ አደጋ ራስ መንገሻን ከነሰዋቸው ለመደምሰስ ስለሆነ ፣ በውስጥ ዐወቅ ባላገሮች እየተመሩ በስላች መንገድ ደብረ ኃይላ መድረሳቸው ታወቀ ። በዚያን ጊዜ ፣ በራስ መንገሻ ዘንድ ምክር ተይዞ ፣ ". . . ከእንግዲህ ወዲያ ከዚህ መሸሸ ለኛ ውርደት ነው ። ቢቀናን ተዋግተን አሸንፈን እንመለሳለን ። ባይቀናንም ስለ ሀገራችን ተዋግተን እንሞታለን ። እርስዎ ግን ቢማረኩም ፣ ቢሞቱም ፣ ላገር ውርደት ለኢጣልያ ደስታ ነውና ከሸዋ ጦር እስኪመጣ ድረስ ወደራስ ወሌ ግዛት ወደ ሰለዋ ተጠግተው ቢቆዩ ይሻላል" ብለው ራስ መንገሻን መከሩዋቸው ። የራሳቸውም አሽከሮች መቀሌ በነበሩበት ሰዓት ፣ "ጦርነቱን ለማድረግ ካፄ ምኒልክ ፈቃድ አላገኘንምና እንደዚሁ ወደ ሸዋ እየተላላከን ዝም ብለን በእንጣሎ እንቀመጥ" የሚል አሳብ ቀደም ብለው አቅርበው ነበር ።

ከዚህ በኋላ ፣ ራስ መንገሻ አሳባቸውን ተቀብለው ከደብረ ኃይላ ወደ ሰለዋ ተጓዙ ። እነቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ግን ፣ እዚያው ደብረ ኃይላ ሆነው ሲጠባበቁ በማዦር አሜሊዎ የሚመራው ያገር ተወላጅ ግንባር ቀደም ወታደር መንደር ሲያቃጥል አዩት ። ከዚያ የሁለቱ ወገን ወታደር ተቀራርቦ ሲዋጋ ፣ ምንም እነዚህ በርትተው ለመመከት ቢፈትኑ የኢጣልያኖቹ ወገን በመሣሪያ ጥራት ፣ በሠራዊት ብዛት ስለበለጠ ፣ በቀላል ጦርነት አሁንም ጣልያኖቹ አሸነፉ ። ከኢጣልያኖች ወገን የሞተው 11 የቆሰለው 30 ሲሆን ፣ ከኢትዮጵያ በኩል የሞተው 30 የቆሰለው አንድ መቶ ግድም መሆኑን ባራቲዬሪ[1] ሲያመለክት ፣ ከኢጣልያ ወገን ሟቾቹ ሁሉም ያገር ተወላጆች መሆናቸውን ቤላቪታ ይገልጻል ።[2]

1 Memoire d'Afrique . . P. 218
2 Adua - E. Bellavita, P. 540

በጦርነቱም ላይ ትንሽ ጦር ይዘው ገትረው በዝግንነት የተዋጉት
ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ከፉኛ ቆስለው ተማረኩ ። ከሸዋ የመጡ
መሆናቸውን ስላወቁ ፣ በሸዋ ያለውን ወታደራዊ ድርጅትና የጦር አቅዋም
ማዠር ሳልሳና ጋዜጠኛው ሜርካቲሊ ሲጠያይቁዋቸውና በዚሁ ጊዜ ቴኔ
ንቲ ሞዜቲ በእንጣሎ ሲያክማቸው ሰነበተ ። ቀጥሎም በደንብ ታክመው
ሲድኑ መሣሪያ ይሆኑናል በማለት ከእንጣሎ ወደ አሥመራ አዛወሯ
ቸው ። ጋዜጠኛው ሜርካቴሊ ከደብረ ኃይላ ምርኮኞች የተገኘ ወሬ
ብሎ ለማስጠንቀቅ በጻፈው ላይ ፣ "ምርኮኞች ያሁኑ ጦርነት ምንም
አይደለም ፤ እውነተኛውን ጦርነት ከአንድ ወር ዐሥራ ሁለት ቀን
በኋላ ታገኙታላችሁ ብለዋል" ይልና ከሁለት ቀን በኋላ ደግሞ ፣ "ሸዋ
ለጦርነት ተዘጋጅቷል ፣ ትልቅ ጦርነት ሳይሆን አይቀርም ፣ የንጉሡ
ሠራዊት በሚያቀባብል ጠመንጃና በብዙ ጥይት ታጥቋል ። መድፍና
መትረየስም በብዛት አግኝቷል ፣ ወታደሩም ዘወትር ተኩስ ይማራል"
ብለው ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም እንደ ነገሩት በጽሑፍ ያመለከታል።[1]

ምንም እንኳን ፣ አንዳንድ ጊዜ ጠንክረው ማጥቃት ወይም መከ
ላከል ቢችሉም ፣ የኢጣልያኖች ጠባይ አብዛኛውን ጊዜ አሸናፊ ሲገጥማ
ቸው ሽሽታቸውና መርበድበዳቸው ከመጠን በላይ ሲሆን ፣ በዚያው
መጠን ተሸናፊ ያገኙ እንደሆነ ጉራቸውና ኩራታቸው የበዛ ነው ።
በደብረ ኃይላ ፣ ያውም ራስ መንገሻ ሳይገጥሙ ፣ ቁጥሩ በጣም ባነሰ
ጦር ላይ ስለ ቀናቸው ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሁሉም በደስታ ወደፊት ይገ
ሠግሡ ጀመር ። በሸዋ የሚደረገውን የጦር ዝግጅት ቢሰሙትም ከንቀት፣
የተነሣ እንሸነፋለን ብለው በፍጹም አልጠረጠሩም ።

በዚህ ዓይነት ፣ ከደብረ ኃይላ ጦርነት በኋላ ወደፊት እየገሠገሡ
እስከ አላጌ ፣ ከዚያም አልፈው አሸንጌ ሐይቅ ድረስ ዘልቀው በደረሱ
በት ሹም ሽር ማድረግ ፣ ምሽግ መመሸግና ወታደር እየሰበሰቡ ለው
ጊያ መዘጋጀት ያዙ ። በዚሁ ጊዜ በራስ መንገሻ ትእዛዝ አምባ አላጌ
ታስረው የነበሩትን ራስ ስብሐትን ዤኔራል አሪሞንዲ ከእስራት ፈትቶ
በአጠገቡ አስቀመጣቸው ። ውሎ አድሮም ከተመከረ በኋላ ፣ አጋሜን
እንዳይሰጣቸው ከርሳቸው በፊት የኢጣልያ ጦር ራስ መንገሻ የሾሟ
ቸውን ሹም አጋሜ ተስፋዬን አባርሮ የአጋሜን ግዛት ለራሱ ታማኝ
ለደጃች ሐጐስ ተፈሪ ሰጥቶ ነበር ።በዚህ ምክንያት ፣ አሁን ሐጐስ
ተፈሪን መሻር ስለማይቻል ፣ ለራስ ስብሐት ሁለት አውላሎን ጨምሮ
የእንደርታን ግዛት ሰጣቸው ። በእንዳ መሆኔም ደጃች አሊን ሾሞ
በበላይ ያስተዳድር ጀመር ።

---

1 Italia ed Etiopia . . .Conti Rossini PP. 164-170.



በዚህ መካከል ፣ በዋናው ጠቅላይ አዛዥ በዤኔራል ባራቲዬሪና
የትግሬና የአጋሜ ግዛት አስተዳዳሪ ብሎ በሾመው በዤኔራል አሪሞ
ንዲ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ ። ዤኔራል ባራቲዬሪ ፣ "እስከ አላጌ
ድረስ የያዝነው አገር ሰፊ ስለሆነ ፣ የያዝነውን እያጠናከርን እንደ
ጊዜው ሁኔታ ወደፊት እንራመድ ፣ ያለዚያ ከዋናው የጦር ሠፈር
ድርጅታችን ከምጥዋና ከአሥመራ ፣ ከአዲግራትም በጣም ርቀን 360
ኪሎ ሜትር አልፈን ስንሔድ ደህና አድርገን ወደማናውቀው ተራ
ራማ አገርና ሕዝብ መካከል ስንዘልቅ ፣ ቁጥጥሩም ግንኙነቱም ያስ
ቸግረናል" ሲል ፤ ዤኔራል አሪሞንዲ ፣ "አሁኑኑ የወታደራችን ሞራል
ከፍ ባለበት ሰዓት ወደፊት ገሥግሠን ከሸዋ ወደ አሸንጌ የሚጓዘ
ውን የሸዋን ጦር አለበት ድረስ ሔደን እንውጋው" አለ ።

ዤኔራል ባራቲዬሪ ፣ የዚህን ጉዳይ ከፖለቲካና ከጦር አማካሪዎቹ
ጋር ተመካክሮ እስከ አላጌና እስከ አሸንጌ ድረስ የያዝነው አገር ብዙ
ነው ። ስለዚህ በተያዙት አገሮች በሚገኙት ከተሞች በመቀሌ ፣ በዕ
ዳጋ ሐሙስ ፣ በእንጣሎና በደብረ ኃይላ ፣ በአላጌ ምሽጋችንን እያጸ
ናን ለዓድዋና ለመቀሌ ፣ ለምጥዋና ለአሥመራ አማካይ በሆነው
በአዲግራት ዋና መቀመጫችንንና የጦር ሠፈራችንን አድርገን ወታ
ደራችንን የበለጠ እናጠንክር ።በዚሁም ጊዜ የላስታን ሕዝብ እየሰበ
ከን ፣ የራያንና የአዘቦን ሕዝብ ከወሎና ከአውሳ ሕዝብ ጋር በማስተባ
በር ፣ በምኒልክ ላይ የሚነሡበትን መንገድ እያዘጋጀን እንቆይ የሚ
ለው የባራቲዬሪ አሳብ ጸና ።

# ምዕፍራ ሐያ ሁለት

## የኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያን መሳፍንት ከፋፍሎ ለማስነሣት ያደረገው የመጨረሻ ሙከራና ያፄ ምኒልክ ያጸፋ መልስ

ኮሎኔል ፒያኖ ፣ ከትራቬርሲ ጋር ከአዲስ አበባ ወደ ሮማ ከተመለሰ በኋላ ሁለቱ መንግሥታት በፊታቸው የተደቀነው በትክክል የኃይሉ መንገድ ብቻ ነው ። ላፄ ምኒልክ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትርም ፣ እንደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም ፣ እንደ መልካም አገረ ገዥም ሆነው የወን ድም ንጉሣቸውን በቅን ልቦና ፣ በትሑት ሕሊና የሚያገለግሉት ራስ መኰንን ፣ የኢጣልያን አገር የጦር ኃይሉን ድርጅት ፣ የመድፍና የመትረየሱን ፣ የጠመንጃውን ብዛት ከነፋብሪካው በየከተማው እየዞሩ ጐብኝተው ተመልሰዋል ። ይኸንኑ ለንጉሡ በዝርዝር ስለ ገለጹ ፣ ከእንደዚህ ያለው መንግሥት ጋር መዋጋት ዋዛ አለመሆኑን ምኒልክ ተረድተዋል ። አብዛኛውን ጊዜ ሌላው "እንበለው" ሲል እነርሱ የሰላም መንገድ ይከተሉ የነበረበት አንዱ ምክንያት ይኸው ነው ። ይሁን እንጂ ፣ የሰላም መልክ በሚያሳዩበት ጐን በሰላማዊ እነጋገር ኃያል የሆነውን የአውሮፓ መንግሥት እያዘናጉ የመሣሪያውን ስብሰባ ፣ የወታደሩን ድርጅት በግልጽም በስውርም በትጋት ማካሔዳቸውን ቀጥለው ነበር ።

የኢጣልያና የእንግሊዝ መንግሥታት ፣ ቀድሞ ከነበራቸው የወዳጅነት ውል በቀር እ.ኤ.አ. በግንቦት 5 ቀን 1894 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒና የእንግሊዝ እምባሳደር ሰር ፍራንሲስ ክላር ፎርድ ፣ ሮማ ላይ በውጋዴንና በእንግሊዝ ሱማሌ ወሰን ስላለው ጉዳይ የፕሮቶኮል ፊርማ ተፈራርመው ወዳጅነታቸውን አጽንተዋል ። በዚሁ ዓመት በሰኔ ወር ኮሎኔል ፒያኖ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ኢጣልያ በእንግሊዝ እንደ ተደገፈች ወሬው አዲስ አበባ ደርሷል ። የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ፣ እ.ኤ.አ. በ1843 ዓ.ም. ዠምሮ ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር የሸዋ ንጉሥ ወጥነውት የነበረውን የወዳጅነት ውል እንደገና በማደስ ፣ በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያና የፈረንሣይ ወዳጅነት ባዲስ መንፈስ ተቀስቅሷል ። በዚያው አንጻር ከመስኮቦች ጋር ያለው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተመሳሳይነት እየተጠቀሰ ፣ መስኮብና ኢትዮጵያ

መላከተኛ እየተለዋወጡ ወዳጅነታቸውን አጠባብቀዋል ። የኢትዮጵያ ዕድልም ይበልጥ ሲቃና በዚህ ጊዜ ፈረንሳይና መስኮብ ባንድ ወገን፣ እንግሊዝ በሌላው ወገን ሆነው ጀርመን ፡ አስትሪያ ፡ ኢጣልያ የተዋዋሉትን የሦስቱን የቃል ኪዳን ስምምነት (Triple Alliance) ለማፍረስ የጋራ ጐራ በመፍጠራቸው ሁኔታው ለኢትዮጵያ የፖለቲካም የወታደራዊ ጥቅምም ሰጥቷል ።

ዐፄ ምኒልክ ፡ ከነዚህ ሁለት መንግሥታት ጋር ወዳጅነታቸውን በሚያጠባብቁበት ጊዜ ፡ የኢጣልያ መሪዎችም እነፒያኖ ወደ ሮማ ከተመለሱ በኋላ ከምኒልክ በኃይልም ፡ በዘዴም የውጫሌን ውል የማጽደቁና የመረብን ወሰንነት የማግኘቱ ጉዳይ ከሸፎባቸዋል ። አሁን ያላቸው ምርጫ መሳፍንቱን እንደገና ባዲስ ስጦታና ተስፋ አባብሎና ገፋፍቶ በምኒልክ ላይ ክማስነሣቱ ላይ ዐርፏል ።

ፒያኖና ትራቬርሲ ፡ በሐምሌ ወር ላይ ኢትዮጵያን ለቀው ወደ አገራቸው ተመልሰው የመልእክታቸውን አለመሳካት በራፖር ለመንግሥታቸው አቀረቡ ። በሚቀጥለው በነሐሴ ወር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ክሪስፒ የሚከተለውን መመሪያ በምስጢር ለኤርትራው ገዥ ለጄኔራል ባራቲዬሪ እንደዚህ ሲል አስተላለፈለት ።

> ይቅርታ የማይደረግለት የምኒልክ አቅዋም አንድ የመከላከያ ፕላን እንድናበጅ ያስገድደናል ። በዮሐንስ ላይ ምኒልክን እንደ ደገፍን አሁን የምኒልክን ባላንጦች ማበረታታት አለብን ። በትግሬ መንገሻ ፡ በሐረር መኰንን ከግል ምኞታቸው በቀር በንጉሠ ነገሥቱ ላይ የጥላቻና የበቀል ምክንያት አያጡም ። ምኒልክ ሲሞት በኢጣልያ የበላይ ጠባቂነት ሥር የንጉሠ ነገሥታዊው ግዛት በደቡብና በሰሜን የተከፋፈለ ሁለት መንግሥት ሊሆን ይችላል ። በሌላም አኳኋን ለኛ በሚጠቅመን ረገድ ሌላ መንገድ ሊገኝ ይችል ይሆናል ። አሳቡን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ቀላል አይደለም ። ነገር ግን ሊሆን የሚችል ነው ። ክቡርነትዎ እጥማጅና ዘዴ በመፈለግ ከመንገሻና ከመኰንን ዘንድ ልንልካቸው ለስ ምንችለው ብልህነታቸው የተረጋገጠውን (ሰላዮችና ቀስቃሾች) ወኪሎች አሳብዎን እንደሚገልጡልኝ አምናለሁ ።[1]

ባሪቲዬሪ ፡ ከክሪስፒ ለተላለፈለት መመሪያ የሰጠውን መልስ ለጊዜው ማግኘት አልተቻለም ። ይህም ምናልባት አብዛኛውን ጊዜ እንደ

1. Italia ed Etiopia, Conti Rossini, P. 105 Italia in Africa, Angelo Del Boca, P. 508.



ዚህ የመሳሰለውን ምስጢራዊ ጉዳይ የሚለዋወጡት በቁጥር ቃል ስለ ሆነ ፡ ቁጥሩ ተፈትቶ እጽሑፍ ላይ ባለመስፈሩ ይሆናል ።

በዚህ ፈንታ ፡ ክዚህ ጉዳይ ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ሲኞር ብላን ከሮማ እ.ኤ.አ. በ16 መስከረም 1894 ዓ.ም ጥብቅ ምስጢር ብሎ ቁጥር 34947 ለዠኔራል ባራቲዬሪ ያስተላለፈለት ቃል እንደዚህ የሚል ነው ።

> ለክቡር የኤርትራ ቅኝ አገር ገዥ. . . በቁጥር 1563. . . ስለ ሐረር የጻፉልኝን ራፖር በምስጋና ተቀብያለሁ ።
>
> በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና (ክሪስፒ) በክቡርነትዎ መካከል በ10 ፡ በ11 ፡ በ12 ቀን ባለፈው ወር (ሐምሌ) ልውውጥ የተደረገው ቴሌግራም እኔም ወድጄ የተስማማሁበት በአቢሲኒያ ጉዳይ ለምናደርገው እርምጃ መመሪያችን ነው ። የምናደርገው ሁሉ በሰሜን በራስ መንገሻ ዘንድ ፡ በደቡብ በራስ መኰንን ዘንድ የኛ የበላይነት ስሜት የበለጠ ከፍ እያለ እንዲሔድ ማድረግ ነው ። እነሱን ከፋፍሎ በነዚህ ሁለት አውራጃዎች ላይ ኢጣልያ የበላይ ጠባቂነቷና በቁቁጥጥሯ ከጊዜ ጋር ሊረጋገጥ ይችላል ።
>
> የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ (ክሪስፒ) በትግሬ በኩል ላለው ለመቶ አለቃ ሙላዚኒ አስፈላጊውን መመሪያ እንዲሰጡት ፈቅደዋል ። እንደዚሁም በራስ መኰንን ዘንድ ለሚሆነው ለመጀመሪያው መረጃ አሰባሰብ ለካቫሊዬር ፌልተርም ፡ እንደዚሁም ምንም እንኳ አስቸጋሪ መሆኑ ቢሰማኝ ፡ በራስ መኰንን በኩል ላለው ጉዳይ ከፌልተር የተሻለና ከፍ ያለ ሰው መምረጥ እንዳለብን ይሰማኛል ። የሆነ ሆኖ ፡ ክቡርነትዎ ከመንግሥት ትእዛዝ ሳይጠብቅ የተመቸውን ጊዜ መርጠው ሥራውን ለመጀመር ትእዛዝ መስጠት ይችላሉ ።
>
> በኔ በኩል የምጨምረው በቅኝ እገዛዝ ፖለቲካችን ኢጣልያን በሚመለከተው ጉዳይ የሐበሻ ጉዳይ ታላቅ ቁም ነገር ያለው ሆኖ መገኘቱንና የዚህም ጉዳይና አሠራራችን ሁሉ ያሁኑም የመልእክታችን ልውውጥ ምስጢሩ በጥብቅ መጠበቅ አለበት ። ፊርማ ብላን ።

ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ የበለጠ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፍራንቼስኮ ክሪስፒ ፡ በተለይ በንጉሡ በኡምቤርቶና ቅኝ አገር በሚፈልጉት በቀኝ ክንፍ አማካሪዎች ዘንድ ታላቅና ብልህ መሪ ተብሎ ግምት የተጣለበት ነው ። በተደጋጋሚ ጠቅላይ ሚኒስትርነትንም የያዘው በዚሁ ምክንያት ነው ። ነገር ግን ፡ ኢትዮጵያ አሁን ያለችበትን የጠነከረ አቅዋም በትክክል ሳያጠና ይኸን የመሰለውን መመሪያ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አማካይነት በቀላሉ ሲሰጥና አሳቡ ከሥራ ላይ እንደሚውል ማመኑ ሞኝነቱን ወይም ችላ ባይነቱን ያሳያል ። በጠቅላላው ኢትዮጵያ ላይ የኢጣልያንን የበላይ ጠባቂነት በምኒልክ በኩል ፈትኖ አል ሆነለትም ። ይኸ ሁሉ ውዝግብ የተፈጠረውም በዚህ ምክንያት መሆኑን

እየተገነዘበው ፣ ሁለቱን መሳፍንት ራስ መኰንንንና ራስ መንገ
ሻን በምኒልክ ላይ በማስነሣት ፣ በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ ሁለት
መንግሥታት አቋቁሞ ፣ ኢጣልያ ከሁለቱ የመንግሥታት ኮርቻ ላይ
ተቀምጣ እንደልቧ ጋልባ መላ ኢትዮጵያን ለመግዛት እንድትችል
ከማሰብም ፣ ከመምከርም ወደኋላ ለማለት አልቻለም ።

ከርሱ ግምት ትናንት መረብ ላይ ወንጌልና መስቀል ቀርቦ በመ
ሐላ ከኢጣልያ መንግሥት ጋር ከተስማሙ በኋላ ፣ የተከዱት ራስ መን
ገሻ ፣ የተዋዋላቸው ጀኔራል ጋንዶልፊ ከተሻረና በርሱ እግር ከመ
ጣው ከባራቲዬሪ ጋር ንግግር እንኳ የተነፈጋቸው መስፍን ፣ ዛሬ እን
ደገና እኛ ከፈቀድን ኑ ብንላቸው አቤት ብለው ሮጠው ይመጣሉ ።
መሣሪያም ካገኙ አፈሙዛቸውን ያለማመንታት ወደ ምኒልክ ያዞራሉ
ነው ። ከሁሉ ደግሞ የሚገርመው ፣ ራስ መኰንን ያፄ ምኒልክ አክ
ስት የወይዘሮ ተናኘ ወርቅ ልጅ መሆናቸውን ፣ ከልጅነት እስከ ዕው
ቀት ባፄ ምኒልክ ቤት ያደጉት ፣ ከባላምባራስነት ሦስት ደረጃ (ግራዝ
ማች ፣ ቀኛዝማች ፣ ፊታውራሪ) ዘለው በደጃዝማችነት ደረጃ የሐረር
ገዥ የሆኑት ፣ አሁንም ከጨርጨር ግዛት ጭማሪ ጋር በራስነት ማዕ
ረግ የከበሩት ፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ የበኵር ልጅ መስለው በሙሉ
ሥልጣን የሚሠሩት ፣ በተለይ በውጫሌ ውልና በወሰኑ ጉዳይ የኢጣ
ልያኖችን ማጭበርበር እየተመለከቱ የሚናደዱት ፣ መንገሻን የከዱ
ኢጣልያኖች አሁን ምኒልክን ክዳና በሐረር እናንግሥህ ቢሏቸው ፣ እን
ደምን ሊያምኑንና መሣሪያ ሊሆኑን ይችላሉ ብለው አለመጠርጠራ
ቸው ፣ የኢጣልያኖችን የሞኝነት ብልጠት ሊያሳውቅ ከማስቻሉም
በላይ አስገራሚ ነው ።

ነገር ግን ፣ ይኸን የመሳሰለው አሳብ በገራገሮቹና ከንቱ ድንፋ
ታና ጉራ ከሚያጠቃቸው ኢጣልያኖች ዘንድ የሚደቀነው በጠቅላ
ላው የጥቁርን ዘር ከነአቅዋሙ ከመናቃቸው የተነሣ መሆኑ አይጠረ
ጠርም ። በነርሱ ግምት በአፍሪካ የሚገኝ ሁሉም ቂል ነው ። አንድነ
ትም ፣ ኅብረትም ፣ ያገር ፍቅርና የነጻነትም ስሜት የለውም ። ላበላ
ውና ላለበሰው ይሞታል ። ስለዚህም ነው አፍሪካውያኑ በቅኝ አገዛዝ
ሥር ለመውደቅ የበቁት ብለው ፣ የኢትዮጵያንም በነጻነት መኖር
በአጋጣሚና በፈረንጆች ቸልተኝነት እያመካኙ ፣ ኢጣልያ በቀላሉ
መሳፍንቱን ከፋፍላ ልትገዛቸው እንደምትችል በተለይ የቀኞቹ ክፍ
ሎች ያምናሉ ።

ይሁን እንጂ ፣ በነዚሁ ጐን በምክር ቤቱ በግራ በኩል ተቀም
ጠው በፊት ዐፄ ዮሐንስን ፣ አሁንም ዐፄ ምኒልክን የሚደግፉ
ነበሩበት ። ጣልያኖቹን ሁሉ ባንድ የክፋትና የቂልነት መስመር



መመልከት ትክክል አይሆንም ። በዶጋሊ ጦርነት ጊዜ በራስ አሉላ
መሪነት ባለቁት 500 የኢጣልያ ወታደሮች ምክንያት የቀኞቹ በራስ
አሉላና ባፄ ዮሐንስ ተናደው ፣ "ጦር ልከን እንበቀል ፣ ደርቡሾቹን
በኢትዮጵያ ላይ እናስታጥቅ" እያሉ ሲያውኩ ኡሊስ ባርቢዬሪ
የሚባለው አማካሪ ፣ "ጥፋተኞቹ አበሾች አይደሉም ። በዶጋሊ የሞ
ቱትን መበቀል ከፈለጋችሁ 5 መስቀያ አበጅታችሁ እነርሱን ወደ
ሞት አገር የላኩዋቸውን ባለሥልጣኖች ፣ ባንዱ መስቀል ላይ ዲ
ሮቢላን (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረ) ፣ በሁለተኛው ላይ ሪኮቲን
(የጦር ሚኒስትር የነበረ) ፣ በሦስተኛው ላይ ሞቺኒን ፣ በአራተኛው ላይ
አርጌውን ደቀስቋሳ ደ ፕረቲስን (ጠቅላይ ሚኒስትር) የነበረ ፣ አምስተ
ኛውን ለክሪስፒ መድቡት" ያለውን ማስታወሱ ይበቃል ።[1] እነዚህ
ሁሉ ስቅላት የፈረደባቸው ባለሥልጣኖች የምጥዋን መያዝና ቀጥሎ
ያለውን የኢትዮጵያ መሬት ወረራ በኃይል የደገፉና የመሩ ናቸው ።

የክሪስፒና የብላን መንግሥት ፣ መሳፍንቱን ባፄ ምኒልክ ላይ ማስ
ነሣት ለቅኝ ግዛት መስፋፋት መፍትሔ መሆኑን እንዳመነበት ፣ ዐፄ
ምኒልክም በርሱ ውስጥ ያሉትን የኤርትራ መኳንንት ማስከዳት ጣላ
ትን ለማዳከም የሚረዳ መሆኑን በበኩላቸው ተገንዝበዋል ። በዚሁ
መሠረት ፣ ራስ መንገሻ አዲስ አበባ ውስጥ ከዐፄ ምኒልክ ጋር ተወያይ
ተው ወደ መቀሌ እንደ ተመለሱ ፣ እርሳቸው ለኢጣልያ መሣሪያ በመሆን
ፊንታ እንዲያውም ለኢጣልያኖች ታማኝ ሆነው ሲያገለግሉ የቆዩ
ትን ደጃች ባሕታ ሐጐስን በምን አኳኋን አስከድተው ከኢጣልያኖቹ
ሲዋጉ እንደ ሞቱ ባለፈው አንብበናል ።

እንደዚሁም ፣ ነገሩ እዳር አልወጣም እንጂ ፣ ደርቡሾቹን በኢትዮ
ጵያ ላይ ለማስነሣት ተሞክሮአል ። በመጨረሻ ደግሞ ፣ ጣሊያኖች አሳ
ባቸውን ለውጠው ራሳቸው በከሰላና በአቆርዳት ከደርቡሾቹ ጋር በሚ
ዋጉበት ጊዜ ክርስቲያን ለክርስቲያን መረዳዳት ይገባልና እርዱን
ብለው ላፄ ምኒልክም ፣ ለራስ መንገሻ ዮሐንስም ጥያቄ አቅርበው
ነበር ። አሁን ግን ፣ የኢጣልያ ጠላትነትና አገር ወራሪነት ግልጽ
እየሆነ መጥቶ ሁለቱ መንግሥታት በጠብ ተለያይተዋል ። ኢጣልያኖ
ቹም ከመረብ እያለፉ የትግሬን አውራጃ መውረር ሲጀምሩ ፣ በምዕ
ራብ በኩልም ለመስፋፋት በከሰላና በአቆርዳት ተዋግተዋል ። የከሰ
ላን ከተማ እጅ ማድረጋቸው በአዲስ አበባ ተሰምቶ ስለነበረ ፣ ዳግ
ማዊ ምኒልክ በኢጣልያኖች ላይ ደርቡሾቹን ለማስነሣት የሚችሉበት

1 Gli Italiani in Africa - Angelo Del Boca, PP. 287 - 288

ጉዳይ በቤተ መንግሥቱ ውይይት ተነሥቶ አንዳንዶቹ ሱዳንን ፣ "ዘራፊና ቀማኛ ናቸው" ሲሉ ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ፣ "ለኛ ጠላትነት ከኢጣልያ ደርቡሽ ይሻለናል ። ምክንያቱም ደርቡሽ ባገር ውስጥ ሲገባ ያገኘውን ዘራርፎ ወደ አገሩ ይመለሳል ። ጣልያን ግን ፣ መሬቱን ራሱን ይሠርቃል" አሉ ይባላል ።

ከዚህ በኋላ ፣ ከደርቡሾች ጋር በኢጣልያ ላይ ለመስማማት ራስ ቢቶደድ መንገሻ አቲከምንና የቋራውን ገዥ ራስ መሸሻ ቴዎድሮስን ጉዳዩን እንዲያጠኑ ከደጃች ቢተው ጋር ተመካከረው ከደርቡሾቹ ጋር በገዳሪፍ በኩል ግንኙነት እንዲደረግ ንጉሠ ነገሥቱ አዘው ነበር ። በዚሁ መሠረት ፣ ደርቡሾቹን ለመሳብ ሲሉ በሚያዝያ ወር 1887 ዓ.ም እንደዚህ የሚል ደብዳቤ ጽፈው ነበር ።

> በኔና በናንተ መካከል አንድ ጊዜም ጦርነት ተደርጎ አይታወቅም... አሁን ከዚህ ቀደም ከመጣብን ጠላት ሁሉ የባሰ ጠላት መጥቶብናል ። የመጣው እኔንና እናንተን ባሪያ አድርጎ ለመግዛት ነው ። የኔና የናንተ ቀለም አንድ ነው ። ስለዚህ የጋራ ጠላታችንን ለማባረር እንተባበር ።

በዚሁ መሠረት ፣ ደጃች አራዶ (አርአዶ) የሚባሉ ካፔ ምኒልክ ወደ መተማ (መጺጋ —ካፍታ) ተልከው ከደርቡሾች ጋር መነጋገራቸውን ፣ የዓድዋለትም ኡስማንኤል አዝራ ፣ ቅና አሊ ፣ ኤት ታይሽ የሚባሉ የሱዳን ተወላጆች ተባብሮ የመዋጋቱን ነገር ለመወያየት በንጉሡ ሠፈር መታየታቸውን የኮንቲ ሮሲኒ መጽሐፍ ይጠቁማል ። የዓድዋለት ግን ጦርነቱን አልተካፈሉም ። ከጦርነቱ በኋላ በሌላ ቀን በተርኩፍ መጥተው ከኮሎኔል ስቲፋኒ ጋር ተዋግተው መሸነፋቸውን ያረጋግጣል ።[1]

በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች መሳፍንቱም ፣ መኳንንቱም ፣ ምሁራኑም ፣ አስተርጓሚዎችም ፣ በጠቅላላው የቤተ መንግሥቱም ፣ የቤተ ክህነቱም ሰዎች እንደ እቴጌ ጣይቱ ሴቶቹ ሳይቀሩ በሚወዳቸውና በሚተማመንባቸው ሕዝብ እየተደገፉ ፣ እንዳንድ ቤተሰብ ሆነው የጠላትን ወረራ ይቃወሙ ነበር ። ስለዚህም መሳፍንቱን በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ለማስነሣትና እርስ በርስ አዋግተው የመንግሥቱን አቅዋም ለማድከም ፣ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች የሚያውጠነጥኑትን ሤራና ውስጣዊ አድማ እየተከታተሉ ያከሽፉት ነበር ። እንዲሁም

---

1 Italia ed Etiopia -Conti Rossini (ከዠኔራል ቢጋና) Veigano Ettore Guesseppe ራፖር ላይ ገጽ 135—136



በዚያው አንጻር በጣልያን ላይ ጠላት ለመፍጠር በኢጣልያ ሥር በሹመትና በገንዘብ እየተደለሉ የሚያገለግሉትን ሹማምንት ለማስከዳት በበኩላቸው ምኒልክና ጣይቱ ከአበሮቻቸው ጋር ይጣጣሩ እንደነበረ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል ።

ባለፈው ጊዜ ፣ የኢጣልያ ሰላዮች በንግድና በፖለቲካ ወኪልነት፣ በሕክምና ፣ በመሐንዲስነትና በአገር መርማሪነት በየአውራጃው ተሠማርተዋል ። በየመሳፍንቱ አጠገብ ተሰግስገው ለመሳፍንቱ እንደ ብርቅ የሚቆጠረውን የጠመንጃ ፣ የሽጉጥ ፣ የሥጋጃ ፣ የጨርቃ ጨርቅና የሽቶ ሽቀጥ እያደሉ ወሬ ፣ ለሚያመጣ ጸሐፊና አስተርጓሚ የገንዘብ ጉርሻ እያጠገቡ በመስለል በኢትዮጵያ መንግሥት አቅዋም ላይ አድማ ያውጠነጥናሉ ። እዚሁ አገራቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ሆነው ተንኮላቸውን በተንኮል ከመቃወም በቀር በሮማ ምክር ቤት የቀኙና የግራው ክፍል የሚያደርገውን የከረረ ጠብና ክርክር ምኒልክና ተከታዮቻቸው በሥፍራው በመገኘት ጠቡን ለማፋፋም ቀርቶ ጉዳያቸውንና ሰላማዊ አቅዋማቸውን ፣ ጥቃታቸውንና ብሶታቸውን በተቃዋሚ አማካሪዎችና በጋዜጦቻቸው በኩል የመግለጽ አቅም አላገኙም ።

በታላቁ የምክር ቤት እነኡሊስ ባርቢዩሪ ፣ እነገብርኤል ሮዛ ፣ እነናፖሊዎን ኮላጅያኒ ፣ እነፊሊፖ ቱራቲ ፣ እነአንድሪያ ኮስታ ፣ እነኢምብሪያኒ ማቲዎ ከነጓደኞቻቸው ፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልተማረ ያልሠለጠነ በአውሬነት የሚኖር ነውና ኢጣልያ ይዛ ልታሠለጥነው ይገባል" ከሚሉት የቀኝ ክፍሎች ጋር ፣ "የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ ሥልጣኔ ያለው ሕዝብ ነው ፤ አሁንም ሰላምና ጸጥታ በሚፈልገው በምኒልክ መሪነት የአውሮፓን ሥልጣኔ ባገሩ ውስጥ ከማስገባት ላይ ይገኛል ። አበሻን እናሠልጥን ከማለት የራሳችሁን ወደኋላ የቀረውን አውራጃ (ሲሲል ሳርዲኛ . . .) አሠልጥኑ መሬቱን አልሙ" እያሉ መጨቃጨቃቸውን ጭምጭምታውን በፈረንሳዮቹ በነሞንዶን ፣ በመስኮቦቹ በነሌዎንቴቭ በኩል ዘግይቶ ከመስማት በቀር ችሎታቸው ከዚህ አልፎ ሮማ አይደርስም ።

በአለፈው ዘመን ፣ የውስጡ የርስ በርስ ጦርነታችን ፣ የቤተ ክህነቱ ስለ ሥልጣኔ ያለው ጥብቅ ተቃዋሚነት ፣ የነገሥታቱና የመሳፍንቱ ባለጉልታዊ አቅዋም ሁሉም ተደራርበ ኢትዮጵያን ከሥልጣኔ ወደኋላ አስቀርቶ ከዚህ ሁኔታ ላይ ማስገኘቱ አሳዛኝ መሆኑ ቢታወቅም ፣ በዚያው ባላቸው የኋላ ቀር አቅዋም ፣ የኛዎቹ ፖለቲካውን በፖለቲካ ፣ ወታደራዊውን በወታደራዊነት አቅዋም እየታገሉ የመጨረሻ አሸናፊ መሆናቸው ከአድናቆት ጋር ያስመሰግናቸዋል ።

# ምዕራፍ ሐያ ሦስት

## ስለ ዋግሹም ብሩ መያዝ — ስለ መሐንዲሱ ካፑቺ መታሰር

ዋግሹም ብሩ፣ ከላይ ከነገደ ዛጉዬ ከወረዱት ከላስታ ባላባቶች ከዚህ እንደሚከተለው ይወለዳሉ ። የላስታው ወንድ ወሰን ላዬ ፋሲል በስ ድስተኛ ደረጃ የምትወለደዋን ወርቅ ውሃን አግብተው ደጃች በቀቱ ንና ራስ ኃይሉን ፣ ደጃች ተድላን ፣ የዋድላውን ራስ መሸሻንና ወይ ዘሮ አይቼሽን ይወልዳሉ ።

ከዋግ ደግሞ ፣ ዋግሹም ክንፉ ዋግሹም ወሰንንና ወይዘሮ በተሐን ይወልዳሉ ። ወይዘሮ በተሐ ከአቶ አምኃ ዋግሹም ገብረ መድኅንን ፣ ገብረ መድኅን ከወይዘሮ አይቼሽ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስንና ዋግሹም ብሩን ይወልዳሉ ። ዋግሹም ወሰን ደግሞ ዋግሹም ተፈሪን ፣ ተፈሪ ዋግሹም ከበደን ፣ ዋግሹም ከበደ የታወቁትን አርበኛ ማገር ዠኔራል ኃይሉንና ደጃች በላይን ይወልዳሉ ። የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባለቤት ወይዘሮ ላቀች የዋግሹም ብሩ ልጅ ናቸው ።

ዋግሹም ብሩ ፣ ከወንድማቸው ካዬ ተክለ ጊዮርጊስ ጀምሮ ባዬ ዮሐንስም ፣ አሁንም ባዬ ምኒልክ ጊዜ የዋግሹምነቱን ሹመት ይዘው ላስታንና ዋግን ያስተዳድራሉ ። አዲስ አበባ በመጡ ጊዜ ፣ በታላቁ ቤተመንግሥት በአዳራሹ ግብር በተደረገበት ሰዓት ሌሎች ራሶች በብር ሰንና ብርት እጃቸውን ታጥበው ሲበሉ ፣ ለዋግሹም ብሩ እንደ ቆየው ልማድ የወርቅ ሰንና ብርት ቀርቦላቸው መታጠባቸውን ፣ ዋግሹሙም ሁለት ጊዜ ብር በእጃቸው ተርፍሰው እብርቱ (ማህን) ላይ ማፍሰሳቸውን ከዚህ በፊት ተገንዝበናል ።

እርሳቸውም ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስም ከአዲስ አበባ ወደ የግዛታ ቸው እንደ ተመለሱ ራስ መንገሻ ከኢጣልያኖቹ ጋር በኰዓቲትና በሰን ዓፌ ሲዋጉ የጦርነቱን ወሬ በጽሕፈት አድርገው ወደንጉሠ ነገሥቱ ልከ ዋል ። ዋግ ሹም ብሩና ራስ መንገሻ በወሰን እየተጣሉ የቆየ ጠብ ነበራቸው ። ምናልባት በ1863 ዓ.ም. ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስና ዐፄ ዮሐንስ ተዋግተው ያዬ ዮሐንስ አሸናፊነትና ዙፋን መቀማት ቂሙ ከወንድማ ቸው ከዋግሹም ብሩ ገና አልጠፋም ይሆናል ። በዚሁ የተነሣ ራስ መንገሻ ከኢጣሊያኖች መዋጋታቸውንና የርሳቸውንም ጠብ ገልጠው

ወዳዐፄ ምኒልክ ልከው ኖሮ ንጉሠ ነገሥቱም ፣ “ውሾች እርስ በርስ ሲጣሉ ሌላ አውሬ ሲመጣባቸው የራሳቸውን ጠብ አቁመው ጠላታቸውን ባንድነት ይመከታሉና እናንተም ተስማምታችሁ ጠላትን መክቱ ። የሚያስታርቃችሁም ቁም ነገረኛ አቶ በየነን ልኬያለሁና ታረቁ ። የኢጣልያኖችንም ወረራ ራስ መንገሻ ስለ ጻፈልኝ ፣ ለአውሮፓ መንግሥታትና ለጣልያኖችም ጽፌያለሁ ። የአቶ በየነን* ቃል ደህና አድርገህ አድምጠው ። ደብዳቤውንም አንብበህ ከሰው እጅ እንዳይገባ መልሰህ ላክልኝ ። እስከዚያም ስንቅ እያዘጋጀህ ጠብቀን” የሚል ለዋግሹሙ ጽፈውላቸው ነበር ። ንጉሠ ነገሥቱ ይኸን ለመጻፍ የተገደዱት ፣ “ራስ መንገሻ በኢጣልያኖቹ በተሸነፉበት ወቅት ዋግሹሙ ከግዛታቸው ከላስታ አልፈው ወደ ትግሬ ግዛት ስለገፉ ፣ በዚህ ከራስ መንገሻ ጋር ተጣልተዋል” የሚለው ወሬ በአዲስ አበባ በርክቶ ተወርቶ ስለነበረ ነው ።[1]

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ፣ ዋግሹም ብሩ ካፄ ምኒልክ እየተሰወሩ ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ጋር እየተጻጻፉ ወሬ ያቀብሉ ነበር ። ከጠላት ጋር በጐን ለመላላክ ያደረሳቸው እርግጠኛው ምክንያት አይታወቅም ። ጸሐፌ ትእዛዝ ገብረ ሥላሴም ፣ “ዋግሹም ብሩ ተሸረው ልጃቸው ጓንጉል ተሾመ” ከማለት በቀር ፣ በመጽሐፋቸው ሌላ ዝርዝር አልሰጡም ። መቸም በዚያን ጊዜ እነዚህን የመሳሰሉትን መሳፍንትና መኳንንት ከንጉሠ ነገሥት ማዕከላዊ መንግሥት የሚያሸፍታቸው ፣ “የማዕረግ ስሜና ግዛቴ አነሰ ፣ በግቢ በቤተ መንግሥቱ የምጋበዝበት መሶቤ ተዋረደ” የሚለው ቅሬታ ነው ። በዚህ ምክንያት እንዳይባል አዲስ አበባ የመጡ ጊዜ እስከ አደባባይ ነጋሪት እያስመቱ መግባታቸው ፣ በግብር ጊዜ ራሶች በብር ሰንና ብርት ሲታጠቡ እርሳቸው የወርቅ ሰንና ብርት ቀርቦላቸው መታጠባቸው ተጽፏል ። መሶባቸው ከራስ መንገሻ ወልዱ ለዮሐንስ ዝቅ ብሎ ፣ ወይም በሽልማት ጊዜ ወይም ለርሳቸው የተላከው መስተንግዶ አንሶ በዚህ ተቀይመው እንደሆነ አናውቅም ። ምንም እንኳን ፣ ብሩ ያፄ ተክለ ጊዮርጊስ ወንድምና በዕድሜም በጣም የሸመገሉ ቢሆኑ ፣ መንገሻ የንጉሠ ነገሥቱ ያፄ ዮሐንስ ተከታይ አልጋ ወራሽ ፣ ባይታደሉ ነው እንጂ መንገሥ እንኳን ይገባቸው ነበርና ፣ በዘመኑ እንደ ነበረው ልማድና አስተሳሰብ ከርሳቸው ጋር መፎካከሩ የሚያምር አልነበረም ።

ባለፈው ምዕራፍ እንደ ጠቀስነው ፣ የኢጣልያ ሰላዮች በኢትዮጵያ በተሠራጩበት ሰዓት ፣ ከአዲስ አበባ ወደ ግዛታቸው ወደ ላስታ

* አቶ በየነ ይመር በኋላ ቀኛዝማች ተብለው የፖስታ ሚኒስትር የነበሩት ይሆኑ ?

1 Italia ed Etiopia . . . Conti - Rossini - PP. 127 - 131.



እንደ ተመለሱ ካፄ ምኒልክ ጋር መጻጻፋቸውን ሳያቋርጡ ፣ ባንድ ወገን በታማኝ መላከተኛ አማካይነት ፣ ከመረብ ወዲህ የተያዘውን የትግሬን ግዛት ከሚያስተዳድረው ከጄኔራል አሪሞንዲ ጋር ዋግሹም ብሩ መጻጻፋቸውና አንዳንድ ወሬ ማቀበላቸው በሰነድ የተረጋገጠ ነው ። ይኸንንም ዓይነት አድራጎት አንዳንድ የዘመኑ መሳፍንት የሚከተሉት የአኗኗር ዘዴ ነው ። ባጋጣሚ ከሁለቱ ኃያላን አንደኛው ቢሸነፍ ፣ ካሸናፊው ጋር ተስማምቶ የተሻለ ኑሮን ለመቀጠል እንዲችል ቀደም ብሎ በመጻጻፍ ወዳጅነት ለመፍጠር ሙከራ ያደርጋል ። በዚህ ጊዜ ፣ አንዳንድ መሳፍንት አንድ የግል ቁጭት ሲያድርባቸው በወገንና በጠላት መካከል ያለው ልዩነት ይጠፋባቸዋል ። የኢጣልያኖች የፕሮፓጋንዳቸው መላስ ደግሞ ፣ በዚያው እንጻር የማር ወለላ የሚፈስበት ሆኖ ይታያል ። በዚህ ሁኔታ ቀደም ባለው ጊዜ ዐፄ ዮሐንስ በትንሹ ፣ ዐፄ ምኒልክ በትልቁ ተታለው እንደነበረ የታወቀ ነው ። በመጨረሻ ግን ፣ ኢጣልያ መርዘኛ ጠላት ከመሆን አልዘለለም ።

ጊዜያዊው የትግሬ አስተዳደሪ የነበረው ጄኔራል አሪሞንዲ ፣ “ዋግሹም ብሩ በዚህ ጽሕፈት ቤት ዘንድ የታወቀውን ታማኝ አሽከራቸውን ከመቅደላ ልከው ንጉሠ ነገሥቱ ከእንጦጦ ገና አለመነሣታቸውን ፣ ያልተነሡትም የጅማው አባ ጅፋር ሸፈተ ስለ ተባለ መሆኑን ፣ የኢጣልያን ወረራ ለማገድ ራስ ሚካኤል ፣ ራስ አሉላ ፣ ራስ መንገሻ አቲከም መታዘዛቸውን ፣ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ለምኒልክ አለመታዘዛቸውንና የኢጣልያ ወዳጅ መሆናቸውን ፣ መስከቦቹ መስቀልና ንዋየ ቅድሳት እንጂ ፣ መድፍ ስለአላመጡ ምኒልክ መቀየማቸውን ፣ መሐመድ አንፋሪ በአውሳ በምኒልክ ላይ መሸፈቱን ፣ ጓንጉል ዘገዬ ጓሊማ ላይ የሸዋን ጦር ለማስቸገር ማሰቡን” አስረዱኝ ይላል ። ይኸ ጊዜ በማናቸውም ግንባር የተፈተነው ዕርቅ ስቶ ንጉሠ ነገሥቱ ከተት ሠራዊት ብለው ወደ ትግሬ ለመዝመት የሚዘጋጁበት ሰዓት ነው ። በዚህም ጊዜ የመስኮብ ንጉሠ ነገሥት የላካቸው መልክተኞች በሌዎንቴቭ መሪነት አዲስ አበባ ሲገቡ መድፍ ያመጣሉ ተብሎ ተስፋ ተደርጎ ሳያመጡ ቀርተዋል ። የጅማው አባ ጅፋር ሸፈተ ተብሎም በሐሰት ተወርቶአል ። አሪሞንዲ እላይ እንዳመለከት ነው ፣ ይኸን ማስረጃ ከዋግሹም ብሩ ካገኘ በኋላ እርሱ ደግሞ እ.ኤ.አ ኅዳር 29 ቀን 1895 ዓ.ም. ላለቃው ለጄኔራል ባራቲዬሪ ማስተላለፉን ይገልጻል ።[1] ዋናው ግን ፣ የዋግሹም ብሩ ክዳት የተገለጸው እንጂኒየር ካፑቺ የተያዘለት ነው ።

1 Documenti sul combattimento di Amba Alagge e sulla diffesa di Maccale- Enrico Voghera, P. 33, Allegato no. 10.

የኢጣልያኖች የስለላ ሥራ ፤ ከሌሎች ከተሞች ይበልጥ ያተኮረው ንጉሠ ነገሥቱ ባሉበት በአዲስ አበባ ነበረ ። በዚህም ራሱ ዋና ወኪል ሆኖ ከተቀመጠው ከኮንት አንቶኔሊ በቀር እነሊዮፖልዶ ትራቪርሲ ፤ እነኮንት ሳልምቤኒ ሁሉ በተቻለ መጠን አዲስ አበባን በጠብ እስኪለቁ ድረስ ካገር ተወላጅ ጋር ግንኙነት በማድረግ ስለላቸውን አላቋረጡም ነበር ።

ከእነዚህ ሁሉ የበለጠ አዲስ አበባ ተቀማጭ ሆኖ በስለላ ሥራው በኢጣልያ ባለሥልጣኖች ዘንድ የታወቀውና ከፍተኛ ግምት የተሰጠው እንጂኒየር ሉዊጅ ካፑቺ ነው ። ይህ ሰው እ.ኤ.አ. በ1870 ዓ. ም. ከነማርኬዝ አንቲኖሪ ጋር ወደ ሸዋ (አንኮበር) መጣ ። ከርሱም ጋር ጕሴፔ ኪያሪኒ የሚባለው ጓደኛው አብሮት ነበር ። ማርኬዝ አንቲኖሪ ልጥ ማረፍያ የሚባለው መሬት ለማረፊያ ተሰጥቶት በዚያ ሲኖር ከዕለታት አንድ ቀን ወደ አደን ሲሔድ የገዛ ጠብመንጃው ባርቆበት ሞተ ። ኪያሪኒ ደግሞ ፤ አንቶኒዮ ቼኪ ከሚባለው ከሌላ ጓደኛው ጋር ሆነው አገር እንመረምራለን ብለው ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሔደው ሳለ ፤ ከከፋ አልፈው ጌራ ሲደርሱ የጌራ ንግሥት (ጌራጌኔ) አገሩ በወቅቱ በማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣን ሥር ባለመሆኑ ፤ “የምኒልክና የጐበና ሰላዮች ሳትሆኑ አትቀሩም” ብላ አሰረቻቸው ። ኪያሪኒ ሲሞት አንቶኒዮ ቼኪ ምጥዋ ያሉት ኢጣልያኖች ላጼ ዮሐንስ ነግረው እርሳቸው ለጐጃሙ ለራስ አዳል (ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት) “ተላልከህ አስፈታው” ብለው ስለላኩ ፤ ራስ አዳል ከጌኔ ጋር ተላልከው አስፈትተውታል ። ከዚያ ወደ ውጋዴን ሔዶ የዓድዋ ጦርነት በየካቲት ሲደረግ እርሱ ቀደም ብሎ በኅዳር ወር ሞቃዲሾ አጠገብ ላፎሊ ከሚባለው ሥፍራ ሲደርስ የተከተሉት ሰዎች ከድተው ገደሉት ።

እንጂኒየር ካፑቺ ግን ፤ ዐፄ ምኒልክ አንኮበርም ፤ እንጦጦም ፤ አዲስ አበባም የነበሩ ጊዜ ሳይለይ ፤ ስራሱም ንግድ እየነገደ ፤ በተረፈ የታዘዘውን የቤትና ማናቸውንም የመሐንዲስነት ሥራ እየሠራ በማገልገልና ንጉሠ ነገሥቱን በማስደሰት ኖረ ። ዐፄ ምኒልክም ወደኋላ የቀረች አገራቸውን ለማሠልጠን ባላቸው ፍላጐት የእጅ ብልሃትና ትጉኅ ሠራተኛ በጣም ይወዱ ነበርና ፤ በሙያው አቅርበውት በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የብዙ ሕንፃ ሥራ ተካፋይ ነበር ።አሁን ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ከሆኑ ወዲህ ፤ በውጫሌ ውል በ17 ኛው አንቀጽ ያለው አይስማማንምና ሠርዙ ፤ አንድ ጊዜ ተዋውለናልና አንሰርዝም ፤ አገር ይዛችኋልና ልቀቁና በወዳጅነት እንስማማ ፤ አንለቅም በሚለው አሳብ ከፍ ያለ ውዝግብ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል በተቀሰቀሰበት ሰዓት ፤ መሐንዲሱ



ካፑቺ ካንዳንድ ባለሥልጣኖች ይልቁንም ካስተርጓሚዎችና ከጸሐፊዎች ጋር በግል ወዳጅነት እየተገናኘና ወሬ እየሰበሰበ ምሥጢራዊ የሆነ የጽሑፍ ግልባጭ እስከ ማግኘት ደርሷል ። ያንን በግልጽም በቁጥር ቃልም እያደረገ ፤ በሸምበቆ ዘንግ ውስጥ እያስገባ ወደ ሮማ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፤ ብዙ ጊዜም ወደ አሥመራ ለጄኔራል ባራቲዬሪ ፤ አንድ አንድ ጊዜም ዘይላና ኤደን ለሚገኙት የኢጣልያ ቆንስሎች ይልክ ኖሯል ። እስኪያዝ ድረስ 95 ጊዜ በቁጥር ቃል እያደረገ በልዩ ልዩ መንገድ የስለላ ወሬ ጽፏል ። የተያዘበት 96ኛው ስለ መስኮቦች አገባብ የሚናገር ነው ።

ጠቅላይ አዛዡ ጄኔራል ባራቲዬሪ ፤ ኢጣልያ አገር ለሚገኘው ጓደኛው ለጄኔራል ዳልቬርሜ እ.ኤ.አ. ግንቦት 12 ቀን 1895 ዓ.ም. ከምጥዋ በጻፈለት ረዥም ደብዳቤ ውስጥ በመጨረሻ ፤ “ . . .ከኮዓቲት ጦርነት ወዲህ ምኒልክ ወደፊት ገፍቶ ቅኝ አገሮቻችንን ለመውረር ፕላን እንዳለው የካፑቺ ደብዳቤዎች ያስረዳሉ ። የካፑቺ ስም በጋዜጣ እንዳይወጣ ተጠንቀቅ”[1] ብሎታል ። በኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቤተ መዛግብት ስለርሱ የሚናገረው ማስታወሻ ደግሞ እንደዚህ ይላል ። “መሐንዲሱ ካፑቺ ፤ ብልሁ ደፋሩ ፤ የተከበረው . . .የሸዎቹን ጥብቅ ቁጥጥር አልፎ ጠቃሚ ማስረጃዎችን ይልክ ነበር”[2] ከዚሁ በማያዝ ፤ “እንደዚሁ እንደ ለመደው ፤ ከዕለታት አንድ ቀን የስለላ ደብዳቤውን አዘጋጅቶ ፤ በሸምበቆ ዘንግ ውስጥ በዘዴ አስገብቶ በዘይላ በኩል ለኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሲልክ ፤ ያው የተላከው ፖስታ አመላላሽ ምስጢሩን አውጥቶ ያቶ ጳውሎስ ዘበኞች ይዘውት ወደ አዲስ አበባ አመጡት” ሲል ያስረዳል ። የተያዘው ፖስተኛ ስሙ ደስታ መሆኑን ዶክተር ሳሊምቤኒ በጻፈው ማስታወሻ ያረጋግጣል ።[3]

የርሱም በስለላ መያዝ በዙሪክ (ስዊስ) ጋዜጣ ተጽፎ ነበር። ከዚያ በኋላ ራሱ በጽሑፍ ያስፈረው ቃል እንደዚህ የሚል ነው ።

> በየካቲትና በመጋቢት መካከል ስለኔ ጉዳይ ስብሰባ ተደርጎ ሳለ ፤ ንግሥቲቱ (ጣይቱ) በገርፉ (አዳል) በኩል ወደ አገሩ ይግባ ብላ ልታስገድለኝ ስታስብ ንጉሠ ነገሥቱ አገር ለቆ ይውጣ አሉ ። አዛዥ ወልደ ጻድቅ ደግሞ ፤ እዚሁ መያዣ ሆኖ ይቀመጥ ስላሉ የርሳቸው አሳብ ጸደቀ ። . . .ግንቦት 8 ቀን 1895 ዓ.ም. ምኒልክ ከአዲስ አበባ ወደ ወረይሉ ሔዱ . . .ከሁለት ቀን በኋላ የምንነጋገረው ነገር አለና እንድትመጣ የሚል ቃል ስለ ደረሰኝ ፤ ወደዚያ እንደ ሔድሁ ታሰርሁና

1 Precursori del Impero Africano - R -Truffi, PP. 196- 197.
2 Ibid, P. 228
3 Crispi e Menelich . . P. 246.

> የውጭ አገር ሰዎች ያሉበት አንድ የፍርድ ዓይነት ጉባኤ ሆነ ። በጉባኤው ላይ የነበሩ ስድስት የፈረንሣይ ፣ ሁለት የእርሞን ፣ አንድ የግሪክ ተወላጆች ነበሩ ። ክሱ በሰላይነት ነበርና ንጉሡ የምትጸጸፍ በትን የቁጥር ቃል ብትሰጠኝ እለቅሀለሁ አሉኝ ። እኔም የቁጥሩን ቃል አልሰጥም ብዬ እስራቴ አላግባብ መሆኑን ተከራከርሁ ። ስለዚህ ጉዳይ ፣ እዚያ ያሉት ፈረንጆች አሳባቸው ተጠይቆ በዚያን ጊዜ ሙሴ ሽፍኔ ስለ ሁሉም ሆኖ ፣ "ስላገርዎ ጸጥታ ሲሉ በዚህ ሰውዬ ላይ ማናቸውንም እርምጃ ለመውሰድ መብት አለዎት ..." ብሎ ተናገረ .... ሙሴ ሞንዶን ግን ፣ መሰቀል አለበት ብሎ ነበር ... ከዚህ በኋላ ወደ ኮላሽ አምባ ተወስጄ ታሰርሁ ። .... ከዚያም ለማምለጥ ስሞክር ተይዤ በእግር ብረት ታሰርሁ ። ... ከዚያ ደግሞ በኅዳር ወር እግር ብረቱ ወለቀልኝ ። ..[1]

በዚህ ዓይነት ፣ ከአዲስ አበባ እ.ኤ.አ. ሚያዝያ 20 ቀን 1895 ዓ.ም. በቁጥር 88 ያስተላለፈው የቁጥር ቃል ስላዬ ምኒልክ ጉዞ ወደ ቦሩ ሜዳ ፣ ስለ ተከተላቸው የሠራዊት ቁጥርና እንደዚሁም ኢትዮጵያና መስኮብ በመተባበር ከኢትዮጵያ የእንግሊዝ ሥልጣን እንዲወገድ ሁለቱ መንግሥታት መመካከራቸውን የሚገልጽ ነው ። ካፑቺ በኮላሽ አምባ እንደታሰረ ፣ ከግንቦት ወር 1887 ዓ.ም. ጀምሮ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ እስከ ኅዳር ወር 1889 ዓ.ም. እንደቆየ ፣ የኢትዮጵያና የኢጣልያ መንግሥታት ስምምነት አድርገው ምርኮኞች ሁሉ ሲለቀቁ ፣ እርሱም በዚህ ጊዜ አብሮ ተለቀቀ ።

ዳግማዊ ምኒልክ ፣ ከወላሞ (ወላይታ) ጦርነት እንደ ተመለሱ ፣ ሹም አጋሜ ተሰፋዬ ከራስ መንገሻ ተልከው መጥተው ፣ "ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ወሎ ብቅ ቢሉ ወደፊት ገፍቶ ብዙ አገር የያዘው የኢጣልያ ጦር ወደ መጣበት ሊመለስ ይችላል" ብለው በነገሯቸው ጊዜ ፣ ላዩን አዲስ የሚሠራውን የግሼን ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ለመጎብኘት አስመስለው ፣ ውስጡን ኢጣልያኖቹን ለማስፈራራት ወረይሉ ሔዱ ። በዚህም ወቅት ዋግሹም ብሩ ከኢጣልያ ባለሥልጣ ኖች ጋር ግንኙነት አድርገው ይላላካሉ የሚለው ወሬ በዝቶ ነበርና ካፑቺ በታሰረ በሁለተኛው ወር ዋግሹም ብሩም ታሰሩ ።

የዚህን ጉዳይ በዘመኑ ንጉሠ ነገሥቱን እየተከተሉ የጦርነቱን ሁኔታና ያገር ውስጥ ወሬ ባዲስ አበባ ለቀሩት ፈረንሳዮች በጽሕፈት ያስረዱ የነበሩት አስተርጓሚው ግራዝማች ዮሴፍ ፣ ለሙሴ ሞንዶን ቪዳዬ የጻፉለትን ስናነብ የነገሩን ምክንያት በትክክል ያብራራልናል ። ደብዳቤውም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈው ነው ።

---

1 Precursori del Impero Africano - R.Truffi, P. P. 225 - 231.



ይድረስ ከሙሴ ሞንዶን በሰኔ 13 ከጻፍሁልዎ በኋላ የተገኘ ወሬ እልክልዎታለሁ ። ዋግሹም ብሩ ጃንሆይ ለሰጠርተዋቸው መጡ ። ከዚህ በኋላ ደጃች ሐጎስ ተፈሪ በአዲግራት (ከኢጣልያኖች ጋር) ያለ ፣ የላ ከው ሰላይ ከጃንሆይ ፊት ቀርቦ ቢጠይቁት ለጌታ አድራለሁ ብዬ መጣሁ አለ ። በኋላ ግን ፣ ዐርባ ኸራፍ ይገረፍ ብለው ቢያዙ ሦስት ጊዜ እንደ ተመታ እውነቱን ልናገር አለ ምስጢሩን አወጣ ። ዋግሹም ብሩ ካፖት (ካፑቺ) የሚባል ነጋዴ ታስረ ብለው ወደ ጀኔራል ባራቲዬሪ ቢልኩ እውነቱን ለማወቅ ፣ ደግሞ ራስ አሉላ ትግ ሬን ሁሉ ይዘው ተነሥተዋል ቢሉ ፣ ያሉበትን ለማወቅ ጃንሆይም ወረ ይሉ መከረማቸውንና አለመከረማቸውን ለመመርመር መጣሁ ብሎ ተናገረ ። ከዚህም በኋላ በጣም ቢገረፍ እንደሱ ያሉ ሌሎች ሰባት ሰላ ዮች አሰያዘ ። እነዚያም ሰባቱ የጃንሆይ ጠበንጃ ይዘው ሰላይ ሆነው ተገኙ ። ይህ ሁሉ የክፎች ሥራ ነው ።

በሰኔ 10 ቀን እሑድለት ራሶችን ሁሉ በጧት አስጠሩ ። ደጃዝማቾ ችም ተጠሩ ። አራዳ ላይ ነጋሪት ወጥቶ ይመታ ጀመር ። ዋግሹም ብሩም ከመኳንንቶቻቸው ጋር ተጠርተው ገቡ ። ዘበኛው ሁሉ ተሰ ልፎ ነበር ። ከዚህም በኋላ ጃንሆይ የወቀሳ ደብዳቤ አጽፈው ራስ ቢትወደድ መንገሻን ፣ አለቃ ገብረ ሥላሴን አሲይዘው ከነዚህ በራት ሊጋባ ሠራዊቱን ዘበኞች አስከትለው የዋግሹምን እጅ ለመያዝ ሰደዱ ። እጃቸው ከተያዘ በኋላ የወቀሳ ደብዳቤ ተነበበ ። ቃሉም ይህ ነው ።

... የካፑቼን (ካፑቺን) መያዝ ወደ ኢጣልያኖች ልከሃል ። ራስ መንገሻ ሲዋጋ እርዳኝ ቢልህ ሳትረዳው ቀረህ ። ሹም አጋሚ ተሰፋዬ ወደኔ ሲመጣ ሽፍታ ልከህ አስወጋኸው ። የፈሰስ ብር* አውጣ ብልህ እምቢ አልህ ። ለወታደር ቀለብ ያስራት እህል ሰብስብ ብልህ ሳትሰበስብ ቀረህ ። ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎህ በኢጣልያኖች ሰፈር የሰ ቆጣው ጌታ ከገባልን ምኒልክ ሊያቅተን ነወይ እያሰኘህ ታስደነፋ ብኛለህ ። ይህን የመሰለ ነገር ሌላ ሌላ ነገር ሁሉ ደግሞ የወቀሳ ደብ ዳቤ ተነበበላቸው ። ከዚህ በኋላ አገርህን ለልጅህ ለዋግሹም ጓንጉል ሰጥቸዋለሁ ። አንተም ጉዳዩን ሰጨርሰ እፈታሃለሁ ነፍጥህን ከብት ህን በደብዳቤ ለጓንጉል አስረክብ አሏቸው ። ከዚህ በኋላ አራዳ ላይ ዓዋጅ ሲነገር የዋግ ሰው ዋግሹም ብሩን ማሰሬ እየወሳለተ ቢያስቸ ግረኝ ነው ። አገሩን ለሌላ ሰው አልሰጠሁ-ብህም ለጌታህ ልጅ ነው ። ይህንም ማድረጌ እንድትወደኝ ባውቅህ ነው ። ዋግሹም ጓንጉልን ያልተ ከተልህ አይቀጡ ቅጣት እቀጣሀለሁ ብለው ዓዋጅ አስነገሩ ።[1]

በዚህ ዓዋጅ ዐፄ ምኒልክ ፣ በዚህ የጦርነት ሰዓትና በዓድዋ ውጊያ ዋዜማ የላስታንና የዋግን ሕዝብ ላለማሳዘን ጥንቃቄ እንዳ ደረጉ ይታያል ። ሌላ ደጀ ጠኚ ሳይጠፋ ሹመቱን ለግዞተኛው ልጅ ለዋግሹም ጓንጉል መስጠታቸው በዚህ በጉልተኝነት ዘመን ሕዝቡ

---

* የፈሰስ ብር ለጦርነቱ ከሕዝብ ላይ መዋጮ እንዲደረግ የታዘዘው ፈሰስ ይባላል ።

1 ፓሪስ ቤተ መጻሕፍት ከሞንዶን ቪዳዬ ፋይል ቁ. 92.

"ጌታችን ቢታሰሩ የተሾመው ያው የጌታችን ልጅ ነው" ብሎ ደስ ብሎት ኅብረቱን እንዳይነፍግ ነው ። በእውነትም ዋግሹም ጓንጉል ከዚህ ጊዜ ዠምሮ በአላጌውም ፥ በመቀሌውም ፥ በዓድዋውም ጦርነት ሳይለዩ አገልግሎታቸውን ላገራቸውና ለንጉሠ ነገሥቱ በትጋት በመቀጠል ያባታቸውን ጉድለት አሟልተው ፈጽመዋል ። በዚህ ላይ ደግሞ ፥ ወይዘሮ ላቀች ብሩ የንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ባለቤት ከመሆናቸው በላይ የዋግሹም ብሩ ትውልድ ከዋድላ ፥ ከደላንታ ፥ ከትግሬና ከጐጃም ባላባቶች ጋር በአምቻ በጋብቻ ስለተሳሰረ ፥ በዚህ በጦርነት ዋዜማ ሕዝቡን ለማስተባበር ያለግልፍታ በብልህነት ሁሉንም አስታሞ መያዝ ያስፈልጋል ። ያፄ ምኒልክ ጠባይ ከዚህ ሁኔታ ጋር ሰምና ወርቅ ሆኗል ማለት ይቻላል ።

በዓለም አቀፍም ፥ በአገር ደረጃም ቢሆን ፥ በማናቸውም ጊዜ ስላይ ሆኖ ያገሩን ምስጢር ለባዕድ ያቀበለ ቅጣቱ ከፍ ያለ ነው ። በጦርነት ሰዓት ደግሞ አገሩን ከድቶ ያገሩን ወታደራዊ ምስጢር ለወራሪ ጠላት ያቀበለ በሞት እንደሚቀጣ አይጠረጠርም ።

ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ መሳፍንት በመከፋፈል ፥ በተለይ በዘመነ መሳፍንት በቀላሉም ፥ በከባዱም ጉዳይ እርስ በርሷ ስትተላለቅ ኖራለች ። ያ ጊዜ አልፎ አሁን የሰላምና የጸጥታ ጊዜ ተገኝቶ ሕዝቡም ወታደሩም ከጦርነት ሁካታና ከምዝበራ ሊያርፍ የገመረበት ጊዜ ነው ። በደቡብ ኢትዮጵያ በከፋ ፥ በወላሞ ፥ (ወላይታ) በአሩሲ ፥ (አርሲ) በሲዳሞ ፥ በባሌ በሐረርጌ ጦርነት ቢደረግም ፥ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ወሰኗን ለማግኘት የብሔርን አንድነት ሰብስቦ አንድ ብሔራዊ ቤተ ሰብ ያለበት መንግሥት ለማዋቀር ስለሆነ ፥ ጦርነቱ ወግና ሥርዓት ያለው ነው ።

ስለዚህ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ በተለመደ ትዕግሥታቸው ፥ ዋግሹም ብሩን በሞት በመቅጣት ፈንታ ለጊዜው በግዞት ቦታ አስቀምጠው እንዲያውም ፥ "ጉዳዩን ስጨርስ (ከኢጣልያ ጋር የማደርገውን ጦርነት) እፈታሃለሁ" ማለታቸው ፥ ሹመቱን ከቤተሰባቸው አለማውጣታቸው ጉዳዩን በኃይል ሳይሆን ፥ በልስላሴና በማስታመም እንደ ያዙት በግልጽ ይታያል ። ይህም የርስ በርስ ጦርነትን አግዶ በዚህ ፈንታ የሕዝብን ክንድ በጠላት ላይ ያስተባብራል ።

በዚህ ዓይነት ትዕግሥት ነው ዐፄ ምኒልክ እያንዳንዱ ፥ "ማን ከማን ያንሣል ፥ ማን ለማን ያደገድጋል" እያለ እርስ በርስ በመዋጋት የተለያየውን መስፍን ሁሉ ፥ በሥልጣናቸው ጥላ ሥር ሰብስበው በአንድ እግር አቁመው በማዋጋት ወደፊት የምናነበውን ዓለምን ያስደነቀውን የዓድዋ ድል ያገኙት ።



ደጃዝማች ባሕታ ሐጎስ በሐላይ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ በቆአቲትና በሰናፌ
እና ቀኛ አዝማች ኃይለማርያም በደብረ ኃይላ የተዋጉባቸውን
ቀበሌ የሚያሳይ ካርታ

